በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች

ADDIS ABABA

በ

ተስፋ አከለ

ሰኔ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የአማርኛ ቋንቋ  አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ

በከፊል ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት

በ

ተስፋ አከለ

ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች


በ

ተስፋ አከለ


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ ፊርማ

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምሥጋና ........ i
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ ii
የአባሪ ማውጫ ........ iv
አጠቃሎ ........ v
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ ዓላማ ........ 4
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5
1.4 የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.5. የቃላትና የሐረጋት ፍቺ ........ 6
ምዕራፍ ሁለት ........ 8
የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ........ 8
2.1. የተከታታይ ምዘና ምንነት ........ 8
2.2. የተከታታይ ምዘና ባህሪያት ........ 9
2.2.1. ተከታታይ ምዘና ስርአታዊ ነው (Systematic) ........ 9
2.2.2. ተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው (Cumulative) ........ 9
2.2.3. ተከታታይ ምዘና ሁሉአቀፍ ነው (Comprehensive) ........ 10
2.2.4. ተከታታይ ምዘና አቅጣጫ ጠቋሚ ነው (guidance oriented) ........ 10
2.3. የተከታታይ ምዘና ዓላማ ........ 11
2.4. ተከታታይ ምዘና ለምን ያስፈልጋል? ........ 12
2.5. በተከታታይ ምዘና እና በተለምዶአዊው ምዘና መካከል የሚስተዋሉ ጉልህ ልዩነቶች ... 14
2.6. የተከታታይ ምዘና የሂደት ደረጃዎች ........ 15
2.7. የተከታታይ ምዘና መሠረታዊ መርሆዎች ........ 16
2.8. የተከታታይ ምዘና ጥቅም እና ደካማ ጎኖች ........ 18
2.8.1. ተከታታይ ምዘና ለመምህራን የሚሰጠው ጥቅም ........ 18
2.8.2. ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች የሚሰጠው ጥቅም ........ 19

A.A.U. LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

2.8.2.1 የማስተካከያ እገዛ (Remediation) 20
2.8.2.2. የማጠናከሪያ እገዛ (Enrichment Activities) 20
2.8.3. የተከታታይ ምዘና ደካማ ጎኖች 20
2.9. በተከታታይ ምዘና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች 21
2.9.1. ተማሪዎች በምዘና ላይ ያላቸው ግንዛቤና ልምድ 21
2.9.2. መምህራን በተከታታይ ምዘና ላይ ያላቸው ግንዛቤና ልምድ 22
2.10. ምጋቤ ምላሽና ተከታታይ ምዘና 23
2.11. ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር የሚያስችሉ መሠረታዊ ነገሮች 24
2.12. የምዘና ስልቶች ወይም ዘዴዎች 26
2.12.1 የቃል ጥያቄ 27
2.12.2. ምልከታ 28
2.12.3. ቅድመ ፈተና 28
2.12.4. የቤት ሥራ 29
2.12.5. ፈተና እና ሙከራ 29
2.12.6. ፕሮጀክት 30
2.12.7. የመምህር- ተማሪ ውይይት 32
2.12.8. ሰነደ ትምህርት 33
2.12.9. የራስ ምዘና 34
2.12.10. የጓደኛ ለጓደኛ (የቢ.ጤ.) ምዘና 35
2.12.11. እየወጡ ማቅረብ 36
2.13. የቀደምት ተጓዳኝ ጥናቶች ቅኝት 37
ምዕራፍ ሦስት 39
የጥናቱ ዘዴ 39
3.1. የመረጃ ምንጮች 39
3.2. የአሠልጣኝ መምህራንና የተማሪዎች አመራረጥ 39
3.3. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች 42
3.3.1. የጽሑፍ መጠይቅ 42
3.3.1.1. ለመምህራን የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ 42
3.3.1.2. ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ 43
ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

3.3.2. ቡድን ተኮር ውይይት ........ 44
3.3.3. የሰነድ ፍተሻ ........ 45
3.3.4. ምልከታ ........ 45
3.4. የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል ........ 45
3.5. የመረጃ አተናተኑ ዘዴ ........ 46
ምዕራፍ አራት ........ 47
የመረጃ ትንተና ........ 47
4.1. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 47
4.2. የአሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች(ዘዴዎች) አጠቃቀም ........ 56
4.2.1. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች ከአሠልጣኝ መምህራን ምላሽ አንፃር ........ 57
4.2.2. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና ሥልቶች ከተማሪዎች ምላሽ አንፃር ........ 59
4.2.3. የአሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸውን የምዘና ስልቶች አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላሽ እና ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ልዩነት ትንተና ........ 61
4.2.4. በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች ........ 62
4.2.5. የተከታታይ ምዘና ሥልቶችን አስመልክቶ ከጽሑፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኙ ውጤቶች ማብረሪያ ........ 63
4.3. የተከታታይ ምዘና አተገባበርን በተመለከተ ከአሠልጣኝ መምህራን የተገኘ ምላሽ 64
4.4.ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ አሠልጣኝ መምህራን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 68
4.5. ተማሪዎች ስለ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 71
4.6. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በጽሑፍ መጠይቁ እና በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ለቀረቡላቸው ልቅ ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ትንተና ........ 81

4.7. ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቁና በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ለቀረቡላቸው ልቅ ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ትንተና ........ 83
ምዕራፍ አምስት ........ 86
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሐሳቦች ........ 86
5.1. ማጠቃለያ ........ 86
5.2. መደምደሚያ ........ 90
5.3. የመፍትሔ ሐሳቦች ........ 92
ዋቢ ጽሑፎች ........ 94
አባሪዎች ........ 99

# ምስጋና

ጥናቱ ተጀምሮ ለፍፃሜ እስኪበቃ ድረስ የጥናቱን ረቂቅ በማንበብና ቅርፅ በማስያዝ የዘወትር ድጋፋቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለዶክተር አረጋ ኃይለሚካኤል ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስ:: ያለእርሳቸው ብርቱ ድጋፍ ጥናቱ እዚህ ደረጃ ላይ ሊደርስ አይችልም ነበርና::

ከጎኔ ሁናቸው ለጥናቴ የሚሆኑ ጠቃሚ ፅሁፎችንና ሐሳቦችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ ጓደኞቼ ሙሉሰው አሰራቴ፣ ታየ ገረሱ፣ አንለይ አዳነ እና የሺጥላ ምንይልሸዋ ምስጋናዬ ኗሪ ነው::

ለጥናቴ የሚሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችን በምሰበስብበት ወቅት ትብብራችሁ ላልተለየኝ የመቀሌ፣ ዓብይ ዓዲ እና የዓድዋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የቋንቋ ትምህርት ክፍል አሠልጣኝ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም የአስተዳደር አካላት ከልብ አመሰግናችኋለሁ:: በተለይም ሀብታሙ ደስታ ያደረግህልኝን ትብብር አልረሳውም::

የጥናቱን ረቂቅ በመተየብና በማስተካከል ከፍተኛ እገዛ ላደረጋችሁልኝ ለባለቤቴ ለኑርዓይኒ አብደልለጢፍ እና ለንብረት ኃይሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ::

ሙሉ ደመወዜን እየከፈለ ላስተማረኝ የዓድዋ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ በጣም ከፍተኛ ምሥጋና አቀርባለሁ::

በመጨረሻም ለጥናቱ የሚሆን የምርምር ማካሔጃ ገንዘብ በመስጠት የተባበረኝንና ያስተማረኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ከልቤ አመሰግነዋለሁ::

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

# የሠንጠረዥ ማውጫ


ሠንጠረዥ ገጽ

1 በሦስቱ ኮሌጆች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ............................ 40

2 በሦስቱም ኮሌጆች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአንደኛ ዓመት ተማሪዎችን አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ............................ 41

3 የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህን በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ ............................ 47

4 ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ ............................ 78

5 በተከታታይ ምዘና እቅድ ማውጣት የሚኖረውን ሚና በተመለከተ አሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ ............................ 49

6 ተከታታይ ምዘና ከቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ ጋር ስላለው ግንኙነት በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ ............................ 50

7 በተከታታይ ምዘና ተማሪዎች የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ ............................ 51

8 የተከታታይ ምዘናን ጥቅም በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ ............................ 53

9 የተከታታይ ምዘና ዓላማን በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ ............................ 54

10 ምጋቤ ምላሽን በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ............ 55

11 የተከታታይ ምዘና ሥልቶችን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው በአሠልጣኝ መምህራን የተሰጡ ምላሾችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ............ 58

12 መምህራን የተከታታይ ምዘና ሥልቶችን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው በተማሪዎች የተሰጡ ምላሾችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ.. 60

13 የተከታታይ ምዘና አተገባበርን በተመለከተ ለአሠልጣኝ መምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ............................ 64

14 ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት የሚያሳይ ሰንጠረዥ.. 69
15 የመመሪያና የመስፈርት ግልፅነትን፣ የሚደረግላቸውን እገዛና የሚሰጣቸውን ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ..................... 72
16 በተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እና የአሠልጣኝ መምህራንን የተከታታይ ምዘና ትኩረት በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ..... 74
17 አሠልጣኝ መምህራን ለተማሪዎች ያላቸውን ሚዛናዊነት በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ ........................................................................ 76
18 ከአሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ያገኙትን ጥቅም በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ........................................................ 78
19 በተከታታይ ምዘና ሂደት ስለሚሰማቸው ሃላፊነትና ከጓደኞቻቸው ጋር ስላለው ትብብር የተማሪዎች ምላሽ ............................................ 79

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# የአባሪዎች ማውጫ

አባሪ **ገጽ**


አባሪ 1፡ ለአሠልጣኝ መምህራን የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ.......................................99
አባሪ 2፡ ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ..................................................106
አባሪ 3፡ ለመምህራን እና ለተማሪዎች የተዘጋጁ የቡድን ተኮር መወያያ ጥያቄዎች.......................................................................................................111
አባሪ 4፡ የምልከታ መከታተያ ቅፅ.................................................................112
አባሪ 5፡ የዓድዋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኮርስ ቢጋር (እቅድ)..............................114
አባሪ 6፡ የዓብይ ዓዲ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኮርስ ቢጋር (እቅድ).........................116
አባሪ 7፡ የመቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኮርስ ቢጋር (እቅድ)..............................120
አባሪ 8፡ የዓድዋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የውጤት ማስፈሪያ ቅፅ.............................122
አባሪ 9፡ የዓብይ ዓዲ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የውጤት ማስፈሪያ ቅፅ.......................124
አባሪ 10፡ የመቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የውጤት ማስፈሪያ ቅፅ..........................126
አባሪ 11፡ ከመቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተማሪዎች የተወሰደ ናሙና የግል ስራ.......................................................................................................127
አባሪ 12፡ ከዓብይ ዓዲ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተማሪዎች የተወሰደ ናሙና የግል ስራ.......................................................................................................130
አባሪ 13፡ በክፍል ውስጥ ምልከታ ሲካሄድ አሰልጣኝ መምህራን ሲያስተምሯቸው የነበሩትን ርዕሶችንና ትምህርቱ የተሰጠበትን ቀን የሚያሳይ መግለጫ.................................132

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በትግራይ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሶስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው:: ይህ ጥናት ገላጭ ጥናት ሲሆን፣ የጥናቱ ተተኳሪዎች በተጠቀሱት ኮሌጆች ውስጥ ያሉ 12 የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራንና ከሦስቱም ኮሌጆች በነሲብ የዕጣ ናሙና የተመረጡ 135 የ10+3 መርሀግብር አንደኛ ዓመት የቋንቋ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: ለጥናቱ የሚሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የጽሑፍ መጠይቅ፣ የቡድን-ተኮር ውይይት፣ ምልከታና የሰነድ ፍተሻ ጥቅም ላይ ውለዋል:: በመረጃ አተናተኑ ሂደትም አሀዛዊና አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ስራ ላይ ውለዋል:: የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየውም የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ ያልተሟላ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ አሠልጣኝ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው ፈጣንና በቂ ግብረ ምላሽ እንደማይሰጡ፣ የተማሪዎቻቸውን የግልና የቡድን ስራዎች ሲያርሙ መስፈርት እንደማይጠቀሙና ተከታታይ ምዘናዎችን መቼ እና እንዴት እንደሚተገብሩ በኮርስ ቢጋሮቻቸው ላይ በግልፅ እንደማያካትቱ የጥናቱ ውጤት ያሳያል:: የተገኘውን የጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ግልፅ የሆነ የተከታታይ ምዘና ዕቅድ እንዲያዘጋጁ፣ የተማሪዎችን የቡድንና የግል የምዘና ተግባራት በመስፈርት መሰረት እንዲያርሙ፣ በተከታታይ ምዘና ሒደት ተማሪዎች የሚሳተፉበትን መንገድ እንዲያመቻቹ የመፍትሄ ሐሳቦችን ጠቁሟል::

ABABA UNIVERSITY ... LS LIBRARY

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን ማስተማርና ምዘና በጣም ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው ነገሮች ናቸው። በመሆኑም ተነጣጥለው አይታዩም። በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የሚካሔዱ ምዘናዎች የቋንቋ መማር-ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካላት ናቸው። በመሆኑም Huges(1989፤1)፣ Heaton(1988፤3)፣ Wall and Anderson (1991፤3) እንደሚገልጹት፣ ቋንቋን የማስተማር አላማዎች ግባቸውን ሊመቱ የሚችሉት ምዘናን በተግባር ላይ በማዋል ነው። ያለምዘና ደግሞ ውጤታማ የመማር -ማስተማር ሂደት ተካሂዷል ለማለት እንደሚያስቸግር NEID(1999፣ 5)ይገልፃል።

ምንም እንኳን የተለያዩ ምሁራን ቋንቋን በማስተማርና በምዘና መካከል ከፍተኛ ቁርኝት እንዳለ ቢገልጹም፣ የትኛው የምዘና አይነት የቋንቋ መማር-ማስተማሩን ሂደት የበለጠ እንደሚያግዘው ግልፅ የሆነ ነገር አላስቀመጡም። ይሁን እንጂ ምሁራን እንደሚያመለክቱት በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚሰጡት ሙከራዎችና የማጠቃለያ ፈተናዎች ተማሪው በአንድ ቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያሳየውን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዲሁም ችሎታ ሙሉ በሙሉ አያሳዩም። ለምሳሌ Shepard (2000፤4)፣ Alausa (1999፤7) እንዲሁም AED/ BESO II (2006፣ 27) እንደሚገልጹት፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ምዕራፍ ወይም ሴሚስተር ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡት ፈተናዎች ተማሪው በየዕለቱ የሚያሳያቸውን ሁለንተናዊ ባህርያት እንዲሁም የሚያከናውናቸውን ተግባራት አያመለክቱም።

ከላይ ከተጠቀሰው ሐሳብ በተጨማሪ መምህራን በተለያዩ ጊዜያት ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ፈተናዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚያገለግሉት ተማሪው በሚማረው ትምህርት ዙሪያ አልፏል ወይም ወድቋል የሚል ውሳኔ ለማሳለፍ ነው። ይህ አይነቱ የምዘና ስርአት ተለምዶአዊ የምዘና ስርአት ይባላል። የተለምዶአዊ ምዘና ስርአት ድክመት ደግሞ ሌሎች አማራጭ የምዘና ስርአቶች እንዲመጡ በር ከፍቷል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ተከታታይ ምዘና ነው (Ur፤1996)።

## 2.12. የተከታታይ ምዘና ስልቶች ወይም ዘዴዎች

መምህራን ተማሪዎቻቸውን የሚመዝኑባቸው የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶች (ዘዴዎች) አሉ:: በምዘና ወቅት የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ተጠቅሞ ተማሪዎችን መመዘን የተማሪዎችን የተለያዩ ችሎታዎች ለማወቅና ስለተማሪዎች ሁኔታ ተገቢ መረጃ ለማግኘት እንደሚረዳ Brown and Knight (1994፣23) እንዲሁም NIED (1999፣5) ይገልፃሉ:: ለምሳሌ ፈተናዎች የሚመዝኑት ተማሪዎች በአንድ ርዕስ ላይ ያላቸውን ዕውቀት ሲሆን የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ ወይም የመፃፍ ችሎታ ለመመዘን የምንጠቀምባቸው የምዘና ስልቶች ደግሞ ፈተና ከመስጠት በእጅጉ ይለያሉ:: በመሆኑም የተለያዩ የምዘና ስልቶችን መጠቀም ተማሪዎች በየትኛው የቋንቋ ክሂል ጠንካራ እንደሆኑ በየትኛው ክሂል ደግሞ እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው ለማወቅ ይረዳል::

ከምዘና ስልቶች ጋር በተያያዘ ሁኔታ Jarolemik and Parker (1997፣36)፣ እንዲሁም NIED (1999፣15) የተከታታይ ምዘና ስልቶችን በሁለት ይከፍሏቸዋል:: እነዚህም የምዘና ዘዴዎች መደበኛ የሆኑ የተከታታይ ምዘና ስልቶች (Formal assessment techniques) እና መደበኛ ያልሆኑ የተከታታይ ምዘና ስልቶች (Informal assessment techniques) ናቸው:: በመሆኑም የቡድን ውይይት፣ ምልከታ፣ የባሕሪ መግለጫ መዝገቦች፣ የቃል ጥያቄዎች ወዘተ. መደበኛ ያልሆኑ የምዘና ስልቶች ሲሆኑ መደበኛ ወደ ሆኑት የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች በምንመጣበት ጊዜ ደግሞ ፈተናዎች፣ ሰነደ ትምህርት እና ፕሮጀክቶች ይገኙበታል::

አንዳንድ የምዘና ስልቶች ከሌላው የምዘና ስልት በተሻለ መልኩ የተወሰኑ ባሕሪያትን ለመለካት ተሽለው የሚገኙበት አጋጣሚ አለ:: ለምሳሌ ከፈተና ይልቅ ፕሮጀክቶችን በመጠቀም የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ በተሻለ ሁኔታ መመዘን እንደሚቻል Puhl (1997፣5) ይገልፃሉ::

USAID/ Basic Education Program (2006፣25)፣ የተከታታይ ምዘናዎችን በኢትዮጵያ ባሉ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመተግበር ባወጣው የመመሪያ ሰነድ ውስጥ ለተከታታይ ምዘና የምንጠቀምባቸውን የምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች እና ተግባራቸውን በሚከተለው መልክ አቅርቧቸዋል፤

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዘዴዎች → | - ቅድመ ፈተና<br>-የቡድን ውይይት | - ምልከታ<br>-የቃል ጥያቄ | -የቤት ስራ | - ሙከራ | - የግል እና የቡድን ፕሮጀክቶች | -የምዕራፍ ማጠቃለያ ፈተናዎች |
| ተግባር → | - ትምህርት ለማቀድ | -በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር-ማስተማር እንቅስቃሴ ከሁኔታዎች አንፃር ለማስተካከል | -የመማር-ማተማሩን ሂደት ለመቆጣጠር | -የመማር-ማስተማሩን ሂደት ለመቆጣጠር እና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት | -ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ምን ያህል በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ለማረጋገጥ | -ውጤት ለመስጠት |

ከላይ በቀረበው አመልካች ስዕላዊ መግለጫ አማካይነት የተመለከቱት የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች እዚህ ላይ የተጠቀሱበት ምክንያት በተከታታይ ምዘና ሂደት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለመመዘን ከምንጠቀምባቸው የምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች ጋር ከፍተኛ የሆነ ተዛምዶ ስላላቸው ነው:: ከዚህም በተጨማሪ በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎቻችን በምንመዝንበት ጊዜ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለብን አቅጣጫ ስለሚጠቁም ነው::

አብዛኛውን ጊዜ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎቻችን በተከታታይ ሁኔታ ለመመዘን የምንጠቀምባቸው የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች የሚከተሉት መሆናቸውን NIED (1999፣15-20)፣ Puhl (1997፣3-13)፣ Elington and Earl (1997፣4-15)እና Shaaban(2001፣19-25) ይገልፃሉ::

### 2.12.1 የቃል ጥያቄ

ይህን የተከታታይ ምዘና ስልት አንድ መምህር በየትኛውም የመማር-ማስተማር ጊዜ አዘውትሮ ሊጠቀምበት ይችላል:: ይህ ዓይነቱ ስልት ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደተገነዘቡት ለማወቅና ተማሪዎች የት ላይ ችግር እንዳለባቸው ለማወቅ ይጠቅማል::

አብዛኛውን ጊዜ አንድ መምህር የዚህ ዓይነቱን የምዘና ስልት መደበኛ ባልሆነ መንገድ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ከተማሪዎች ጋር ተራክቦ ለመፍጠርና ለመመዘን የሚጠቀምበት

ነው:: በክፍል ውስጥ የቃል ጥያቄን እንደ አንድ የምዘና ዘዴ የመጠቀም ዋና አላማ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን ትኩረት ወደ ትምህርቱ ለመሳብ እንደሆነ NIED (1999፣15) ይገልፃሉ::

### 2.12.2. ምልከታ

ምልከታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሩትንና የሚናገሩትን በጥሞና በዓይን በመከታተል የምንመዝንበት ዘዴ መሆኑን Brooks (2002፣5) ይገልፃሉ:: በምልከታ አማካይነት መረጃ ለማግኘት ከተፈለገ መምህራን የምልከታ ክሂል ያስፈልጋቸዋል:: ይህም የምልከታ ክሂል ምን መመልከት እንደሚፈልጉ ማወቅን፣ በጥሞና ማዳመጥን፣ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በሚያደርጓቸው ተራክቦዎች ላይ ማተኮርን፣ ጠቃሚ ነገሮችን በማስታወሻ መያዝን እና ደግሞ ደጋግሞ ማሰብን ይጠይቃል::

እንደ NIED (1999፣19) ገለፃ፣ ምልከታ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው:: ምልከታ የሚካሄደው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሲወያዩና የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲያከናውኑ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ አስተማሪው እየተዘዋወረ በመመልከት እንዲሰሩ የታዘዙትን ተግባራት በትክክል ማከናወናቸውንና በሂደትም የጋጠሟቸውን ችግሮች መጠየቅና መረዳት አለበት::

### 2.12.3. ቅድመ ፈተና

ለማስተማር በምናቅድበት ጊዜ ተማሪዎቻችን ስለምናስተምረው ርዕስ ነገር ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ትምህርቱን ማስተማር ከመጀመራችን በፊት ማወቅ መቻል እንዳለብን NIED (1999፣18) ይገልፃል:: በመሆኑም ተማሪዎች ስለርዕሱ ያላቸውን የቀደመ ግንዛቤ ለማወቅ ከተወሰነ ጊዜ ቀደም ብሎ ለተማሪዎች የቅድመ ግንዛቤ ፈተና መስጠት ያስፈልጋል:: ከቅድመ ግንዛቤ ፈተና የተገኘው ውጤት አስተማሪው ለወደፊት ለማስተማር የሚጠበቅበትን ትምህርት በአግባቡ እንዲያቅድና የተለያዩ የምዘና ተግባራትን በዕቅዱ ወስጥ እንዲያካትት ዕድሉን ይፈጥርለታል::

### 2.12.4. የቤት ሥራ

የቤት ሥራ ተማሪዎች የተማሩትን ነገር በሚገባ እንዲለማመዱ የሚያግዝ የምዘና ስልት ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የቤት ስራ አንድ አስተማሪ ተማሪዎች ምን ያህል ትምህርቱን እየተከታተሉ እንደሆነ የሚያረጋግጥበት ስልት ነው:: የቤት ስራ ከሂደታዊ የምዘና ስልቶች መካከል አንዱ ሲሆን ተማሪዎች የትኞቹን ርዕሶች ደግመው መማር እንዳባቸውና እንደሌለባቸው የእርምት ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የምዘና ስልት ነው::

### 2.12.5. ፈተና እና ሙከራ

ፈተና እና ሙከራ በቋንቋ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለመመዘን ከፍተኛ ሚና አላቸው:: በፈተና እና በሙከራ መካከል የተወሰነ ልዩነት እንዳለ Race et al. (2005፣82)እና Norris (2000፣275) ይገልፃሉ:: አንድ መምህር ፈተና ለመፈተን በሚያስብበት ጊዜ ለተማሪዎቹ አስቀድሞ ይነግራቸዋል:: ከዚህም በተጨማሪ የፈተና የትኩረት አቅጣጫ በተወሰኑ ይዘቶች ላይ ነው:: በሙከራ ጊዜ ግን መምህሩ ሙከራ ለተማሪዎች እንደሚሰጥ አይነግራቸውም:: ከዚህም በተጨማሪ ለተማሪዎች የሚሰጠው ሙከራ በንግግር ወይም በፅሁፍ መልክ ሊቀርብ ይችላል::

ከትምህርቱ አላማ ጋር ግንኙነት ያላቸውና በጥንቃቄ የተዘጋጁ የቋንቋ ፈተናዎችና ሙከራዎች በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ አዎንታዊ አመለካከት እንዲፈጠር ያደርጋሉ:: በተገቢው ሁኔታ የተዘጋጁ ፈተናዎችና ሙከራዎች የተማሪዎችን በርትቶ የማጥናት ስሜት ይቀሰቅሳሉ:: ከዚህም በተጨማሪ በጥንቃቄ የተዘጋጁ ፈተናዎቸ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ ያለባቸውን ችግር እንዲለዩና በየትኞቹ ርዕሶች ላይ በርትተው መሥራት እንደሚገባቸው አስፈላጊውን መረጃ እንደሚሰጡ Race et al.(2005፣82) እና Hedge (2000፣127) ይገልፃሉ::

በእያንዳንዱ ምዕራፍ ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡት ፈተናዎች ለመምህራንና ለተማሪዎች የሚሰጡት መረጃ በጣም ጠቃሚ መሆኑን NIED (1999፣20) ይገልፃል:: ነገር ግን ፈተናዎች ተማሪዎች የመንፈቁን ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ የሚሰጡ ከሆነ መምህሩ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ ማስተካከል ስለሚገባው ነገር የሚሰጡት መረጃ የዘገየ ሊሆን ይችላል:: በመሆኑም መምህሩ ፈጥኖ ለተማሪዎች ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ላይሰጥ ይችላል:: ከዚህ ሐሳብ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ Teshome (2001፣28) የSaleem (1989፣261) ስራዎችን በመጥቀስ

*"በመንፈቅ ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡት ፈተናዎች ተማሪዎች ማሻሻል የሚገባቸውን ነገሮች በመጠቆም በኩል የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እጅግ በጣም ያነሰ ነው:: ምክንያቱም ፈተናዎቹ የሚሰጡት በወሰነ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ ስለሆነ ነው" ይላሉ::*

ፈተናዎችና ሙከራዎች ተማሪዎች አንድ ምዕራፍ ከመጨረሳቸው በፊት የሚሰጡ ከሆነ ግን ለመምህራንና ለተማሪዎች ስለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያስተላልፉት መረጃ በጣም ጠቃሚ እና ሂደቱን የሚያግዝ ይሆናል:: በመሆኑም መምህራን ከፈተናዎችና ከሙከራዎች የተገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በየትኞቹ ርዕሶች ላይ ጥንካሬ እንዳሳዩ በየትኞቹ ርእሶች ላይ ደግሞ ድክመት እንዳሳዩ መለየት ይችላሉ:: መረጃዎቹን መሰረት በማድረግም ተማሪዎች ድክመት ያሳዩባቸውን ርዕሶች እንደገና ሊከልሱላቸው ይችላሉ:: በመሆኑም ፈተናዎችና ሙከራዎች በተከታታይ ምዘና ሂደት የመማር-ማስተማሩን ሂደት ለማገዝና ስለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ የተከታታይ ምዘና ስልቶች መሆናቸውን NIED (1999፣20) ይገልፃል::

### 2.12.6. ፕሮጀክት

ፕሮጀክት ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ምን ያህል በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ለማወቅ የሚካሄድ የምዘና ስልት መሆኑን NIED (1999፣20) ይገልፃል:: የፕሮጀክት ስራ በሚሰጥበት ጊዜ የእያንዳንዱ ተማሪ የፕሮጀክት ስራ ይታረምና ውጤት ይሰጠዋል፤ ውጤቱም ይመዘገባል:: በመሆኑም ፕሮጀክት በተከታታይ ምዘና ውስጥ አንድ ዘዴ ወይም ስልት ነው ማለት ይቻላል:: የፕሮጀክት ስራ ለተማሪዎች በሚሰጥበት ጊዜ በጥንቃቄ ማቀድንና ማሰብን ይጠይቃል::

በቡድንም ሆነ በግል የሚሰሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተማሪዎችን ንቁ እና ራሳቸውን ችለው አንድ ስራ እንዲሰሩ በማድረጉ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ (Bligh and Jaques 1980፣43):: በግልም ሆነ በቡድን የሚሰሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ትክክለኛው ጊዜ ተመድቦላቸው መከናወን እንደሚገባቸው Race et al. (2005፣89-92) ይገልፃሉ:: ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን አንድ ፕሮጀክት እንዲያከናውኑ ማድረጉ የተማሩትን ነገር ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉት ለማወቅ እና ሀሳባቸውን በግልፅ እንዲያንፀባርቁ ለማድረግ እንደሚረዳቸው NIED (1999፣20) ይገልፃሉ::

ምንም እንኳን የቡድን ፕሮጀክቶች (ስራዎች) ለተማሪዎች የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ ቢሆንም፤ የቡድን ፕሮጀክትን መሰረት በማድረግ ተማሪዎችን መመዘን ግን ያስቸግራል:: ምክንያቱም በቡድን ስራው ለተሳተፉት ለሁሉም ተማሪዎች አንድ አይነት ውጤት ልስጥ? ወይስ እያንዳንዱ ተማሪ በቡድን ስራ ወቅት ለነበረው ግላዊ ተሳትፎ ውጤት ልስጥ? የሚለውን ጥያቄ ለመወሰን መምህሩን ስለሚከብደው ነው:: በመሆኑም መምህሩ በቡድን ስራ ወቅት እያንዳንዱ ተማሪ የነበረውን ግላዊ ተሳትፎ ከግምት ውስጥ በማስገባት ውጤት ልስጥ የሚል ከሆነ አስቸጋሪና ፈታኝ ስራ እንደሚሆንበት Brown et al. (1997፣77) ይገልፃሉ::

ምንም እንኳ የቡድን ስራዎች ለማረም አስቸጋሪ ቢሆኑም፤ ለተማሪዎች የተለያዩ የቡድን ስራዎችን መስጠት ግን የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፤

- ተማሪዎች አንድን ርዕስ ነገር ወይም ፍሬ ነገር በራሳቸው አስሰው እንዲያገኙ ያበረታታቸዋል::
- የተማሪዎችን ተነሳስኦት ያበረታታል::
- ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ ችግሮች በራሳቸው እንዲፈቱ ያደርጋል::
- የተማሪዎችን የእርስበርስ ትብብር ከፍ ያደርጋል::

የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ለተማሪዎች መስጠት የራሱ የሆኑ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ሁሉ ደካማ ጎኖችም አሉት::

- የተለያዩ የቡድን እና የግል ፕሮጀክቶችን ለተማሪዎች ለመስጠትና ለማቀድ ብዙ ጊዜ ይወስዳል::
- ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን ያከናውኗቸውን ተግባራት አርሞ አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ይወስዳል።
- ተማሪዎች በመካከላቸው የሀሳብ መሰራረቅ እንዳይኖር ስለሚፈሩ እርስበርሳቸው እንዳይረዳዱና እንዳይተባበሩ ያደርጋል::

Brown et al. (1997፣78) የWelsh (1981)ን እና የRudd (1985) ስራዎችን በመጥቀስ እንዳመለከቱት ተማሪዎች ከግል እና ከቡድን ፕሮጀክቶች (ስራዎች) ጋር በተያያዘ መልኩ የሚከተሉት ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፤

- የጊዜ ችግር፣
- ያለመስማማት ችግር፣

- ከፕሮጀክቱ ስራ ጥሩ ማርክ ለማግኘት ብቻ እንጅ ለመማር ያለመፈለግ ችግር።

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቋቋም መምህራን የተማሪዎቻቸውን የቡድንና የግል ፕሮጀክቶች የሚቆጣጠሩበት የጽሑፍ መመሪያ (Written guideline) ያስፈልጋቸዋል። መምህራንም ይህንን መስፈርት አዘል መቆጣጠሪያ ለተማሪዎቻቸው ማሳወቅ እና መስፈርቶችን በማውጣት ሂደት ተማሪዎችን ማሳተፍ ያስፈልጋቸዋል (Brown and Knight 1994፣74)።

የቡድን እና የግል ስራዎችን ለመቆጣጠር መስፈርት የሚያስፈልገው መስፈርቱን መሰረት አድርጎ ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ፍትሐዊ (fair) ውጤት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን በቡድንና በግል ስራዎቹ ዙሪያ ግልፅ ዓላማ ለማስቀመጥና ተማሪዎቹ የትኛውን ክሂልና እውቀት መዳበር እንዳለባቸው ለማወቅና ለማቀድ ጭምር ነው። በመሆኑም መስፈርት አስፈላጊ ነገር ነው።

በአጠቃላይ ውጤታማ የቡድን እና የግል ስራ (ፕሮጀክት) በሚከተሉት ነገሮች ላይ ይመሰረታል፤

- ግልፅ የሆኑ ተግባራትን በመስጠት፣
- ግልፅ የሆኑ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት፣
- ፍትሐዊ (fair) የሆነ ውጤት በመስጠት፣
- ከትምህርቱ ዓለማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን በመቅረፅ።

በመሆኑም ውጤታማ የቡድን ስራ (ፕሮጀክት) ለማካሄድ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ቢሟሉ ተማሪዎች በሚሰሩት ስራ እርካታ ያገኛሉ።

### 2.12.7. የመምህር- ተማሪ ውይይት

የመማር-ማስተማሩን ስራ በተመለከተ በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄድ ውይይት አንድ የምዘና ዘዴ (ስልት) ነው። በተማሪዎችና በመምህራን መካከል የሚካሄድ ውይይት ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ለመምህሩ ጥሩ የሆነ አእምሮአዊ ምስል ከመስጠቱም በላይ በውይይቱ ጊዜ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው Shaaban (2001፣20) ይገልፃል።

በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሔድ ውይይትና ቃለ መጠይቅ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ያሳዩትን መሻሻል ኢመደበኛ በሆነ መልኩ የምንመዝንበት ስልት ነው፡፡ በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄድ ውይይት አንድ ተማሪ በትምህርቱ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነና ፍላጎቱ ምን እንደሆነ ለመመዘን ያስችላል::

## 2.12.8. ሰነደ ትምህርት

ሰነደ ትምህርት በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎችን ለመመዘን ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው:: ሰነደ ትምህርት ማለት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ያከናወኗቸው ስራዎች ስብስብ ወይም ክምችት ሲሆን ተማሪው በሚማረው የቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ምን ምን መሻሻሎችን እንዳሳየ ለመምህሩ አእምሮአዊ ስዕል የሚሰጥ የምዘና ስልት መሆኑን Puhl (1997፣9) ይገልፃሉ::

ምንም እንኳን ሰነደ ትምህርት በተከታታይ ምዘና ሂደት እንደ አንድ የምዘና ስልት መጠቀሙ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ በማዳበር በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ቢኖረውም፤ የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሉት ግን ሳይጠቀስ መታለፍ እንደሌለበት Elington እና Earl (1997፣8) ይገልፃሉ፡፡

የሰነደ ትምህርት ምዘና ጠንካራ ጎኖች፤

- ሰነደ ትምህርት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት እየሰሩ ያስቀመጧቸው የተለያዩ ስራዎች ክምችት በመሆኑ ተማሪዎች ያዳበሯቸውን ክሂሎች በተመለከተ በሰፊው መረጃ ይሰጣል::
- ሰነደ ትምህርት የተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት (Prior Knolwledge) ምን እንደነበርና አሁን ደግሞ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ ይጠቅማል::
- ሰነደ ትምህርት የተማሪዎችን ዕውቀትና ክሂል ምን እንደሆነ አጉልቶ ስለሚያንፀባርቅ ለአስተማሪው ጥሩ መረጃ ይሰጣል::
- ሰነደ ትምህርት ተማሪው ረዘም ላለ ጊዜ ያሳየውን ግለሰባዊ ዕድገት ስለሚያንፀባርቅ ከሌሎች የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ይልቅ ስለተማሪው ሁለንተናዊ ባህሪ አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል::

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

**የሰነደ ትምህርት ምዘና ደካማ ጎን፤**

- የእያንዳንዱን ተማሪ ሰነደ ትምህርት አንብቦ ለተማሪዎች ገንቢ አስተያየት ለመስጠት ጊዜ ይወስዳል::
- የሰነደ ትምህርት ስራዎች በውስጣቸው የተለያዩ ተግባራትን ስለሚይዙ እያንዳንዱን ተግባር መስፈርት አውጥቶ ለመመዘን ይከብዳል::

### 2.12.9. የራስ ምዘና

በምዘና ሂደት ውስጥ አንዱ ዘዴ የራስ ምዘና ነው:: የራስ ምዘና ማለት ተማሪዎች የራሳቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን በራሳቸው የሚገመግሙበት ስልት ነው:: ምዘና ሲባል ደግሞ ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት:: እንደ Puhl (1997፣10) ገለፃ ተማሪዎች በተወሰነ ትምህርት ላይ ትኩረት ሰጥተው ከሰሩ በኂላ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ራሳቸውን ይመዝናሉ:: ይህ ምዘናም ያሳዩትን መሻሻል እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል:: የራስ ምዘና ማለት ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚመዝኑበት ሂደት ነው:: እንደ Puhl ገለፃ ተማሪዎች የራሳቸውን የትምህርት ሂደት በራሳቸው ሲመዝኑ የሚችሉት አስፈላጊ ሁኔታዎች ከተሟሉላቸው ነው:: ከነዚህም አስፈላጊ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው እስከአሁን ደህና አድርጌ የሰራሁት ምንድን ነው? በሚቀጥለው ማሻሻል ያለብኝ ምንድን ነው? ጠንካራና ደካማ ጎኔ የት ላይ ነው? ብሎ ለመመዘን መስፈርቶች ያስፈልጓቸዋል::

Harris (1997፣10) የራስ ምዘና ተማሪዎች በራስ የመተማመን ችሎታቸው እንዲጎለብትና ግልፅነትን እንዲላበሱ ያደርጋል:: ከዚህም በተጨማሪ ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን ለይተው በማውጣት ለድክመቶቻቸው ማስተካከያ የሚሆን መንገድ እንዲቀይሱና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ የሚያስችሉ እርምጃዎች እንዲወስዱ ያስችላቸዋል:: ራስን መመዘን ተማሪዎች ለትምህርታቸው ከፍተኛ ሀላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋል:: በተጨማሪም በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ከማጎልበቱም በላይ ተማሪዎች ስለራሳቸው ትክክለኛ እና አስተማማኝ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: እንደ Puhl (1997፣7) ገለፃ፣ በተከታታይ ምዘና ወቅት የራስ ምዘናን መጠቀም ተማሪው የቋንቋ ችሎታውን የበለጠ እንዲያዳብርና ብስለት የተሞላበት የማሰብ ችሎታ (higher orders thinking skill) እንዲያጎለብት ያደርገዋል::

የራስ ምዘና ስልት በተማሪዎች በኩል ተቀባይነት እንዲያገኝ ጠቃሚነቱም የጎላ እንዲሆን መምህራን የራስ ምዘናን በአግባቡ ሊያዘጋጁትና ሊተገብሩት ይገባል:: በመሆኑም ስለ ራስ ምዘና ዓላማ፣ ጠቀሜታ እና መስፈርቶች ተማሪዎቻቸውን በአግባቡ ማሳወቅ አለባቸው:: ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የመመዘን ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማድረግ የራስ ምዘና በክፍል ውስጥ በሚካሄዱ ዕለታዊ የመማር-ማስተማር ክንውኖች መካተት አለበት::

### 2.12.10. የጓደኛ ለጓደኛ (የቢጤ) ምዘና

በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎችን ለመመዘን ከምንጠቀምባቸው የምዘና ስልቶች አንዱ የቢጤ (የጓደኛ ለጓደኛ) ምዘና ነው:: የቢጤ ምዘና የሚለውን ሰሎሞን (1987፣8) ሲገልፁት፣ ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር የሚያደርጉት የእርስ በርስ የመተራረም ዘዴ ነው ይሉታል::

በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸው (ከጓደኞቻቸው) ጋር በመሆን ሥራዎቻቸውን እርስ በርሳቸው የሚመዝኑበትና ጠቃሚ የሆኑ የማሻሻያ ሐሳቦችን ከጓደኞቻቸው የሚቀስሙበት የምዘና ስልት የቢጤ ምዘና እንደሚባል Puhl (1997፣4) ይገልፃሉ::

ከላይ ከተጠቀሱት ብያኔዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ የቢጤ ወይም የጓደኛ ለጓደኛ ምዘና ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚያካሂዱት የምዘና ስልት መሆኑን ነው:: በመሆኑም የተማሪዎችን የእርስ በርስ መስተጋብር ከፍ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

የቢጤ ምዘና ለተማሪዎች ስለሚሰጠው ጥቅም Puhl (1997፣7-8) እንዲሁም Wilson (2002፣217) የሚከተሉትን ነገሮች አቅርበዋል፤

- በቢጤ ምዘና ዓውድ ውስጥ ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የተለያዩ የምዘና መስፈርቶችን እንዲያወጡ ያስችላቸዋል::
- ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ምጋቢ ምላሽ እንዲሰጣጡ ያስችላቸዋል::
- ተማሪዎች ሐሳባቸውን በነፃነት እንዲያንፀበርቁ ያስችላቸዋል::
- ተማሪዎች እንዲነቃቁ ያደርጋቸዋል::
- ተማሪዎች ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ የማየትና አመዛዝኖ የማሰብ ችሎታን ያጎለብትላቸዋል::

- አስተማሪዎች የተማሪዎቻቸውን ሥራ በማረም የሚያጠፉትን ጊዜ ይቀንስላቸዋል::

ምንም እንኳን የቢ.ጤ ምዘና ከላይ የተጠቀሱት ጠቀሜታዎችና ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም የሚከተሉት ደካማ ጎኖች ደግሞ አሉት፣

- ተማሪዎች እርስበርስ የመተራረም ችሎታ ላይኖራቸው ይችላል::
- በጓደኛሞች መካከል በጣም የመቀራረብ ሁኔታ ስለሚኖር ተማሪዎች በትክክል የጓደኞቻቸውን ስራዎች ላይመዝኑ ይችላሉ::
- አንዳንድ ተማሪዎች ጓደኞቻቸው የሚሰጧቸውን አስተያየት አምነው ላይቀበሉት ይችላሉ::

ምንም እንኳን የቢ.ጤ ወይም የጓደኛ ለጓደኛ ምዘናን መጠቀሙ ከላይ የተገለጹት ደካማ ጎኖች ቢኖሩትም፣ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት የቢ.ጤ ምዘናን አዘውትረው መጠቀም አለባቸው:: ይህንን ለማድረግ የቢ.ጤ ምዘናን ዓላማና ጥቅም ለተማሪዎቻቸው ግልፅ ማድረግ እንዳለባቸው Puhl (1997፣8) ይገልፃሉ::

## 2.12.11. እየወጡ ማቅረብ

Shaaban (2001፣19) እንደሚገልጹት፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ ከምንጠቀምባቸው የምዘና ስልቶች መካከል አንዱ እየወጡ ማቅረብ ነው:: እንደ ምሁሩ ገለፃ ከቋንቋ ትምህርቱ ጋር በተያያዘ መልኩ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ እንዲያቀርቡ በማድረግ መመዘን የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት:: ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል::

- ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታና አጠቃቀም መመዘን ይችላሉ::
- ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን የሐሳብ አደረጃጀት መመዘን ይችላሉ::
- ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት መገንዘብ ይችላሉ::

በአጠቃላይ መምህራን በቋንቋ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን እየወጡ እዲያቀርቡ በማድረግ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ የሐሳብ አደረጃጀት ችሎታ ወዘተ. መመዘን ይችላሉ።

## 2.13. የቀደምት ተጓዳኝ ጥናቶች ቅኝት

ከተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት መገንዘብ እንደሚቻለው ተከታታይ ምዘና የቅርብ ጊዜ ታሪክ ያለው መሆኑን ነው። በሃገራችን የትምህርት ስርዓትም የተከታታይ ምዘና ጥናት ብዙም የተለመደ(የተፈተሸ) አይመስልም። ለዚህ ጥናት ያግዛሉ ብየ ካደረግሁት የተመሳሳይ የሃገርኛ ጥናቶች ቅኝት በተከታታይ ምዘና ላይ ያተኮሩ ሦስት ጥናቶች አጋጥመውኛል።

ከተመለከትኳቸው ሦስት ጥናቶች መካከል አንደኛው ጥናት የተጠናው በአልማዝ ሃይሉ ሲሆን፣ ጥናቱ የተጠናውም በ1999 ዓ.ም. ነው። ይህ ጥናት አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን፣ የጥናቱ ርእስም "አራተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ " የሚል ነው። በጥናቱ ግኝት መሰረትም ተጠኚ መምህራን ተከታታይ ምዘናን የሚተገብሩት ተከታታይ ፈተናዎችን በመስጠት እንደሆነ የጥናቱ አቅራቢ ለማረጋገጥ ችላለች።
ከዚህ ርእስ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ የተመለከትኩት ንብረት አስራደ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያቀረበውን ጥናት ነው። ጥናቱ የተጠናው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2005 ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማም የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መገምገም ነው። የጥናቱ አቅራቢ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የፅሑፍ መጠይቅና የቃል መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን ተጠቅሟል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየውም የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ትምህርቱን መማር-ማስተማር ሂደት ለማሻሻል ተከታታይ ምዘናን አይጠቀሙም።

ከዚህ ርእስ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ የተመለከትኩት ሦስተኛው ጥናት ባየ አሸብር በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያቀረበውን ጥናት ነው። ይህ ጥናት የተጠናው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2006 ሲሆን፣ የጥናቱ ትኩረትም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን አማራጭ የምዘና ስልቶችን ምን ያህል እንደሚጠቀሙባቸው መፈተሽ ነው። አጥኚው ጥናቱን ለማጥናት የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የፅሑፉ መጠይቅና ቃል መጠይቅ ሲሆኑ፣

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየውም የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን የሚጠቀሟቸው የምዘና ስልቶች በጣም አናሳ ናቸው።

ምንም እንኳን የእኔ ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም፤ በአጥኝው ዘንድ የሚከተሉትን ክፍተቶች ይሞላል የሚል እምነት አለ።

የአልማዝ ጥናት ትኩረት በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች የሚማሩ ተማሪዎችን ለመመዘን በሚያገለግሉና ቀላል የማስታወስ ችሎታን(lower ordered thinking skills) በሚያዳብሩ የምዘና ስልቶች ላይ ሲሆን፣ የእኔ ጥናት ትኩረት ግን በኮሌጅ በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ ላይ ነው። በመሆኑም ትኩረቱ ቀላል የማስታወስ ችሎታን በሚሹ ዘዴዎች ላይ ሳይሆን፤ ብስለት የተሞላበት የማሰብ ችሎታን(higher ordered thinking skills) ለማዳበር በሚያስችሉ የምዘና ስልቶች ላይ ነው።

የንብረት ጥናት ትኩረት በእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ላይ ነው። ጥናቱ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ ከግምት ውስጥ አላስገባም። ከዚህም በተጨማሪ መረጃ ለማሰባሰብ የተጠቀማቸው ዘዴዎች የፅሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው። የእኔ ጥናት ትኩረት ግን በአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ላይ ሆኖ፣ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ ጭምር ይፈትሻል። የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያወቹም ከፅሑፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ በተጨማሪ የሰነድ ፍተሻንና ምልከታን ይጨምራል።

የባየ የጥናት ትኩረት በአማራጭ የምዘና ስልቶች ላይ ነው። የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹም የፅሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው። የእኔ የጥናት ትኩረት ግን በተከታታይ ምዘና ስልቶች ላይ ሆኖ የሰነድ ፍተሻንና የምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን ይጨምራል። ከዚህም በተጨማሪ የእኔ ጥናት ኢ-መደበኛ እና መደበኛ የምዘና ስልቶችን ያካትታል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1. የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በትግራይ ውስጥ በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ላይ ነው፡፡

በዚህ ጥናት የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የተሻለ ዘዴ ይሆናል ተብሎ የተመረጠው መንገድ ገለፃን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጥናቱ የገለፃ ስልትን የተከተለበት ምክንያት የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ለመግለጽ የሚያስችል ዘዴ በመሆኑና ለጥናቱ አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን ማለትም በፅሁፍ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይት፣ በሰነድ ፍተሻና በምልከታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገለፃ ስልት ለመተንተን ምቹ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ ስራ ላይ የዋለው ዘዴ ገላጭ የምርምር ዘዴ ሲሆን የመረጃ ምንጮቹም መምህራን፣ ተማሪዎችና ሰነዶች ናቸው፡፡

## 3.2. የአሠልጣኝ መምህራንና የተማሪዎች አመራረጥ

አንድን ምርምር በማከናወን ሒደት ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የተጠኝዎችን የናሙና አመራረጥ ሁኔታ መወሰን ነው፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የተካሔደው በትግራይ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ላይ ነው፡፡ እነዚህም ኮሌጆች ዓድዋ፣ ዓብይ ዓዲና እና መቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ናቸው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ተተኳሪዎች በሦስቱም ኮሌጆች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራንና በተጠቀሱት ኮሌጆች የቋንቋ ትምህርት ዘርፍን መርጠው የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ለጥናቱ የትግራይ ክልል የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው በክልሉ ለረጅም ጊዜ በማስተማር ሙያ ላይ በመቆየቱ የተነሳ በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ችግር መኖሩን በማስተዋሉና መረጃ ለመሰብሰብም አመች ሆኖ በማግኘቱ ነው፡፡ ሦስቱም ኮሌጆች የተመረጡት ከወሳኝ ንሞና (Non Probablity Sampling) ዘዴዎች መካከል ጠቅላይ የንሞና ዘዴን (Comprehensive Sampling) መሰረት በማድረግ ሲሆን፣ ለዚህም ዋናው ምክንያት ሦስቱም ኮሌጆች

ለስልጠናው የሚጠቀሙባቸው ሞጁሎች አንድ ዓይነት በመሆናቸውና ተመሳሳይ ያሰለጣጠን ስርዓትን ስለሚከተሉ ነው፡፡

የመምህራን አመራረጥን በተመለከተ በሦስቱም ኮሌጆች የሚስተምሩ ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል፡፡ በየኮሌጁ ያሉትን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተመለከተ ሰንጠረዥ 1ን ይመለከቷል፡፡

ሰንጠረዥ 1

በሦስቱ ኮሌጆች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የኮሌጁ ስም | የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን ብዛት | የትምህርት ደረጃ | | | ፆታ | | ከፍተኛ ዲፕሎማ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዲፕሎማ | የመጀመሪያ ዲግሪ | ሁለተኛ ዲግሪ | ወንድ | ሴት | የተከተታሉ | በመከታተል ላይ የሚገኙ | ያልተከታተሉ |
| መቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ | 6 | - | 6 | - | 6 | - | 6 | - | - |
| ዓድዋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ | 4 | - | 3 | 1 | 4 | - | 4 | - | - |
| ዓብይዓዲ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ | 2 | - | 1 | 1 | 2 | - | 1 | 1 | - |
| ድምር | 12 | | 10 | 2 | 12 | - | 11 | 1 | - |

የተማሪዎችን አመራረጥ በተመለከተ ለዚህ ጥናት የተመረጡት ተማሪዎች በሦስቱም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በ10+3 መርሀ ግብር በመሰልጠን ላይ የሚገኙ የ1ኛ ዓመት የቋንቋ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች ናቸው፡፡ የ1ኛ ዓመት ተማሪዎች ብቻ የተመረጡበት ምክንያትም ምንም እንኳን የመቀሌና የዓቢይ ዓዲ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሶስተኛ

ዓመት ተማሪዎች ቢኖሯቸውም፤ የዓድዋ መምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ግን እጩ መምህራንን በሰርቲፊኬት ደረጃ ከማሠልጠን ወደ ዲፕሎማ ደረጃ ማሰልጠን የተሸጋገረው በያዝነው ዓመት ስለሆነ በዚህ ምክንያት በሶስቱም ኮሌጆች የአንደኛ ዓመት የ10+3 መርሃ ግብር የቋንቋ ተማሪዎች በነሲብ የዕጣ ንሞና ዘዴ (Simple Random Sampling) ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ ነሲብ የእጣ ናሙና ሥራ ላይ የዋለበት ምክንያት በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ለታሰቡት ተማሪዎች እኩል የመመረጥ እድል እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በየኮሌጆቹ ካሉት አጠቃላይ የአንደኛ ዓመት የቋንቋ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ሃምሳ ሃምሳ በመቶ ተመርጠው የጥናቱ ተሳታፊዎች ሊሆኑ ችለዋል፡፡

በሦስቱም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ለጥናቱ የተመረጡትን ተማሪዎች በተመለከተ ሰንጠረዥ 2ን ይመለከቷል፡፡

ሰንጠረዥ -2

በሦስቱም ኮሌጆች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአንደኛ ዓመት ተማሪዎችን አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የኮሌጁ ስም | የ1ኛ ዓመት የቋንቋ ተማሪዎች አጠቃላይ ብዛት | በዕጣ ናሙና የተመረጡ የ1ኛ ዓመት ተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| መቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ | 84 | 25 | 17 | 42 |
| ዓድዋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ | 120 | 34 | 26 | 60 |
| ዓብይዓዲ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ | 83 | 19 | 23 | 42 |
| ድምር | 287 | 78 | 66 | 144 |

ከሦስቱም ኮሌጆች የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ 144 ተማሪዎች የተመረጡ ሲሆን 9 ተማሪዎች (2 ከመቀሌ፣ 5 ከዓድዋ እና 2 ከዓብይ ዓዲ ) ከመጠይቁ ጥያቄዎች መካከል የተወሰኑትን ክፍት አድርገው በመመለሳቸው በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ በመሆኑም የተሳተፉት ተማሪዎች አጠቃላይ ድምር 135 ነው፡፡

### 3.3. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ከዚህ ጥናት ጋር በተያያዘ መልኩ ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅ፣ የቡድን ተኮር ውይይት፣ የሰነድ ፍተሻና ምልከታ ናቸው፡፡ ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ እና የሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለገሉ ሲሆን፣ የቡድን ተኮር ውይይት ግን ደጋፊ ነው፡፡ የአራቱም መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትኩረት በኢ- መደበኛ የምዘና ስልቶች (Informal Assessment Techniques) እና በመደበኛ የምዘና ስልቶች (Formal Assessment Techniques) አተገባበር ላይ ነው፡፡

#### 3.3.1. የጽሑፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ አስተማማኝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስራ ላይ ከዋሉት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አንዱ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ የቀረበው በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑት መምህራንና ተማሪዎች ነው፡፡ ለሁለቱም ወገኖች የተዘጋጁት የጽሑፍ መጠይቆች መጀመሪያ በጥናቱ አማካሪ ከዚያ ቀጥሎ በስርዓተ-ትምህርት የትምህርት ዘርፍ የማስትርስ ዲግሪ ባላቸው ባለሞያዎች የተገመገመ ሲሆን በተገኘው አስተያየት መሰረትም መጠይቆቹ ለመሰብሰብ የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ መሆናቸው ታምኖበታል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ለመምህራንና ለተማሪዎች የቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች አጠቃላይ ገፅታ ይቃኛል፡፡

##### 3.3.1.1. ለመምህራን የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ

ለመምህራን የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይ መረጃ፣ ዝግ ጥያቄዎችንና ልቅ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ዝግ ጥያቄዎችን የያዘው የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በአራት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ክፍል መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ዓላማና ተግባር ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል መረጃ ለማግኘት የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች አጠቃላይ ቁጥር 20 ሲሆን፣ እያንዳንዱ ጥያቄ የመስማማት መረጃን የሚጠቁሙ አምስት አምስት አማራጮች አሉት፡፡ እነዚህም አማራጮች 'በጣም እስማማለሁ'፣ 'እስማማለሁ'፣ 'መወሰን አልችልም'፣ 'አልስማማም' እና 'በጣም አልስማማም' የሚሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ጥያቄዎች መካከል የተወሰኑት ተሻሽለው የተወሰዱት Race et

al.(2005) "500 Tips on Assessment" ብለው ካሳተሙት መጻሕፍ ውስጥ ሲሆን፣ የተወሰኑት ደግሞ በክለሳ ድርሳኑ የተዳሰሱትን ዕንሰ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

የዝግ ጥያቄዎቹ ሁለተኛው ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሒደት የትኞቹን የተከታታይ ምዘና ስልቶች እንደሚጠቀሙ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች 'ሁልጊዜ'፣ 'አብዛኛውን ጊዜ'፣ 'አንዳንድ ጊዜ'፣ 'አልፎ አልፎ' እና 'በፍፁም' የሚሉ የድግግሞሽ ደረጃን የሚያሳዩ አማራጮችን የያዙ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ የተዘጋጁትም በክለሳ ድርሳን ውስጥ ስለምዘና ስልቶች የተነሱትን ሐሳቦች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

የዝግ ጥያቄዎቹ ሦስተኛው ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር እና የምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸውን በሚመለከት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ካሉት ጥያቄዎች መካከል የተወሰኑት 'አዎ' ወይም 'አይደለም' የሚሉ አማራጮችን የያዙ ሲሆኑ፣ የተወሰኑት ደግሞ ሌሎች አማራጮችን የያዙ ናቸው፡፡ የዝግ ጥያቄዎቹ አራተኛው ክፍል የተዘጋጀው ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ አሠልጣኝ መምህራን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች አጠቃላይ ቁጥር ዘጠኝ ሲሆን እነዚህም ጥያቄዎች 'ሁሉጊዜ'፣ 'አብዛኛውን ጊዜ'፣ 'አንዳንድ ጊዜ'፣ 'አልፎ አልፎ' እና 'በፍፁም' የሚሉ የድግግሞሽ ደረጃን የሚያሳዩ አማራጮችን የያዙ ናቸው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ዝግ ጥያቄዎች በተጨማሪ መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ወቅት ምን ምን ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸውና ምን ዓይነት መፍትሄ መፈለግ እንዳለበት ሐሳባቸውን በነፃ ለመግለጽ የሚያስችላቸው ልቅ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡

### 3.3.1.2. ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ

ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ አጠቃላይ መረጃ፣ ዝግ ጥያቄዎችንና ልቅ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ዝግ ጥያቄዎችን የያዘው የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል 20 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን የተዘጋጀውም ስለመምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ተማሪዎች ምን ዓይነት ግንዛቤ እንዳላቸው

ለማወቅ ነው፡፡ ይህ ክፍል የመስማማት ደረጃን የሚገልጹ አምስት አማራጮችን የያዘ ሲሆን እነሱም 'በጣም እስማማለሁ'፣ 'እስማማለሁ'፣ 'መወሰን አልችልም'፣ 'አልስማማም' እና 'በጣም አልስማማም' የሚሉ ናቸው፡፡

ከዝግ ጥያቄዎቹ ሁለተኛው ክፍል የተዘጋጀው ደግሞ በተማሪዎች ዕይታ መምህራን የትኞቹን የተከታታይ ምዘና ስልቶች ይጠቀማሉ የሚለውን ለማወቅ ነው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ዝግ ጥያቄዎች በተጨማሪ ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና አተገባበር ወቅት ያስተዋሏቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን እንደሆኑ ለመግለጽ የሚያስችላቸው ልቅ ጥያቄዎች ቀርበላቸዋል፡፡

### 3.3.2. ቡድን ተኮር ውይይት

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ አስተማማኝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይረዳ ዘንድ ስራ ላይ የዋለው ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ የቡድን ተኮር ውይይት ነው፡፡ የቡድን ተኮር ውይይቱ የተዘጋጀው ለሁለቱም ወገኖች ማለትም ለመምህራንና ለተማሪዎች ነው፡፡ ለመምህራን የተዘጋጁት የመወያያ ጥያቄዎች በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክሩ ሲሆኑ፣ ትኩረታቸውም መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውን በሚመለከት መረጃዎችን ማግኘት ላይ ነው፡፡

ለተማሪዎች ታስበው የተዘጋጁት የመወያያ ጥያቄዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ እንዲያጠናክሩ ታልመው የተዘጋጁ ሲሆኑ፣ ትኩረታቸውም መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ወቅት በሚያሳዩአቸው ደካማ ጎኖች ላይ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ ለመምህራን በተዘጋጀው የቡድን ተኮር ውይይት ላይ ሰባት መምህራን የተሳተፉ ሲሆን ለተማሪዎች በተዘጋጀው የቡድን ተኮር ውይይት ላይ ግን በእያንዳንዱ ኮሌጅ አምስት አምስት ተማሪዎች በእጣ ተመርጠው የውይይቱ ተሳታፊ ሁነዋል፡፡ ከሁለቱም ወገኖች ጋር የተደረገው ውይይት በመቅረፀ ድምጽ የተቀረፀ ሲሆን፣ ከእያንዳንዱ ኮሌጅ አሠልጣኝ መምህራንና ተማሪዎች ጋር የተካሄደው ውይይት ሰላሳ ሰላሳ ደቂቃ ያህል የጊዜ እርዝማኔ የወሰደ ነው፡፡

### 3.3.3. የሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት ውስጥ ከጽሁፍ መጠይቅና ከቡድን ተኮር ውይይት በተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሰነድ ፍተሻ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ መምህራን በየጊዜው የሚጠቀሙባቸውን ሰነዶች መፈተሽ ከጽሁፍ መጠይቅና ከቡድን ተኮር ውይይት የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነታቸውንና ተአማኒነታቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም መምህራን የተከታታይ ምዘና ተግባራትን በአግባቡ መዝግቦ ለመያዝ የሚጠቀሙባቸውን የውጤት መመዝገቢያ ቅፆች (Mark List)፣ የኮርስ ቢጋሮች ወይም እቅዶች (Course outline) እና ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ያከናውኗቸው የግል ስራዎች ተፈትሸዋል፡፡

### 3.3.4. ምልከታ

ለጥናቱ የሚሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ምልከታውን ለመከታተል ያመች ዘንድ 7 ነጥቦችን የያዘ የምልከታ ቅጽ የተዘጋጀ ሲሆን፣ የምልከታ ቅጹ ተሻሽሎ የተወሰደው Ministry of Education (2004) ለከፍተኛ ዲፕሎማ (Higher Diploma) ሥልጠና ባዘጋጀው ሞጁል ውስጥ ለክፍል ውስጥ ምልከታ (Lesson Observation) ከሚያገለግለው የመከታተያ ቅጽ ላይ ነው፡፡ ምልከታ የተካሄደባቸው መምህራን ከየኮሌጆቹ አንድ አንድ ሲሆኑ ይህ የተደረገበት ምክንያትም በየኮሌጁ ያሉትን ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን መመልከት ካለው የጊዜ እጥረት አንፃር ስለሚያስቸግር ነው፡፡ ምልከታ የተካሄደው በአንድ መምህር ላይ ሦስት ጊዜ ሲሆን በአጠቃላይ በሦስቱም ኮሌጆች 9 ምልከታዎች በሦስት አሰልጣኝ መምህራን ላይ ተካሔደዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል

ከዚህ ቀደም እንደተገለጸው ጥናቱን ለማጥናት ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሁፍ መጠይቅ፣ የቡድን ተኮር ውይይት፣ ምልከታና የሰነድ ፍተሻ ናቸው፡፡ አስተማማኝና ያልተበከለ መረጃ ለመሰብሰብ ሲባል አሰልጣኝ መምህራን የፅሁፍ መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት ምልከታው እንዲካሔድ ተደርጓል፡፡ ከዚያም የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት አስፈላጊው ገለፃ የተደረገላቸው ሲሆን ፣ በተለይ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገው አጥኚው ፊት ለፊት ሁኖ በሚቆጣጠርበት (ባለበት)

ሁኔታ ነው፡፡ ይህ የተደረገውም መጠይቁን በመሙላት ሂደት ተማሪዎች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠትና ሁሉንም የፅሁፍ መጠይቆች ሳይበታተኑ በአግባቡ ለመሰብሰብ እንዲያስችል ነው፡፡ የቡድን ተኮር ውይይቱ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር ከተካሔደ በኋላ ለጥናቱ አጋዥነት ያላቸው ሰነዶች ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ከየኮሌጆቹ የሬጅስትራር ፅህፈት ቤቶች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተኑ ዘዴ

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን አይነታዊና አህዛዊ የመረጃ አተናተን ዘዴዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ከዝግ ጥያቄዎች የተገኙት መረጃዎች አህዛዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም የተተነተኑ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን እና ከተከታታይ ምዘና የሚገኙ መረጃዎችን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው ለማዎቅ ከቀረቡት ጥያቄዎች የተገኙት መረጃዎች አማካይንና መደበኛ ልይይትን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በመሆኑም የመረጃዎቹ አማካይ ከሦስት በላይ ከሆነ የተጠቀሰውን የምዘና ስልት አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ያሳያል፡፡ በመረጃዎቹ መካከል ያለው መደበኛ ልይይት ከፍተኛ ከሆነ የአጠቃቀም ልዩነት መኖሩን ሲያሳይ፣ ዝቅተኛ መደበኛ ልይይት ደግሞ የጎላ የአጠቃቀም ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ እና ተማሪዎች ስለ መምህሮቻቸው የተከታታይ ምዘና አተገባበር ለቀረቡላቸው ዝግ ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ደግሞ በመቶኛ ተሰልተው ቀርበዋል፡፡

አሰልጣኝ መምህራንና ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቁ እና በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ለቀረቡላቸው ልቅ ጥያቄዎች የሰጧቸውን ምላሾች እንዲሁም ከምልከታና ሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ አይነታዊ አተናተን ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ሥር ከጽሑፍ መጠይቅ፣ ከቡድን-ተኮር ውይይት፣ ከምልከታና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡

## 4.1. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ የተገኘ መረጃ ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ በጽሑፍ መጠይቁ ላይ የሰጧቸው ምላሾች በመልክ በመልካቸው ተፈርጀው ተተንትነዋል፡፡

*ሠንጠረዥ -3*

*የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህን በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ*

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካል ነው፡፡ | 12 | 100 | - | - | - | - |

በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ 100% የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካል መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህን በተመለከተ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ ጥሩ መሆኑን ነው፡፡

ሠንጠረዥ -4

ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2 | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘቶች ለመወሰን ይረዳል፡፡ | 11 | 91.6 | 1 | 8.3 | - | - |
| 3 | ከተከታታይ ምዘና የተገኘው መረጃ የበለጠ የሚጠቅመው ለአስተማሪው ነው፡፡ | 8 | 66.6 | 2 | 16.6 | 2 | 16.6 |
| 4 | እንደ እኔ እምነት ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ለመርዳት ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ | 10 | 83.3 | 2 | 16.6 | - | - |

በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አሰልጣኝ መምህራን(91.6% የሚሆኑት) ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘት ለመወሰን እንደሚረዳ አመልክተዋል፡፡ ሦስት እጅ (66.6%) የሚሆኑት መምህራን ደግሞ በጥያቄ ቁጥር 3 እንደተመለከተው፣ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ የበለጠ የሚጠቅመው ለአስተማሪው ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ከጥያቄ ቁጥር 3 ጋር ተቃራኒ በሆነ መልኩ ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆኑት መምህራን ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ለመርዳት ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ በጣም አስፈላጊ መሆኑን በጥያቄ ቁጥር 4 ላይ እንደሚታየው በመስማማት ገልፀዋል፡፡

አሰልጣኝ መምህራን ከሰጧቸው እርስበርሳቸው ከሚቃረኑ ምላሾች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የሚሰጠውን ጥቅም በተመለከተ

አሰልጣኝ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ ያልተሟላ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ የሚጠቅመው ለመምህሩ ብቻ ሳይሆን ለተማሪዎችም ጭምር ስለሆነ ነው፡፡ ይህንን ሓሳብ ደግሞ Pasigna(2000)፣ AED/BESO II (2006) እና Puhl(1997) በአፅንኦት ይገልፃሉ፡፡

*ሠንጠረዥ -5*
*በተከታታይ ምዘና እቅድ ማውጣት የሚኖረውን ሚና በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ*

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | በተከታታይ ምዘና ሂደት እቅድ ማውጣት ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ | 12 | 100 | - | - | - | - |
| 6 | የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በተከታታይ ምዘና ዕቅድ ውስጥ ማካተት በራሱ በቂ ነው፡፡ | 9 | 75 | 2 | 16.6 | 1 | 8.3 |

በተራ ቁጥር 5 ለቀረበው የግንዛቤ ጥያቄ ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን ፣ በተከታታይ ምዘና ሂደት ዕቅድ ማውጣት ከፍተኛ ቦታ እንዳለው አመልከተዋል፤ ይሁን እንጅ በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው የግንዛቤ ጥያቄ፣ ሁለት ሦስተኛ(75%) የሚሆኑት መምህራን፣ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በተከታታይ ምዘና እቅድ ውስጥ ማካተት በራሱ በቂ እንደሆነ በመስማማት አመልክተዋል፡፡ ስለ ሁለቱ ጥያቄዎች በአሠልጣኝ መምህራን ከተሰጡት መልሶች መገንዘብ የሚቻለው መምህራን ስለተከታታይ ምዘና እቅድ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ እንደሌላቸው ነው፡፡ ምንም እንኳን በጥያቄ ቁጥር 5 ላይ ሁሉም መምህራን በተከታታይ ምዘና እቅድ ማውጣት ከፍተኛ ቦታ እንዳለው ቢገልጹም፣ በተራ ቁጥር 6 ላይ ግን አብዛኞቹ መምህራን የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በተከታታይ ምዘና እቅድ ውስጥ

ማካተት በራሱ በቂ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የተከታታይ ምዘና እቅድ ደግሞ የሚያካትተው የምዘናውን ዘዴ ብቻ ሳይሆን የምዘናውን ጊዜ፣ የምዘናውን ዓላማ ጭምር መሆኑን Elington and Earl (1997) እና NIED (1999) በአፅንኦት ይገልፃሉ፡፡

*ሠንጠረዥ -6*

*ተከታታይ ምዘና ከቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ ጋር ስላለው ግንኙነት በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ*

| ተ. ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 7 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን እንደየ ቋንቋ ችሎታቸው ለመለየት ያስችላል፡፡ | 8 | 66.6 | 3 | 25 | 1 | 8.3 |
| 8 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አዘውትረው መገኘታቸውን በተመለከተ በመምህራን የሚደረገው ቁጥጥር የተከታታይ ምዘና አንድ ክፍል ሁኖ ይሰማኛል፡፡ | 9 | 75 | 1 | 8.3 | 2 | 16.6 |

በተራ ቁጥር 7 እና 8 ላይ የቀረቡት የግንዛቤ ጥያቄዎች የሚያተኩሩት ተከታታይ ምዘና ከትምህርቱ ዓላማ ጋር ስላለው ግንኙነት ነው፡፡ በመሆኑም በተራ ቁጥር 7 ላይ በቀረበው ጥያቄ 66% የሚሆኑት መምህራን ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን እንደየቋንቋ ችሎታቸው ለመለየት ያስችላል በማለት ሲገልጹ፣ በተራ ቁጥር 8 ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ ሁለት ሦስተኛ(75%) የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አዘውትረው መገኘታቸውን በተመለከተ በመምህራን የሚደረገው ቁጥጥር የተከታታይ ምዘና ክፍል ነው በማለት መልሰዋል፡፡ የመምህራንን ግንዛቤ በሚደግፍ ሁኔታ፣ አሠልጣኝ መምህራን ባዘጋጁአቸው የኮርስ ቢጋሮች (Course outline) ላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በክፍል



... UNIVERSITY ... LIBRARY

ውስጥ አዘውትሮ መገኘት ራሱን የቻለ ማርክ ተመድቦለት ይታያል (አባሪ 5፣ 6 እና 7ን ይመለከቷል) ፡፡ ይሁን እንጂ Shepard (20008) እና AED/BESO II (2005፣29) እንደሚገልጹት፣ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ከሚማሩት ትምህርት ዓላማ ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፡፡ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያካሂዱት ቁጥጥር ደግሞ ከትምህርቱ ዓላማ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን የሚጠቀሙበት የምዘና ስልት(ዘዴ) ከሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆን አለበት፡፡

ሠንጠረዥ -7

በተከታታይ ምዘና ተማሪዎች የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 9 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ስራዎች ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ | 10 | 83.3 | 1 | 8.3 | 1 | 8.3 |
| 10 | በተከታታይ ምዘና ሒደት ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው መገምገም ይችላሉ፡፡ | 10 | 83.3 | 2 | 16.6 | - | - |
| 11 | ተከታታይ ምዘና መምህራን ብቸኛ ውሳኔ ሰጭ አካል እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ | 3 | 25 | 1 | 8.3 | 8 | 66.6 |
| 12 | በተከታታይ ምዘና ሒደት የመመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት ያላባቸው መምህራን ብቻ ናቸው፡፡ | 8 | 66.6 | 2 | 16.6 | 2 | 16.6 |

በተራ ቁጥር 9 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 83.3% የሚሆኑት መምህራን ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን በጓደኞቻቸው ሥራዎች ላይ ጥገኛ እንደሚያደርጋቸው ገልፀዋል፡፡ ከመምህራኑ ምላሽ በተቃራኒ መልኩ ደግሞ ምሁራን እንደሚገልጹት፣ ተከታታይ ምዘና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ተግባራትን ከጓደኞቻቸው ጋር ተባብረው እንዲሰሩ በማድረግ እና ግላዊ ተሳትፎአቸውን በማዳበር በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ Alausa(1999) እንደሚያመለክቱት፣ በአግባቡ የታቀደ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ኃላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል፡፡

በተራ ቁጥር 10 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 83.3% የሚሆኑት መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው ምገምገም እንደሚችሉ አመልክተዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በተራ ቁጥር 11 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 66.6% የሚሆኑት መምህራን "ተከታታይ ምዘና መምህራን ብቸኛ ውሳኔ ሰጪ አካል እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል" የሚለውን ሐሳብ እንደማይደግፉት ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው የግንዛቤ ጥያቄ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው (66.6%) አሰልጣኝ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት ያለባቸው መምህራን ብቻ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ ይህ ምላሽ ደግሞ በተራ ቁጥር 11 ለቀረበው ጥያቄ ከተሰጠው ምላሽ ጋር ይቃረናል፡፡ እንደ Pierce(2002 ፣19) እና Sheepard (2000፣ 7)እምነት ግን የተከታታይ ምዘና ዋነኛ መርህ ተማሪዎች የሚመዘኑበትን መስፈርት ለተማሪዎች ግልፅ ማድረጉ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም መስፈርት በማውጣት ሒደት ተማሪዎችን ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በተራ ቁጥር 11 የሰጡት ምላሽ ምሁራኑ ከሰጡት ሐሳብ ጋር የሚስማማ ሲሆን፤ በተራ ቁጥር 12 የሰጡት ምላሽ ግን ተቃራኒ ነው፡፡ ከነዚህ ሁለት የተለያዩ መልሶች መገንዘብ የሚቻለው የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት ሂደት ተማሪዎችና መምህራን የሚኖራቸውን የእርስ በርስ ሚና በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራኑ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ እንደሌላቸው ነው፡፡

ሠንጠረዥ -8

የተከታታይ ምዘናን ጥቅም በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 13 | ከተለምዶአዊው(በፅሁፍ መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነሳሳል፡፡ | 12 | 100 | - | - | - | - |
| 14 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተነቃቅተው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ | 10 | 83.3 | 1 | 8.3 | 1 | 8.3 |
| 15 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት ተማሪዎችን ጎበዝ ወይም ደካማ ናቸው ብሎ ለመፈረጅ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ | 1 | 8.3 | 3 | 25 | 8 | 66.6 |
| 16 | ከተለምዶአዊው (በጽሑፍ መልክ ብቻ ከሚቀርበው)የምዘና ሥርአት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በተሻለ ሁኔታ ለመለየት ያስችላል፡፡ | 9 | 75 | - | - | 3 | 25 |

በተራ ቁጥር 13 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ከተለምዷዊው የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነሳሳል በማለት መልሰዋል፡፡ ከሁለት ሦስተኛ በላይ (83.3%) የሚሆኑት መምህራን በተራ ቁጥር 14 ላይ እንዳመለከቱት



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ደግሞ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተነቃቅተው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ለሁለቱም ጥያቄዎች ከተሰጡት መልሶች መገንዘብ የሚቻለው፣ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በማነሳሳትና በማነቃቃት በኩል ስለሚሰጠው ጥቅም የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በቂ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው፡፡

66.6% የሚሆኑት መምህራን የተከታታይ ምዘና ትኩረት ተማሪዎችን ጎበዝ ወይም ደካማ ናቸው ብሎ ለመፈረጅ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን በተራ ቁጥር 16 ላይ እንዳረጋገጡት፣ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በተሻለ ሁኔታ ለመለየት ያስችላል፡፡ ከተሰጡት ምላሾች መገንዘብ የሚቻለው ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት በኩል ስለሚሰጠው ጥቅም መምህራን በቂ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው፡፡

ሠንጠረዥ -9

የተከታታይ ምዘና ዓላማን በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 17 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት በአብዛኛው በውጤት ላይ እንጂ በሒደት ላይ አይደለም፡፡ | - | - | - | - | 12 | 100 |

በተራ ቁጥር 17 ላይ ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን፣ የተከታታይ ምዘና ትኩረት በውጤት ላይ ሳይሆን በሂደት ላይ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው የተከታታይ ምዘና ዓላማን በተመለከተ ሁሉም መምህራን ትክክለኛ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው፡፡

ሠንጠረዥ - 10

ምጋቤ ምላሽን በተመለከተ የአሠልጣኝ መምህራን ግንዛቤ ምላሽ

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 18 | በተከታታይ ምዘና ሒደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት)ሲሰጥ ትክክለኛ እና ስህተት መልሶችን በመንገር ላይ ብቻ ማተኮር አለበት፡፡ | 2 | 16.6 | 1 | 8.3 | 9 | 75 |
| 19 | በተከታታይ ምዘና ሒደት ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) መሰጠት ያለበት በመምህራን እንጂ በተማሪዎች መሆን የለበትም፡፡ | 2 | 16.6 | - | - | 10 | 83.3 |
| 20 | በተከታታይ ምዘና ሒደት ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ማተኮር ያለበት ተማሪዎች የሚያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል ነው፡፡ | 6 | 50 | - | - | 6 | 50 |

በተራ ቁጥር 18 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት መምህራን በተከታታይ ምዘናሒደት ምጋቤ ምላሽ ሲሰጥ ትክክለኛ እና ስህተት መልሶችን ከመንገር በተጨማሪ ገንቢ አስተያየቶችን ጭምር ማካተት እንዳለበት ሲገልጹ፤ በተመሳሳይ መልኩ በተራ ቁጥር 19 ላይ በቀረበው ጥያቄ 83.3% የሚሆኑት መምህራን ምጋቤ ምላሽ በመስጠቱ ሒደት ከመምህራን በተጨማሪ ተማሪዎችም መሳተፍ እንዳለባቸው አመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጅ በተራ ቁጥር 20 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 50% የሚሆኑት መምህራን "በተከታታይ ምዘና ሂደት ምጋቤ ምላሽ ማተኮር ያለበት ተማሪዎች የሚያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል ነው" በሚለው ሐሳብ እንደሚስማሙ ሲገልጹ፣ የቀሩት 50% መምህራን ደግሞ በሐሳቡ እንደማይስማሙ አመልክተዋል፡፡



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ምጋቢ ምላሽን በተመለከተ ከተሰጡት ምላሾች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ መምህራን ስለምጋቢ ምላሽ አሰጣጥ የሰጡት ምላሽ እርስ በርሱ የሚቃረን መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በተራ ቁጥር 18 እና 19 ላይ መምህራን የሰጧቸው ምላሾች፣ መምህራን በምጋቢ ምላሽ አሰጣጥ ዙሪያ የተሟላ ግንዛቤ ያላቸው ቢያስመስልም፣ የምጋቢ ምላሽን ትኩረት በተመለከተ በተራ ቁጥር 20 የሰጡት የዋዠቀ ምላሽ ግን መምህራን ስለምጋቢ ምላሽ ያላቸው ግንዛቤ ያልተሟላ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ እንደ AED/BESO II(2005) እና Puhl (1997) እምነት ደግሞ የምጋቢ ምላሽ ዋነኛ ትኩረት ተማሪዎች በሒደት የሚያሳዩትን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመለየትና እገዛ ለመስጠት ነው፡፡

አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ ትንተና የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህ፣ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት በኩል ስለሚሰጠው ጥቅም፣ ስለተከታታይ ምዘና ዓላማ ጥሩ ግንዛቤ አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ስለሚሰጠው ጥቅም፣ ስለተከታታይ ምዘና እቅድ፣ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት ሂደት መምህራንና ተማሪዎች ስለሚኖራቸው የእርስ በርስ ሚና እና ስለ ምጋቢ ምላሽ አሰጣጥ ያላቸው ግንዛቤ የተሟላ አለመሆኑን ነው፡፡

## 4.2. የአሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች (ዘዴዎች) አጠቃቀም

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው ለማወቅ ከጽሑፍ መጠይቁና ከምልከታው የተገኙት መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡ ከምልከታ የተገኙት መረጃዎች በገለፃ መልክ የሚተነተኑ ሲሆን፣ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ ከአነፃዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች አንፃር (አማካይ እና መደበኛ ልይይት) ተተንትነው ይቀርባሉ፡፡ የተጠቀሱት አነፃዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ማለትም አማካይና መደበኛ ልይይት የተመረጡበት ምክንያትም በተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም ላይ ያለውን ልዩነት በጉልህ ስለሚያሳዩ ነው፡፡ ከፍተኛ መደበኛ ልይይት የሚያሳየው በተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም ላይ በአሠልጣኝ መምህራን ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን ሲሆን፣ ዝቅተኛ መደበኛ ልይይት

የሚያሳየው ደግሞ በተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም ላይ በአሠልጣኝ መምህራን የጎላ ያጠቃቀም ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡

### 4.2.1. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች ከአሠልጣኝ መምህራን ምላሽ አንፃር

ሰንጠረዥ 11 የሚያሳየው አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ተማሪዎችን ለመመዘን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእያንዳንዱ የምዘና ስልት የመረጃዎቹን አማካይ እና መደበኛ ልይይት ጭምር ያሳያል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ-11

የተከታታይ ምዘና ሥልቶችን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው

በአሠልጣኝ መምህራን የተሰጡ ምላሾችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የከታታይ ምዘና ስልቶች | የጊዜ ድግግሞሽን የሚያሳዩ አማራጮች | | | | | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ (5) | አብዛኛውን ጊዜ (4) | አንዳንድ ጊዜ (3) | አልፎ አልፎ (2) | በፍጹም (1) | | |
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | | |
| 1 | ቅድመ ፈተና | - | 5 | 2 | 2 | 3 | 2.75 | 1.28 |
| 2 | የቤት ስራ | 4 | 6 | 2 | - | - | 4.17 | 0.71 |
| 3 | ምልከታ | 3 | 5 | 2 | 1 | 1 | 3.67 | 1.23 |
| 4 | ሙከራ(ፈተና) | 1 | 2 | 6 | 3 | - | 3.10 | 0.90 |
| 5 | የግል ስራ(ፕሮጀክት) | 5 | 6 | 1 | - | - | 4.33 | 0.65 |
| 6 | የቡድን ስራ(ፕሮጀክት) | 2 | 8 | 2 | - | - | 4.00 | 0.60 |
| 7 | የመምህር ተማሪ ውይይት | - | 2 | 2 | 5 | 3 | 2.25 | 1.05 |
| 8 | ሰነደ-ትምህርት(ፖርትፎሊዮ) | - | - | 3 | 5 | 4 | 1.92 | 0.79 |
| 9 | ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | 2 | 9 | 1 | - | - | 4.08 | 0.51 |
| 10 | የራስ ምዘና | - | 2 | 1 | 7 | 2 | 2.25 | 0.96 |
| 11 | የጓደኛለጓደኛ (የበጤ)ምዘና | - | 2 | 4 | 5 | 1 | 2.58 | 0.90 |

ከሰንጠረዥ 11 መመልከት እንደሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ አስልጣኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን አዘውትረው የሚጠቀሟቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች የግል ስራ(አማካይ፤= 4.33) ፤ የቤት ስራ(አማካይ = 4.17)፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ (አማካይ = 4.08) እና የቡድን ስራ (አማካይ = 4.00) ናቸው፡፡ በተጠቀሱት የተከታታይ ምዘና ስልቶች የተመለከቱት መደበኛ ልይይቶችም (0.65) ፤ (0.71)፣ (0.51)፣ (0.60) በቅደም ተከተል ሲሆኑ የሚያሳዩትም በመረጃዎቹ(በተዘረዘሩት ስልቶች) መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም ከመረጃዎቹ በመነሳት፣ መምህራን ስለአራቱ የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም የሰጡት ምላሽ መስማማት የሚታይበት መሆኑን ወይም ደግሞ የጎላ የአጠቃቀም ልዩነት አለመኖሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከላይ ከተዘረዘሩት የተከታታይ ምዘና ስልቶች ቀጥሎ አሠልጣኝ መምህራን የሚጠቀሟቸው ምልከታ (አማካይ=3.67) እና ሙከራ (አማካይ=3.10) ሲሆኑ፣ የሁለቱ ስልቶች መደበኛ ልይይቶችም በቅደም ተከተል (1.23) እና (0.90) ናቸው፡፡ ከመደበኛ ልይይቶቹ መገንዘብ እንደሚቻለው፣ ምልከታን እንጠቀማለን ብለው የመለሱት መምህራን ከፍተኛ መደበኛ ልይይት ያሳዩ ሲሆን፣ ይህም ማለት ምልከታን በተመለከተ በመምህራን ዘንድ የአጠቃቀም ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡

በሠንጠረዡ መሰረት አሠልጣኝ መምህራኑ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች በቅደም ተከተል ቅድመ ፈተና (አማካይ=2.75)፣ የጓደኛ ለጓደኛ ምዘና (አማካይ=2.58)፣ የመምህር ተማሪ ውይይት (አማካይ=2.25)፣ የራስ ምዘና (አማካይ=2.25) ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙበት የምዘና ስልት ደግሞ ሰነደ ትምህርት (አማካይ=1.92)ነው፡፡

### *4.2.2. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና ሥልቶች ከተማሪዎች ምላሽ አንፃር*

ሠንጠረዥ 12 የሚያሳየው አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ተማሪዎችን ለመመዘን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእያንዳንዱ የምዘና ስልት የመረጃወቹን አማካይና መደበኛ ልይይት ጭምር ያሳያል፡፡

## ሠንጠረዥ -12

## መምህራን የተከታታይ ምዘና ሥልቶችን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው በተማሪዎች የተሰጡ ምላሾችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የከታታይ ምዘና ስልቶች | የጊዜ ድግግሞሽን የሚያሳዩ አማራጮች | | | | | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ (5) | አብዛኛውን ጊዜ (4) | አንዳንድ ጊዜ (3) | አልፎ አልፎ (2) | በፍጹም (1) | | |
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | | |
| 1 | ቅድመ ፈተና | 10 | 5 | 37 | 48 | 35 | 2.31 | 1.11 |
| 2 | የቤት ስራ | 19 | 62 | 28 | 23 | 3 | 3.53 | 1.00 |
| 3 | ምልከታ | 3 | 10 | 29 | 51 | 42 | 2.12 | 1.00 |
| 4 | ሙከራ(ፈተና) | 9 | 10 | 40 | 49 | 27 | 2.40 | 1.10 |
| 5 | የግል ስራ(ፕሮጀክት) | 47 | 52 | 11 | 14 | 11 | 3.81 | 1.24 |
| 6 | የቡድን ስራ(ፕሮጀክት) | 38 | 63 | 27 | 3 | 4 | 3.95 | 0.91 |
| 7 | የመምህር ተማሪ ውይይት | 17 | 21 | 24 | 57 | 16 | 2.75 | 1.22 |
| 8 | ሰነደ ትምህርት(ፖርትፎሊዮ) | 13 | 32 | 48 | 18 | 24 | 2.94 | 1.20 |
| 9 | ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | 33 | 42 | 37 | 23 | - | 3.63 | 1.03 |
| 10 | የራስ ምዘና | 13 | 26 | 21 | 54 | 21 | 2.67 | 1.22 |
| 11 | የጓደኛለጓደኛ (የበጤ)ምዘና | 8 | 16 | 25 | 48 | 38 | 2.3 | 1.20 |

ከሠንጠረዥ 12 መመልከት እንደሚቻለው፣ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሟቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች የቡድን ሥራ (አማካይ=3.95)፣ የግል ሥራ (አማካይ=3.81)፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ(አማካይ=3.63)እና የቤት ሥራ (አማካይ=3.53) መሆናቸውን የተማሪዎች ምላሽ ያሳያል፡፡

የተጠቀሱት የምዘና ስልቶች መደበኛ ልይይትም በቅደም ተከተል (0.91)፣ (1.24)፣ (1.03) እና(1.00) ሲሆኑ፣ የሚያሳዩትም ከግል ስራ በስተቀር በሌሎች የምዘና ስልቶች ያለው ልዩነት በጣም ጥቂት መሆኑን ነው፡፡ የግል ስራን ይጠቀማሉ ያሉት ተማሪዎች ግን የአጠቃቀም ልዩነት እንደሚታይባቸው ከቀረበው መደበኛ ልይይት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የተከታታይ ምዘና ስልቶች ቀጥሎ አሠልጣኝ መምህራን አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሟቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች ሰነደ ትምህርት (አማካይ=2.94)፣ የመምህር ተማሪ ውይይት (አማካይ=2.75)፣ የራስ ምዘና (አማካይ=2.67)፣ ሙከራ (አማካይ=2.4)፣ ቅድመ ፈተና (አማካይ=2.31)የጓደኛ ለጓደኛ ወይም የቢጤ ምዘና (አማካይ=2.3) እና ምልከታ (አማካይ=2.12) መሆናቸውን ተማሪዎች ገልፀዋል፡፡ የተዘረዘሩት የምዘና ስልቶች መደበኛ ልይይትም በቅደም ተከተል (1.20)፣ (1.22)፣ (1.22)፣ (1.10) (1.11)፣ (1.20) እና(1.00)ናቸው፡፡ መደበኛ ልይይቶቹም በመረጃዎቹ መካከል አነስተኛ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህም ማለት የተጠቀሱትን ስልቶች በተመለከተ የጎላ የአጠቃቀም ልዩነት አለመኖሩን የተማሪዎች ምላሽ ያሳያል ማለት ነው፡፡

### 4.2.3. የአሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸውን የምዘና ስልቶች አስመልክቶ መምህራን የሰጡት ምላሽ እና ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ልዩነት ትንተና

ከላይ ከቀረቡት ሁለት ሠንጠረዦች (ከሠንጠረዥ 11 እና 12) መገንዘብ እንደሚቻለው፣ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች የግል ሥራ፣ የቤት ሥራ፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብና የቡድን ሥራ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጅ በተማሪዎች ምላሽ መሰረት ደግሞ አሰልጣኝ መምህራኑ አዘውትረው የሚጠቀሟቸው ስልቶች በቅደም ተከተል፣ የቡድን ሥራ፣ የግል ሥራ፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ እና የቤት ሥራ ናቸው፡፡ ምንም

እንኳን ከአሠልጣኝ መምህራንና ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው ተማሪዎችን ለመመዘን መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ተመሳሳይነት ቢታይባቸውም፣ በአጠቃቀም ደረጃ ግን የተወሰነ ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በተማሪዎች ምላሽ መሰረት መምህራን በቀዳሚነት የሚጠቀሙት የቡድን ሥራን ነው፣ በማስከተልም የግል ሥራን ይጠቀማሉ፡፡ በአሠልጣኝ መምህራን ምላሽ መሰረት ደግሞ በቀዳሚነት የሚጠቀሙት ስልት የግል ሥራ ሲሆን ፣ በማስከተልም የቤት ስራን ይጠቀማሉ፡፡ በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ምላሽ ሦስተኛ ደረጃን ይዞ የሚገኘው የተከታታይ ምዘና ስልት ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ የሚለው ነው፡፡ በአሠልጣኝ መምህራን ምላሽ መሰረት የአራተኛ ደረጃን ይዞ የሚገኘው የቡድን ሥራ ሲሆን፣ በተማሪዎች ምላሽ መሰረት ደግሞ የአራተኛ ደረጃን ይዞ የሚገኘው ስልት የቤት ሥራ ነው፡፡

### 4.2.4. በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች

በሦስቱም መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ አንድ አንድ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ከተመረጡ በኋላ በመማር-ማስተማሩ ሂደት የትኞቹን የምዘና ሥልቶች እንደሚጠቀሙ ለማወቅ ሦስት ሦስት ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች ተካሂደዋል፡፡

በሦስቱም መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ይሰጥ የነበረው ኮርስ መሠረታዊ አማርኛ II የተባለው ኮርስ ነው፡፡ በምልከታው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየውም፣ ሁሉም አሠልጣኝ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት የትምህርቱን ዓላማዎች ለተማሪዎች አልተናገሩም፡፡ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ከጻፉ በኋላ በቀጥታ የሚያልፉት ወደ ትምህርቱ ነው፡፡ የተከታታይ ምዘና ዋነኛ ትኩረት ደግሞ የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች ግልፅ በማድረጉ ላይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ አሠልጣኝ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ተማሪዎች በዕለቱ እንዲማሯቸው ስለታቀዱት ርዕሶች ያላቸውን የቀደመ ግንዛቤ ለመፈተሽ ያደረጉት ሙከራ የለም፡፡ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በሂደት ለመመዘን የተጠቀሙባቸው ስልቶችም የቡድን ሥራ፣ የግል ሥራ (በክፍል ሥራ መልክ) እናእየወጡ ማቅረብ ናቸው፡፡

ነገር ግን የቤት ሥራ፣ የራስ ምዘና፣ የቢጤ ምዘና እና የመምህር ተማሪ ውይይት ሲተገበሩ አልተስተዋሉም፡፡

### 4.2.5. የተከታታይ ምዘና ሥልቶችን አስመልክቶ ከጽሑፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኙ ውጤቶች ማብራሪያ

የምዘና ስልቶችን አስመልክቶ ከፅሁፍ መጠይቅ እና ከምልከታ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ የሦስቱም መምህራን ትምህርት ክሊጆች የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የተጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች የቡድን ሥራ፣ የግል ሥራ፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ እና በተወሰነ መልኩ የቤት ሥራ ናቸው፡፡ መምህራን ከተጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች መገንዘብ የሚቻለው አሠልጣኝ መምህራን የተጠቀሙባቸው በመማር-ማስተማር ሂደት እና ከማስተማር በኋላ የሚካሄዱ የምዘና ተግባራትን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ መረጃዎቹ የሚያሳዩት መምህራን ከማስተማር በፊት የሚካሄዱ የምዘና ተግባራትን አለመጠቀማቸውን ነው፡፡ የቅድመ ፈተና የምዘና ስልቶችን አዘውትረው አለመጠቀማቸውና የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ተማሪዎች ስለ ርእሱ ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤ ለማወቅ የሚያስችሉ የምዘና ተግባራትን አለማከናወናቸው፣ ከማስተማር በፊት የሚካሄዱ የምዘና ተግባራትን በአግባቡ እንዳይተገበሩ አድርጓቸዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሐሳቦች በተጨማሪ፣ አሠልጣኝ መምህራን የሚጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች ማለትም የቡድን ሥራ፣ የግል ሥራ፣ እየወጡ ማቅረብና የቤት ሥራ አብዛኛውን ጊዜ የተማሪዎችን የመጻፍና የመናገር ችሎታ ለመመዘን የሚረዱ የምዘና ሥልቶች ናቸው፡፡ እነዚህን የምዘና ሥልቶች ብቻ በተደጋጋሚ ጊዜ መጠቀም ደግሞ መምህራን ተማሪዎቻቸው በቀሩት የቋንቋ ክሂሎች እና ንኡሳን ክሂሎች ስለሚያሳዩአቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች በቂ መረጃ እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡ Shaaban(2001) እንደሚገልጹት መምህራን በክፍል ውስጥ በዓይነት የተለያዩ የምዘና ስልቶችን የሚጠቀሙ ከሆነ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር ሰፊ እድል ያገኛሉ፤ በመሆኑም የሚማሩትን ቋንቋ ለተግባቦት የማዋል ብቃቱን ያዳብራሉ፡፡

## 4.3. የተከታታይ ምዘና አተገባበርን በተመለከተ ከአሠልጣኝ መምህራን የተገኘ ምላሽ

ከዚህ ቀጥሎ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው በጽሑፍ መጠይቆቹ የሰጧቸው ምላሾች ይተነተናሉ፡፡

ሠንጠረዥ-13

የተከታታይ ምዘና አተገባበርን በተመለከተ ለአሠልጣኝ መምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ? | 12 | 100 | - | - |
| 2 | በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎ" ከሆነ የተከታታይ ምዘናን በትምህርት ዕቅድዎ ውስጥ ታሳቢ በማድረግ ያካትታሉ? | 12 | 100 | - | - |
| 3 | በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎ" ከሆነ የሚከተሉትን ተግባራት በዕቅድዎ ውስጥ በግልፅ ያስቀምጣሉ? ሀ. የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ? | 5 | 41.6 | 7 | 58.3 |
| | ለ. የተከታታይ ምዘናውን ጊዜ? | 6 | 50 | 6 | 50 |
| | ሐ. የተከታታይ ምዘናውን ዘዴ? | 7 | 58.3 | 5 | 41.6 |
| 4 | የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የውጤት መከታተያ(የመመዝገቢያ) ቅጾችን ይጠቀማሉ? | 12 | 100 | - | - |
| 5 | በተራ ቁጥር 4 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎ" ከሆነ የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት ለመከታተል(ለመመዝገብ) የሚጠቀሙበትን ቅፅ የሚያገኙት ከየት ነው? | ኮሌጁ አዘጋጅቶ ይሰጠናል | | በዲፓርትመንት ደረጃ እናዘጋጃለን | |
| | | 12 | 100 | - | - |

ተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ስለሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባራት አስፈላጊውን መረጃ የሚሰጥ የምዘና ስርዓት ነው፡፡ ይህንን አስመልክተው Elington እና Earl (1997፡2) እንደሚያብራሩት፣ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ላይ የሚያሳዩትን መሻሻል ለማወቅ ሒደታዊና ተከታታይ በሆነ መልኩ የሚከናወን የምዘና አይነት ነው፡፡ በተጨማሪም Farrant (1980፡25) እንደሚገልፁት፣ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ የሚያሳዩትን አቅምና ብርታት እንዲሁም ደካማ ጎን ለማወቅ በየጊዜው የሚካሄድ የምዘና አይነት ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ Cullingford (1995፡75) የተከታታይ ምዘናን አስፈላጊነት አስመልክተው ሲገልፁ የሚከተለውን ይላሉ፤

> ማንኛውም የማስተማር ስራ ከምዘና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነገር ነው፡፡ በክፍል ውስጥ ገብቶ ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ለተማሪዎች ገለፃ ሰጥቶ መውጣት በጣም ቀላል ነገር ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ተማሪዎች የተማሩትን ይዘት ምን ያህል አውቀውታል? በሂደትስ ምን አይነት ችግር አጋጥሟቸዋል? ብሎ ተማሪዎችን በተከታታይ መልኩ መመዘኑ ነው፡፡

እስከ አሁን በተለያዩ ምሁራን አማካይነት ስለተከታታይ ምዘና ከተሰጡት ብያኔዎች መገንዘብና መረዳት እንደሚቻለው፣ ተከታታይ ምዘና ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር በተቀናጀ መልኩ የሚካሔድ የምዘና አይነት መሆኑንና የትኩረት አቅጣጫውም አንድ ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተማሪው ምን እንደተገነዘበና ምን ምን አይነት መሻሻሎችን እንዳሳየ በሂደት የሚመዘንበት የምዘና ስርዓት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተከታታይ ምዘና ዋና ትኩረት ተማሪዎች በሂደት የሚያሳዩአቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይቶ የማስተካከያ ሀሳቦችንና የእርምት ርምጃ መስጠት ነው፡፡

እንደ Mulu (2005)፣ ተከታታይ ምዘና ማለት ለተማሪዎች የተለያዩ ማጠቃለያ ፈተናዎችን በማዘጋጀት እንዲመልሱ ከማድረግ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መንፈስ ለተማሪዎች የተለያዩ የክፍል ውስጥ የምዘና ተግባራትን በመቅረፅ ተማሪዎችን ማሳተፍና የመማር- ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እንደ Livingston (2001፣29-30) አገላለጽ፣ ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች ከሚሰጠው ጥቅም ጎን ለጎን ለመምህራንም የሚሰጠው ጥቅም በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ መምህራን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ወይም ዘዴዎችን ተጠቅመው ተማሪዎቻቸውን በሚመዝኑበት ጊዜ ስለተማሪዎች ተነሳሽነት (Motivation)፣ ስለተማሪዎች ተሳትፎ (Active participation)፣ ስለተማሪዎች መሻሻል (Progress)፣ ስለተማሪዎች ባህሪ (behavior) ወዘተ. አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያገኙበታል፡፡ ይህም መረጃ ተማሪዎች በሒደት ስለሚያሳዩአቸው ባህሪያትና ችግሮች ፍንጭ ስለሚሰጥ አስተማሪው ለወደፊቱ ችግሮቹን ለይቶ አስፈላጊውን የማስተካከያ መንገድ እንዲቀይስ ያደርገዋል፡፡ ለዚህም ነው ስለተከታታይ ምዘና ምንነት ሲነሳ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው እውቀትና አመለካከት ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ Teshome (2001) የሚገልፁት፡፡

ተከታታይ ምዘና ለቋንቋ መምህራን የሚሰጠው ጥቅም በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የቋንቋ አስተማሪዎች የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን ወይም ስልቶችን ተጠቅመው ተማሪዎችን በሚመዝኑበት ጊዜ ከሚገኘው መረጃ በመነሳት ስለተማሪዎቻቸው የቋንቋ ችሎታ፣ ስለቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴው ጠንካራና ደካማ ጎን፣ ስለቋንቋ ስርዓተ ትምህርቱ ሁኔታ ተገቢ የሆነ ውሳኔ መስጠት ይችላሉ (Phul 1997፣3) እና (Shaaban 2001፣ 17) ፡፡

አማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ከሚሰጥባቸው ክልሎች ውስጥ አንዱ የትግራይ ክልል ነው፡፡ በትግራይ ክልል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርት ዓይነትነት የሚሰጥ ሲሆን፣ በክልሉ በሚገኙ የመምህራን ማስልጠኛ ኮሌጆች ውስጥም የቋንቋ ትምህርት ዘርፍን መርጠው ለሚማሩ ተማሪዎች በኮርስነት ይሰጣል፡፡

- ትምህርት ሚኒስቴር (2003) የኢትዮጵያን የትምህርት ስርዓት ለማሻሻል ባወጣው ፖሊሲ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ሁሉም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት የተከታታይ ምዘናዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው በግልፅ ያስገነዝባል፡፡ ተማሪዎች ከሚያገኙት ውጤት መካከልም 75% የሚሆነው ድርሻ ተከታታይ ምዘናን መሰረት ማድረግ እንደሚገባው ያብራራል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር የተነደፈውን የተከታታይ ምዘና ስልት

በዓድዋ፣ በዓቢ.ዓዲ እና በመቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስራ ላይ እያዋሉት ይገኛሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ትምህርት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ ያሉትን አሰልጣኝ መምህራን የሙያ ብቃት ለማሻሻል ባዘጋጀው የከፍተኛ ዲፕሎማ መርሀግብር ማሰልጠኛ ሞጁል ውስጥ ተከታታይ ምዘና ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ነገር ግን የዚህ ጥናት አቅራቢ በዓድዋ መምህራን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋን ሲያስተምር ሳለ በተለያዩ ጊዜያት ከተጠቀሱት ሌሎች ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን ጋር ተከታታይ ምዘናን በተመለከተ የልምድ ልውውጥ በሚያካሂድበት ጊዜና ጉዳዩን አስመልክቶ ኢመደበኛ ውይይት በሚያደርግበት ጊዜ፣ መምህራኑ ተከታታይ ምዘናን የሚተገብሩት የተለያዩ የቡድን ስራዎችንና ፈተናዎችን ብቻ እያከታተሉ በመስጠት ተማሪዎችን መመዘንና ለሰሩት ስራ ውጤት መስጠት እንደሆነ ሊገነዘብ ችሏል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ደግሞ አጥኚው ከዚህ ቀደም ስለተከታታይ ምዘና ከሚያውቀው ፅንስሃሳብ ጋር ትንሽ የሚቃረን ሁኖ አግኝቶታል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ የተጠቀሰውን አነሳሽ ምክንያት መሠረት በማድረግ በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

ጥናቱ ከላይ የተጠቀሰውን አነሳሽ ምክንያት መሰረት በማድረግ በዓድዋ፣ በዓብይ ዓዲና በመቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸውን ምን እንደሚመስል ይፈትሻል፡፡ ጥናቱ ይህንን ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች ይመልሳል፤

ሀ. በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ምንነትና ዓላማ የተሟላ ግንዛቤ አላቸውን?

ለ. በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሟቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች ምን ምን ናቸው?



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ሐ. በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች (ካሉ) ምንድን ናቸው?

መ. በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚማሩ የቋንቋ ተማሪዎች መምህራኖቻቸው የተከታታይ ምዘናን ሲተገብሩ ያስተዋሏቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?

ሠ. በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት በቂ እና ፈጣን የሆነ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎቻቸው ይሰጣሉን?

ረ. በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን መቼ አና እንዴት እንደሚተገብሩ በትምህርት ዕቅዳቸው ውስጥ ያካትታሉን?

ሸ. በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ተከታታይ ምዘናን እንዴት ይተገብሩታል?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፣

ሀ. በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ ለሆኑት የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው እስከ ምን ደረጃ እንደሆነ የሚያመለክት መረጃ ይሰጣል፡፡

ለ. እውነተኛ የተከታታይ ምዘና አተገባበርን እውን ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልትና አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበትና ተማሪዎቻቸውን እንዴት መመዘን እንዳለባቸው አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡

ሐ. ከዚህ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ጥናት ማካሔድ ለሚፈልጉ አጥኝዎች እንደ መነሻ እና እንደ ማጣቀሻ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

መ. የአማርኛ የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዓድዋ፣ በዓብይ ዓዲ እና በመቀሌ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ ላይ

ያተኩራል:: በመሆኑም በተጠቀሱት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል፣ በተከታታይ ምዘና ሂደት ምን ምን የመመዘኛ ስልቶችን እንደሚጠቀሙ እና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን ምን ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው ይዳስሳል:: ከዚህ በተጨማሪ የዚህ ጥናት ትኩረት መሰረታዊ አማርኛ የተባለውን ኮርስ በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ነው::

ጥናቱ ከላይ በተጠቀሱት በሶስቱም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ላይ የተካሄደው ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ አስተማሪዎች ለማካተትና ለመረጃው አስተማማኝነት ሲባል ነው:: ምንም እንኳን ይህ ጥናት በሶስቱም ኮሌጆች ላይ ቢያተኩርም፣ ንፅፅራዊ ጥናት ግን አይደለም:: በመሆኑም በተከታታይ ምዘና አተገባበር አንደኛው ኮሌጅ ከሌላው ኮሌጅ ጠንካራ ነው ወይስ ደካማ ነው? የሚሉ ዓላማም የለውም::

## 1.5. የቃላትና የሐረጋት ፍቺ

ሁልአቀፍ :- የተከታታይ ምዘና ባህሪ ሲሆን፣ ተከታታይ ምዘና ዕውቀትን፣ ክህሎትንና ዝንባሌን ያቅፋል ማለት ነው::

መደበኛ የምዘና ስልት:- የራሳቸው ጊዜ ተመድቦላቸው የሚከናወኑ የምዘና ስልቶች

መደበኛ ልይይት (Standard Deviation):- ከእያንዳንዱ ውጤት (መረጃ) ላይ አማካይ ውጤቱ ተቀንሶ ካሬ እየተደረገ ተደምሮ ለተሳታፊዎች (ለመረጃዎች) ብዛት ከተካፈለ በኋላ የተገኘውን ዋጋ ካሬ ዘር ውስጥ በማስገባት የሚገኝ ውጤት ሲሆን፣ የሚያሳየውም የተጠኚዎችን የውጤት መቀራረብና መራራቅ ነው::

ምጋቤ ምላሽ:- በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባራት በፅሁፍ ወይም በንግግር መልክ የሚሰጥ የእርምትና የማስተካከያ ግብረ ምላሽ (አስተያየት)

ምዘና:- ተማሪዎችን በሚመለከት ውሳኔ ለመስጠት እንዲረዳ መረጃ የሚሰበሰብበት ሒደት ነው:: ይህም ማለት ተማሪዎች ምን እንደሚያውቁ፣ ምን እንደተረዱና ምን መስራት እንደቻሉ ለይቶ ለመረዳት የሚያስችል ብልሀት ነው::

ሰነደ ትምህርት:- በተከታታይ ምዘና ሒደት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት እየሰሩ ያጠራቀሟቸው የተለያዩ ተግባራት ክምችት

ቅድመ ፈተና፡- ወደፊት ለማስተማር ስለምናቅደው ርዕስ ተማሪዎች ያላቸውን የቀደመ ግንዛቤ ለማወቅ የምንጠቀምበት የምዘና ስልት

ተለምዷዊ ምዘና፡-በፅሁፍ ፈተና ላይ ብቻ ያተኮረ የምዘና ስልት ሆኖ አብዛኛው ሚናው ተማሪው አልፏል ወይስ ወድቋል ብሎ ውሳኔ ለመስጠት ነው

ተላውጦዎች ፡- በተከታታይ ምዘናው አተገባበር ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

አማካይ፡- የተሰበሰቡት ጠቅላላ ነጥቦች ከተደመሩ በኋላ ለተሳታፊዎች ተካፍሎ የሚገኘው ውጤት

ኢመደበኛ የምዘና ስልቶች፡- በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሒደት የራሳቸው ጊዜ ሳይመደብላቸው የሚከናወኑ የምዘና ስልቶች

ግምገማ፡- የምዘና ውጤቶችን በመጠቀም ስለተማሪዎች የክንውን ጥራት ዳኝነት የሚሰጥበት ሒደት ነው፡፡

የማስተካከያ እገዛ፡- በተከታታይ ምዘና ሂደት በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ከሌሎች ፈጥነው የማይረዱ ተማሪዎችን በፍጥነት እንዲረዱት ለማድረግ የምናግዝበት መንገድ

የማጠናከሪያ እገዛ፡- አንድን ትምህርት በተሻለ ሁኔታ ከሌሎች ፈጥነው ለሚረዱ ተማሪዎች ችሎታቸውን የበለጠ እንዲያጎለብቱ ለማድረግ የሚሰጥ እገዛ

የራስ ምዘና፡- በምዘና ሒደት ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚመዝኑበት የምዘና ስልት

የቢጤ ምዘና፡- በምዘና ሒደት ተማሪዎች የጓደኞቻቸውን ስራዎች የሚመዝኑበትና እርስ በርስ ግብረ ምላሽ የሚያገኙበት የምዘና ስልት

ፕሮጀክት፡- ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ምን ያህል በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ለማወቅ በግል ወይም ባቡድን ራሳቸውን ችለው የሚያከናውኑት ተግባር

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1. የተከታታይ ምዘና ምንነት

ተከታታይ ምዘና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት እያገኘ የመጣ የምዘና ስርዓት ነው። ተከታታይ ምዘና የመማር- ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካልና ተማሪዎችን በሂደት የመመዘኛ ስልት ሲሆን ዓላማውም ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ ማገዝና የመማር- ማስተማሩን ሂደት ማሻሻል ነው።

ተከታታይ ምዘና ምንድን ነው? የሚለውን NIED (1999፣7) ሲገልፀው "መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የምዘና ስልቶች ተደጋጋሚ በሆነ ሁኔታ በሚተገበሩበት ጊዜ ተከታታይ ምዘና ይባላል" ይላል:: Ministry of Education, Youth and Culture of Jamica (2004፣2) "ተከታታይ ምዘና ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር በተዋሀደ መልኩ የሚካሄድ፣ የመማር- ማስተማሩን ስራ ለማሻሻልና ተማሪዎችን ለማገዝ ሂደታዊ በሆነ መልኩ የሚከናወን የምዘና ዓይነት ነው" በማለት ይገልፀዋል:: እንደ Cruzon (1990፣135) አባባል ደግሞ ተከታታይ ምዘና አጠቃላይነት ያለው ፅንስ ሐሳብ ነው:: ይህም አጠቃላይነት ያለው ፅንስ ሐሳብ የሚያመለክተው ስለተማሪዎች ችሎታ፣ እውቀት፣ አመለካከትና ክሂል ሆኖ እነዚህን ነገሮች ለማረጋገጥም የተለያዩ የምዘና ስልቶችን ይጠቀማል::

ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን አጠቃላይ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት፣ የትምህርት አቀባበልና አካሄድ በመመዘን ተማሪዎችን ለማገዝ እንዲሁም በተማሪዎች፣ በመምህራንና በትምህርት ቤቱ ላይ ጠቃሚ ውሳኔ ለመስጠት መረጃ የሚሰበሰብበት የምዘና ስርአት መሆኑን AED/ BESO II (2005፣3) ፣ AED/BESO (2006፣ 5) እና የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ (1997፣2) ይገልፃሉ::

ተከታታይ ምዘና ተከታታይ የተባለበት በሚከተሉት ምክንያቶች መሆኑን NIED (1999፣3) ይገልፃል፤

1. ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካል በመሆኑ:: ይህንን አስመልክቶ NIED "በፋብሪካ ውስጥ አንድ የጨርቅ አይነት በሚሸመንበት ጊዜ ጨርቁ ከዲዛይኑ

ጋር ከፍተኛ የሆነ ቅንብር እንዳለው ሁሉ፣ ተከታታይ ምዘና እና ማስተማር ከፍተኛ ቅንብር ያላቸው የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው" ይላል::

2. አንድ የትምህርት ዓይነት በክፍል ውስጥ በሚሰጥባቸው ጊዜያት ሁሉ በመከናወኑ (ማለትም ተከታታይ ምዘና አንድን ንዑስ ርዕስ፣ አንድን ርዕስ፣ ወይም ደግሞ አንድን ምዕራፍ ተከትሎ ሊከናወን በመቻሉ) ነው::

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት ብያኔዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ተከታታይ ምዘና ማለት በክፍል ውስጥ ተከታታይ በሆነ መልኩ የሚካሄድ፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያግዝ ተማሪዎች በሂደት እንዲሻሻሉ የሚያደርግ፣ ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የምዘና ስርአት መሆኑን ነው::

## 2.2. የተከታታይ ምዘና ባሕሪያት

ተከታታይ ምዘና የሚከተሉት መሰረታዊ ባህሪያት እንዳሉት Alausa (1999፣7)፣ እንዲሁም የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ (1997፣5) ይገልፃሉ:: ባህሪያቱም የሚከተሉት ናቸው፤

### 2.2.1. ተከታታይ ምዘና ስርአታዊ ነው (Systematic)

ይህ ማለት መምህራን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ስርአታዊ በሆነ መልኩ ምልከታ ማካሄድ፣ ነገሮችን መገምገምና የታዩትን ባሕሪያት በአግባቡ መመዝገብ ያስችላቸዋል::

ተከታታይ የትምህርት ምዘና በስርአት የሚማራ ሂደት ነው ሲባል ሊያስራ በሚችል ዕቅድ ላይ ይመሰረታል ማለት ነው:: በተከታታይ ምዘና ዕቅድ ማውጣት ከፍተኛ ቦታ አለው:: ምዘና በዘፈቀደ አይከናወንም:: እቅዱ ይዘጋጃል፣ በዕቅዱ መሰረት ይተገበራል:: ዕቅዱ በሚዘጋጅበት ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች ምዘናው የሚካሄድበት ጊዜ፣ የሚተኮርባቸው የትምህርት ክፍሎች እና ንዑሳን ክፍሎች፣ የሪኮርድ አያያዝ፣ ምዘናው የሚካሄድበት ተስማሚ ዘዴ ወዘተ. ናቸው:: እነዚህን መሰረት አድርጎ ዕቅዱ ይዘጋጃል::

### 2.2.2. ተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው (Cumulative)

በአንድ ተማሪ ላይ የተሟላና ተገቢውን የትምህርት ምስክርነትና ውሳኔ ለመስጠት በአንድ ጊዜ የሚሰጥ የፈተና ግምገማ በቂ አይሆንም:: ምክንያቱም ስለተማሪው ሁለንተናዊ የአእምሮ፣

የሙያ ክህሎትና አመለካከት ዕድገት በቂ መረጃ ስለማይሰጥ ነው:: በተከታታይ ምዘና አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተጠናቅረው መቅረብ አለባቸው:: ይህ ካልተደረገ ስለተማሪዎቹ የተሟላ መረጃ ተይዟል ለማለት አይቻልም::

ተከታታይ ምዘና ተደጋጋሚ የምዘና ውጤት ነው ሲባል ተከተታታይ ምዘና በባህሪው የተለያዩ የምዘና ስልቶችን ስለሚጠቀም ተማሪው በተለያዩ ጊዜያት የሚያሳያቸውን አጠቃላይ ባህሪያት አጠቃሎ የሚያሳይ ማለት ነው (Vale፣1995: በTeshome 2001፣28 እንደተጠቀሰው)::

2.2.3. **ተከታታይ ምዘና ሁልአቀፍ ነው** (Comprehensive)

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው በቂ ዕወቀት ቀስመው፣ ክህሎታቸውን አዳብረውና አመለካከታቸውን አስፍተው እንዲወጡ ይጠበቃል:: ተማሪዎች ሊኖሯቸው የሚገቧቸውን እነዚህን ባሕሪያት በትክክል ለመመዘን በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጡ ፈተናዎችና ሙከራዎች በቂ አይደሉም፣ በእርግጥ በፈተና ዕውቀትንና ክህሎትን መለካት ይቻል ይሆናል:: አመለካከትንና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ ወዘተ. ለመለካት ግን ያስቸግራል::

ተከታታይ ምዘና እንደ ተለምዶአዊው ፈተና በአእምሮአዊ ክህሎት (Cognitive skill) ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ ሁለቱንም ማለትም እውቀትንና ክህሎትን እንዲሁም አመለካከትን (ስሜትን፣ ዝንባሌንና እምነትን) ለመመዘን ያስችላል::

2.2.4. **ተከታታይ ምዘና አቅጣጫ ጠቋሚ ነው** (guidance oriented)

ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው ውጤት የተማሪዎችን የወደፊት አቅጣጫ ስለሚጠቁም በመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው:: በትምህርታቸው ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ለመርዳት የሚቻለው የተከታታይ ምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ ነው:: የተከታታይ ምዘና ዋነኛ አላማ ተማሪዎችን አልፈዋል ወይም ወድቀዋል ብሎ ውሳኔ ለመስጠት (ለመፍረድ) አይደለም፤ ተማሪዎችን ለመርዳት እንጂ:: ተማሪዎችን ለመርዳት ደግሞ በተከታታይ ምዘና አማካይነት ስለተማሪዎች በቂ መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል:: በሌላ አገላለፅ ተከታታይ ምዘና መምህራን የተማሪዎቻቸውን ችግሮች በሚገባ እንዲለዩና አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ የሚያግዝ ነው::

## 2.3. የተከታታይ ምዘና ዓላማ

የተከታታይ ምዘና ዋነኛ ዓላማ አንድ መምህር ስለሚያስተምራቸው ተማሪዎች ስውጥ፣ ጠንካራና ደካማ ጎን አስተማማኝ የሆነ መረጃ መስጠት ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ በመማር ማስተማሩ ሂደት ዙሪያ ስለሚያሳዩአቸው እንቅስቃሴዎች አስተማማኝ የሆነ መረጃ ይሰጣል:: ስለዚህም ከተከታታይ ምዘና የተገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ተማሪው በአንድ የትምህርት አይነት በሚያሳየው ጠንካራና ደካማ ጎን ዙሪያ አስተማሪው ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጥ ያስችለዋል::

እንደ Murphy (1996፣75) እና እንደ ICDR (2004፣5) እምነት ተከታታይ ምዘና አምስት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፣እነሱም የሚከተሉት ናቸው፤

- ተማሪው በሚማረው ትምህርት ዙሪያ የሚያሳየውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለመለየትና እገዛ ለማድረግ፤
- አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ በጊዜው ለመስጠት፤
- ስለተማሪው ሁኔታ አስፈላጊውን መረጃ ለሚመለከተው ክፍል ለማቅረብ፤
- ተማሪው በክፍል ውስጥ ሲማር ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥመውን ችግር ለመለየት፤
- ተማሪው በሚማረው የትምህርት ዓይነት አልፏል ወይስ ወድቋል? ብሎ ለመወሰን፤

McAfee and Leong (1997፣18) ደግሞ የተከታታይ ምዘና ዓላማን በተመለከተ የሚከተለውን ይላሉ፤

> *ተከታታይ ምዘና ትምህርትን ለማቀድ፣ ውሳኔ ለመስጠት፣ የክፍል ውስጥ የመማር - ማስተማር ሁኔታዎች ለተማሪዎች ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ እና ልዩ እገዛ የሚፈልጉ ተማሪዎች የትኞቹ እንደሆኑ ለመለየት በጣም አስፈላጊ መረጃ ይሰጣል::*

Wilkin (1991፣39) ደግሞ ተከታታይ ምዘና የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት ይላሉ፤

- ተማሪዎች ወደፊት እንዴት መማር እንዳለባቸው ለማገዝና ለማቀድ፤
- ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ኖሮአቸው ትምህርቱን እንዲከታተሉ ለማድረግ፤
- ተማሪዎች በሂደት በሚያሳዩት መሻሻል እና በሌሎች ነገሮች ላይ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት፤

ከላይ ከተጠቀሱት ነገሮች ጋር በተያያዘ መልኩ Ministry of Education (2003፣7)፣ AED/BESO II (2005፣10) መምህራን ተማሪዎቻቸውን እንዲመዝኑ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች የሚከተሉት እንደሆኑ ይገልፃል፤

- የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ለማሻሻል:: ይህም ማለት የምዘና ውጤቶች ተማሪው እንዴት እየተማረ እንዳለ እና አስተማሪው እንዴት እያስተማረ እንዳለ ምጋቤ ምላሽ ስለሚሰጡ ከምጋቤ ምላሽ የተገኘው መረጃ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ያግዛል፤
- ተማሪዎች የትኛውን ይዘት የበለጠ መማር እንዳለባቸው ለመወሰን፤
- የመማሪያ ወይም የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለማሻሻል፤
- ስለተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ ለወላጆች፣ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ለሚመለከታቸው ክፍሎች አስተማማኝ የሆነ መረጃ ለመስጠት፤
- ተማሪዎች በየትኞቹ የትምህርት ዓይነቶች ጠንካራ እንደሆኑ፣ በየትኞቹ የትምህርት ዓይነቶች ደግሞ ድክመት እንዳሳዩ ለመለየትና ድክመት ባሳዩበት ትምህርት ላይ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመቀየስ፤

በአጠቃላይ የተከታታይ ምዘና ዋነኛ ዓላማ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን ለማሻሻልና ተማሪዎችን በሚማሩት ትምህርት ዙሪያ ውጤታማ ማድረግ ነው::

## 2.4. ተከታታይ ምዘና ለምን ያስፈልጋል?

ተከታታይ ምዘና ለቋንቋ መምህራን በጣም አስፈላጊ መሆኑን Elington and Earl (1997፣3) እንዲሁም Puhl (1997፣2) ይገልፃሉ:: ተከታታይ ምዘናን በመጠቀም መምህራን ተማሪዎቻቸውን በሚመዝኑበት ጊዜ፣ የሚመዘኑት ተማሪዎች በአንድ ነገር ላይ ያላቸውን ዕውቀት ብቻ ሳይሆን ስሜታቸውንና ባሕሪያቸውንም ጭምር ነው::

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን አክለው እንደሚያብራሩት፣ የመማር-ማስተማሩን ሂደት እና የተቀመጡትን የትምህርት አላማዎች ግብ መምታት በተመለከተ ተከታታይ ምዘና መደበኛ እና አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል::

ተከታታይ ምዘና በፈተና አማካይነት ልንመዝናቸው ወይም ልንለካቸው የማንችላቸውን ነገሮች በሂደት እንድንመዝናቸው ያስችለናል:: ተከታታይ ምዘና ከሚሰጠው ጥቅም መካከል አንድ አስተማሪ ምጋቤ ምላሽና እርማት በመስጠት ላይ ያተኮረ የምዘና ሥርአት እንዲከተል ያደርገዋል (NIED, 1999)::

ተከታታይ ምዘና ዕውቀትን፣ ክህሎትንና አመለካከትን ለመመዘን ያስችላል:: ተማሪዎች ምን ያህል ዕውቀት፣ ክህሎትና ልምድ እንዳላቸው ለማረጋገጥ በቀለም ትምህርት ላይ የተመሠረተ ፈተና ሊያረጋግጥ ስለማይችል የተሻለ ዘዴ መጠቀም ይገባል:: ይህም ተከታታይ ምዘና ነው:: በመሆኑም ተከታታይ ምዘና የተማሪውን አጠቃላይ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለመመዘን ያስችላል (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ 1997)::

ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በአንድ ርዕስ ላይ የተጨበጠ ዕውቀት እስከሚይዙ ድረስ በተደጋጋሚ ይከናወናል:: ስለዚህም ተከታታይ ምዘና በትምህርት ሂደት ተማሪዎችን ለማበረታታትና ደረጃ በደረጃ ለማገዝ የሚያስችል ዘዴ ነው:: ተከታታይ ምዘና መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር በየጊዜው ግንኙነት እንዲያደርጉ ስለሚያስገድድ የመምህራንና የተማሪዎችን ግንኙነት ያጠናክራል::

Puhl (1997፣2) አክለው እንደሚገልጹት፣ በአንድ በተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ ፈተና የተማሪዎችን አጠቃላይ ዕውቀትና የክህሎት ሁኔታ (ሥዕል) አያሳይም:: ፈተና አብዛኛውን ጊዜ በአእምሮአዊ ክህሎት (cognitive skill) ላይ በማተኮር ለተማሪዎች አመለካከት (ስሜት፣ ዝንባሌ፣ እምነት) እና ክህሎት ዝቅተኛ ቦታ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ፈተናን ብቻ በትምህርት ቤት ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ተማሪዎች በሽምደዳ ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋል:: ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት ለተማሪዎቻችን የምንሰጣቸወ ፈተናዎች የሚያተኩሩት በተወሰኑ ይዘቶች ላይ ስለሚሆን ጥልቀት አይኖራቸውም:: ምዘና ደግሞ ሰፋ ማለት አለበት:: የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመመዘን ደግሞ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን መጠቀም አለብን:: ተከታታይ ምዘና ደግሞ መምህራን የተለያዩ የምዘና ስልቶችን (ዘዴዎችን) እንዲጠቀሙ ስለሚያበረታታ በጣም አስፈላጊ ነው::

ተከታታይ ምዘና ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመሻሻል ትልቅ እገዛ ያደርጋል:: Puhl (1997፣3) የChappelle እና Douglas (1993)



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ስራዎችን በመጥቀስ ተከታታይ ምዘናን በክፍል ውስጥ መጠቀም በፈተና እና በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ ተግባራት መካከል የሚያጋጥመውን ያለመጣጣም ክፍተት በእጅጉ እንደሚቀርፈውና በፈተና ሳቢያ ሊመጣ የሚችለውን ጭንቀትና ግርታ በእጅጉ እንደሚቀንሰው ይገልፃሉ:: ከላይ ከተጠቀሰው ሐሳብ በተጨማሪ ተከታታይ ምዘናን መጠቀም የተማሪዎችን ሁለተኛ ቋንቋ ለማሳደግ ከፍተኛ የሆነ እገዛ አለው:: ከላይ የተጠቀሱት ምሁር አክለው እንደሚገልጹት በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ የተለያዩ ፀባዮችን የሚያንፀባርቁ ናቸው:: ለምሳሌ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በማህበራዊ ዳራቸው፣ አፍ በፈቱበት ቋንቋ፣ በባህላቸው፣ በመጡበት አካባቢ፣ በፍላጎታቸው ወዘተ. መለያየት የተነሳ የተለያዩ ግለሰባዊ ልዩነቶችን ያሳያሉ:: ተከታታይ ምዘናን በዚህ አይነቱ የተማሪዎች ግለሰባዊ ልዩነት በእጅጉ በሚንፀባረቅበት ክፍል ውስጥ መጠቀም ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ የምዘና አማራጮችን እንዲያገኙ እድሉን ይፈጥርላቸዋል::

በአጠቃላይ ተከታታይ ምዘና እንዲኖር ከሚያስፈልጉት ነገሮች መካከል ተከታታይ ምዘና ሁለንተናዊ ባህሪያትን መመዘን ስለሚያስችል፣ በፈተና አማካይነት ልንለካቸው የማንችላቸውን ነገሮች እንድንለካ ስለሚያስችለን፣ የተለያዩ የምዘና ስልቶችን እንድንጠቀም ስለሚያስችለን፣ መምህራን የተለያዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን እንዲጠቀሙና የተማሪዎችን ሁለተኛ ቋንቋ ችሎታ ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ እንዲያዳብሩ ስለሚያበረታታ ነው::

## 2.5. በተከታታይ ምዘና እና በተለምዶአዊው ምዘና መካከል የሚስተዋሉ ጉልህ ልዩነቶች

በተከታታይ ምዘና እና በተለምዶአዊው ምዘና መካከል የሚከተሉት ጉልህ ልዩነቶች እንደሚስተዋሉ Elington and Earl (1997፣2) ይገልፃሉ::

ተለምዶአዊው ምዘና በባሕሪው ውጤታዊ ሲሆን፣ ተማሪዎችን በመመዘን የሚገኘው መረጃ የሚያያዘው ከውጤት ጋር ነው:: በመሆኑም አብዛኛው ሚናው ተማሪው አልፏል ወይስ ወድቋል? ብሎ ውሳኔ ለመስጠት ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች የተማሩትን ነገር እንዲያጠኑ እና እንዲያስታውሱ የሚገፋፋ ነው:: ተለምዶአዊው ምዘና ከተጠቀሱት ባህሪያት በተጨማሪ የሚከተሉት መለያ ባሕሪያት አሉት፣

- ምጋቤ ምላሽ አይሰጥም፤
- አብዛኛውን ጊዜ በፅሁፍ የምዘና ተግባራት ላይ ያተኩራል፤
- የትኩረት አቅጣጫው በተወሰኑ የፈተና ናሙናዎች ላይ ስለሆነ ጠባብና ጥልቀት የሌለው ነው፤

ተከታታይ ምዘና ደግሞ በተቃራኒው በባሕሪው ሂደታዊ ሲሆን፣ ተማሪዎችን በመመዘን የሚገኘው መረጃ የሚጠቅመው ተማሪውን በሂደት እንዲሻሻል ለማድረግ ነው:: በመሆኑም ትኩረቱ የመማር-ማስተማሩን ሂደት በመሻሻል ላይ ነው:: ተከታታይ ምዘና ከተጠቀሱት ባሕሪያት በተጨማሪ የሚከተሉት መለያ ባሕሪያት አሉት፤

- ተማሪዎች የተለያዩ ምጋቤ ምላሾችን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲሰጣጡ ያደርጋል፤
- በዓይነት የተለያዩ የምዘና ተግባራትን ያካትታል፤ በመሆኑም ጥልቀት አለው
- የሚያተኩረው በፅሁፍ ተግባራት ላይ ብቻ አይደለም፤

## 2.6. የተከታታይ ምዘና የሂደት ደረጃዎች

AED/BESO II (2006፣18) ፣ NIED (1999፣17) እንዲሁም ዳንኤል ዘውዴ (1999፣7) ተከታታይ ምዘና በሦስት ደረጃዎች ተከፋፍሎ ሊካሄድ እንደሚችል ይገልፃሉ:: እነዚህም ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ከማስተማር በፊት (Before Instruction)

   በዚህ ደረጃ ተከታታይ ምዘና የሚደረግበት ዋና አላማ

   ሀ. ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት ምዕራፍ፣ ዋና ርዕስ ወይም ንዑስ ርዕሶች ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤና ልምድ በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ፤

   ለ. ተማሪዎች ስለሚማሩት ይዘት የተዛባ (የተሳሳተ) ፅንሰሀሳብ ካላቸው መረጃ ለመሰብሰብ፤

   ሐ. በመጨረሻም የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ይመጥናሉ የሚባሉ ተግባራትንና መልመጃዎችን ባካተተ መልኩ ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ወዘተ ናቸው::

2. በማስተማር-መማር ሂደት

   በዚህ ደረጃ ተከታታይ ምዘና የሚተገበርበት ዋነኛ አላማ

ሀ. ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ምን ያህል እየተከታተሉ ናቸው? ምን ያህል እየተረዱ ናቸው? ከተማሩት ውስጥ ምን ያህሉን ተገንዝበዋል? ምን ዓይነት ችግር አጋጥሞአቸዋል? ወዘተ. በሚሉና በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ፣

ለ. በደንብ እየተከታተሉ ያሉትን ለማበረታታት፣

ሐ. የመማር ችግር ያጋጠማቸውን እንደ ችግራቸው መጠን የተለያዩ ድጋፎችንና እገዛዎችን ለመስጠት፣

መ. በማስተማር ሂደቱ ላይ መሻሻል በሚገባቸው ነጥቦች ዙሪያ ማስተካከያ ለማድረግ (ለምሳሌ ከትምህርት ዕቅዱ መሻሻል ጀምሮ እስከ ድጋሚ የማስተማር ሁኔታ ሊያጠቃልል ይችላል)፣

3. ከማስተማር በኋላ

በዚህ ደረጃ ተከታታይ ምዘና የሚካሄድበት ዋነኛ ዓላማ

ሀ. በየምዕራፉ የተካተቱትን የትምህርት አላማዎች መሠረት ባደረገ መልኩ ተማሪዎች ምን ያህል የባሕሪ ለውጥ አምጥተዋል? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ፣

ለ. በተሰበሰበው መረጃ መሰረት አንድ ተማሪ አልፏል ወይስ ከሚጠበቀው በታች አምጥቷል? ብሎ ለመወሰንና ውጤት ለመስጠት እንዲሁም ከተፈለገው በታች ያመጡትን ተማሪዎች በድጋሚ ለማዘጋጀት ይውላል::

## 2.7. የተከታታይ ምዘና መሠረታዊ መርሆዎች

ምሁራን እንደሚገልፁት ተከታታይ ምዘና ስርዓታዊ ነው:: በመሆኑም በመርህ ይመራል:: የተከታታይ ምዘና መርሆዎች የሚባሉትም የሚከተሉት ናቸው፤

1. እንደ Ministry of Education, Youth and Culture of Jamica (2004) ገለፃ፣ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑና መምህራንም የተለያዩ የመመዘኛ ናሙና ስራዎችን እንዲጠቀሙ የሚያስችል መሆን አለበት:: ምክንያቱም የተከታታይ ምዘና ዋነኛ ዓላማ ተማሪዎችን ማገዝና በሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መለየት ስለሆነ፣ ችግሮቹን ከተለያየ አቅጣጫ ለመረዳትና ለመለየት የተለያዩ ናሙና መመዘኛ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ማድረጉ አንዱ መሰረታዊ ነገር ነው::

2. ተከታታይ ምዘና መምህራን አስፈላጊ ምጋቤ ምላሾችን ለተማሪዎች በወቅቱ እንዲሰጡ የሚያስችል መሆን አለበት:: ምጋቤ ምላሹ የሚጠቅመው ለተማሪው ብቻ ሳይሆን ለመምህሩም ጭምር ነው:: ከተከታታይ ምዘና የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ አስተማሪው ለወደፊቱ ትምህርቱን ሲያስተምር ምን ዓይነት አቅጣጫ መቀየስ እንዳለበት ይረዳዋል:: (Ministry of Education, Youth and Culture of Jamica, 2004)

3. እንደ NIED (1999:14) ገለፃ፣ ተከታታይ ምዘና መምህራን የተለያዩ የምዘና ስልቶችን እንዲጠቀሙ የሚያስችል መሆን አለበት:: በተከታታይ ምዘና ሂደት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በሚመዝኑበት ጊዜ ተማሪዎችን ለማገዝና የመማር ማስተማሩን ሂደት የተቃና ለማድረግ የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶችን የመጠቀሙ ሌላው ፋይዳ ደግሞ መምህራን ስለተማሪዎቻቸው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል::

4. ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ የሚያግዝ መሆን አለበት (NIED 1999)::

5. ተከታታይ ምዘና ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ስነ ዘዴን የሚያጎለብት መሆን አለበት:: የተከታታይ ምዘና ዋነኛ ሚና የመማር ማስተማሩን ሂደት ማሻሻል ነው:: በዚህ ሚናውም እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ እንዲያገኝ ያግዘዋል:: ምጋቤ ምላሽ የመስጠቱ ሂደት ደግሞ አንዱ ተማሪ ከሌላኛው ተማሪ እንዲሁም ተማሪዎች ከመምህሩ ጋር የእርስ በርስ መስተጋብር እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ይህም ለተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ በር ይከፍታል:: ይህን በተመለከተ Richards (2004) በድረ ገፅ ያሰራጨት መረጃ በተከታታይ ምዘና አማካይነት ብዙ የተማሪ ቁጥር ባላቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታል::

6. ተከታታይ ምዘና ወቅታዊ መሆን አለበት:: ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩን ሂደት መሰረት አድርጎ በወቅቱ የሚካሄድ መሆን አለበት:: በትምህርት ፕሮግራሙ ማለቂያ ላይ የሚካሄድ ምዘና አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ በመስጠት በኩል የሚያበረክተው ፋይዳ አናሳ ነው (Race et al. 2005፣7)::

7. ተከታታይ ምዘና ግልፅ መስፈርቶችን የያዘ እና እነዚህም መስፈርቶች በተማሪዎች የሚታወቁ መሆን አለባቸው:: Pierce (2002፣9) እና Sheepard (2000:7)

እንደሚገልጹት የተከታታይ ምዘና ዋነኛ መርህ ተማሪዎች የሚመዘኑበትን መስፈርት ለተማሪዎች ግልፅ ማድረጉ ላይ ነው:: ተማሪዎች የሚመዘኑበትን መስፈርት አስተማሪው በግልፅ ማስቀመጥና ለተማሪዎቸ በግልፅ መንገር መቻል አለበት:: መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከመመዘናቸው በፊትም ሆነ በሚመዝኑበት ጊዜ ለተማሪዎች የመመዘኛ መስፈርቶችን አስቀድመው ማሳወቅ አለባቸው::

8. እንደ NIED (1999) ገለፃ፣ ተከታታይ ምዘና በመማር ማስተማሩ ሂደት አይቀሬ አካል ነው:: ተከታታይ ምዘና መተግበር ያለበት የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካል ተደርጎ እንጅ እንደ ተጨማሪ ስራ ተደርጎ አይደለም:: ስለሆነም መደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሊተገበር ይችላል::
9. ተከታታይ ምዘና ከትምህርቱ (ከስርዓተ ትምህርቱ) አላማ ጋር ግንኙነት ያለው መሆን አለበት (Shepard 2000፣8) ፣(AED/ BESO II 2005፣27):: መምህራን በሚያካሂዱት ምዘና እና በትምህርቱ አላማዎች መካከል ያለው ግንኙነት ደካማ ከሆነ የምዘናው ተግባር የመማር ማስተማሩን ሂደት በማሻሻል በኩል የሚኖረው አስተዋፅኦ በጣም ደካማ ይሆናል:: በመሆኑም የቋንቋ መምህራን የሚጠቀሙበት የምዘና ስልት ከሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት አላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆን አለበት::

## 2.8. የተከታታይ ምዘና ጥቅም እና ደካማ ጎኖች

ተከታታይ ምዘና የራሱ የሆነ ጥቅምና ደካማ ጎን አለው:: ተከታታይ ምዘና ጥቅም የሚሰጠው ለመምህሩ ብቻ ሳይሆን ለተማሪዎችም ጭምር ነው:: ከዚህ በመቀጠል ለመምህራንና ለተማሪዎች ምን ዓይነት ጥቅም እንደሚሰጥ እናያለን::

### 2.8.1. ተከታታይ ምዘና ለመምህራን የሚሰጠው ጥቅም

የቋንቋ መምህራን ሚና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቋንቋውን ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው:: ተማሪዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተማር ደግሞ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ነገር ግን ይህ በራሱ በቂ አይደለም:: የተማሪዎችን የዕለት ተዕለት ለውጥ ለማወቅ ተማሪዎች ተከታታይ በሆነ መልኩ ሊመዘኑ ይገባል (Puhl 1997፣5)፣ (Elington and Earl 1997፣3):: እንደ ምሁራኑ ገለፃ ተከታታይ ምዘናን በክፍል ውስጥ መጠቀም ለመምህሩ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፤

- የትኞቹ ተማሪዎች በሚማሩት ርዕስ ዙሪያ የተሻለ እየሰሩ እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል::
- የመማር-ማስተማሩን ሂደት ውጤታማነት ለማወቅና ተማሪዎችን ለማገዝ ይረዳዋል::
- የትኛው ርዕስ ለተማሪዎች አስቸጋሪ እንደሆነና ተማሪዎች ደግመው መማር እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው ለመወሰን ይረዳዋል::
- መምህራን መርሃ ትምህርቱን በበለጠ ሁኔታ እንዲሸፍኑት ያደርጋል::
- የቋንቋ ክሂሎችን በሚገባ ለመመዘን ያችላል።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ተከታታይ ምዘና ለቋንቋ መምህራን የትኞቹ ተማሪዎች በትምህርታቸው መሻሻል እያሳዩ እንደሆነና የትኞቹ ተማሪዎች ደግሞ ችግር እንዳለባቸው በመለየት በኩል ከፍተኛ ዕድል ይሰጣል:: የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግም መምህሩ በክፍል ውስጥ ሲያስተምር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለይቶ እገዛ እንዲያደርግላቸው ይረዳዋል::

ከላይ ከተገለጸው ጥቅም በተጨማሪ ከተከታታይ ምዘና የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ የትኛው ርዕስ ለተማሪዎች አስቸጋሪ እንደሆነ ማወቅ ይቻላል:: ከዚህ መረጃ በመነሳት አስተማሪው ተማሪዎችን የሚያግዝበትን ተግባር እንዲቀይስ ያስችለዋል::

2.8.2. ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች የሚሰጠው ጥቅም

ከዚህ በፊት እንደተገለፀው ተከታታይ ምዘና የሚካሄዱ ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን ችግር ለመለየትና በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው:: ይህ የተከታታይ ምዘና ተግባር ደግሞ በተለያየ መልኩ ይገለፃል:: ለምሳሌ ያህል ተማሪዎች በተከታታይ መልኩ በሚመዘኑበት ጊዜ ከመምህራንና ከቢጤዎቻቸው ተደጋጋሚ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ያገኛሉ:: ይህም ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች የራሳቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዲለዩ፣ እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያርሙ ወይም ደግሞ በትምህርቱ ዙሪያ ውጤታማ ሊያደርጓቸው የሚችሉ አማራጭ ዘዴዎችን እንዲቀይሱ ያደርጋቸዋል:: ከዚህም በተጨማሪ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች የተለያዩ እገዛዎችን ከመምህሮቻቸው ወይም ከቢጤዎቻቸው እንዲያገኙ ያስችላቸዋል:: እንደ Pasigna (2000፣3) እና AED/BESO II (2006፣42) እምነት ደግሞ የተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች የሚሰጣቸው ጥቅሞች በሁለት ተከፍለው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፤ የማስተካከያ እና የማጠናከሪያ እገዛዎች ተብለው::

2.8.2.1 የማስተካከያ እገዛ (Remediation)

Pasigna (2000፣5) "የማስተካከያ እገዛ" የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ምንነት ሲያብራሩ "በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ከሌሎች ፈጥነው የማይረዱ ተማሪዎችን በፍጥነት እንዲረዱት ለማድረግ የምናግዝበት መንገድ የማስተካከያ እገዛ ይባላል" ይላሉ:: የቋንቋ መምህራን ተማሪዎች ያሉባቸው ችግሮች የትኞቹ እንደሆኑ ከፈተሹ እና ከለዩ በኋላ ችግር ለተስተዋለባቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን የማስተካከያ እገዛ በመስጠት ሊረዷቸው ይችላሉ:: ይህን እገዛ መስጠት ለተማሪዎች አንድን ዕውቀት ወይም ክሂል የበለጠ እንዲገነዘቡት እድሉን ይፈጥርላቸዋል::

2.8.2.2. የማጠናከሪያ እገዛ (Enrichment Activities)

በክፍል ውስጥ የሚማሩትን ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ለማድረግ ከሚያስፈልጓቸው እገዛዎች መካከል የማጠናከሪያ እገዛ አንዱ ነው:: የማጠናከሪያ እገዛ አንድን ትምህርት ከሌሎች ፈጥነው ለሚረዱ ተማሪዎች ችሎታቸውን የበለጠ እንዲያገለብቱ ለማድረግ የሚሰጥ እገዛ ነው። አዝጋሚ ተማሪዎች በተለያዩ የማስተካካያ እገዛዎች በሚረዱበት ጊዜ ፈጣኖቹ ሌላ በጣም ፋይዳ ያለው ነገር መስራት እንደሚገባቸው በትምህርት ልማት አካዳሚ የመሰረታዊ ትምህርት ስልታዊ ግብ (1997፣ 38) ይገልፃል። አብዛኛውን ጊዜ የማጠናከሪያ ተግባራት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲማሩ የቀሰሙትን ዕውቀትና ክህሎት በበለጠ መልኩ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል:: እነዚህም የማጠናከሪያ ተግባራት በተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች ይቀርቡላቸዋል::

በአጠቃላይ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በትምህርታቸው እንዲነቃቁ ለማድረግ፣ በየጊዜው ያሳዩትን መሻሻሎች እንዲገነዘቡ ለማድረግ፣ ያለባቸውን ችግር እንዲለዩ ለማድረግ ወዘተ. ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ መገንዘብ ይቻላል::

2.8.3. የተከታታይ ምዘና ደካማ ጎኖች

Almayehu (2004፣5)፣ Elington and Earl (1997፣5) እና Nitko (2005፣47) እንደሚገልጹት ምንም እንኳን ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን በመመዘን በኩል ከፊተና ይልቅ ተመራጭነት ቢኖረውም የተወሰኑ ደካማ ጎኖች አሉት::

UNIVERSITY ... ABABA UNIVERSITY

መምህራን ተከታታይ ምዘናን በመጠቀም ተማሪዎቻቸውን በሚመዝኑበት ጊዜ፣ ተማሪዎች መምህራን ሁል ጊዜ የሚፈፅሙትን ስህተተ የሚከታተሉ ይመስላቸዋል:: ይህ ደግሞ በተማሪዎች የዕለት ተዕለት የትምህርት እንቅስቃሴ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው:: ከዚህም በተጨማሪ ተከታታይ ምዘና በአግባቡ ካልታቀደና በስራ ላይ ካልዋለ በስተቀር በተማሪዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል:: ይህንን በተመለከተ Elington and Earl (1997፣4) የሚከተለውን ይላሉ፤

> *ተከታታይ ምዘና በጥንቃቄ ካልታቀደ አስተማሪዎች ድንገተኛ የሆኑ ስራዎችን ለተማሪዎቻቸው እየሰጡ ከሚገባው በላይ ሊመዝኗቸውና ሊያስጨንቃቸው ይችላሉ:: ይህ ደግሞ በአስተማሪውና በተማሪዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ሊያሻክረው ይችላል::*

የተከታታይ ምዘናን ውጤታማነት ለመጨመር ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ መልኩ ሊከሰቱ የሚችሉትን ደካማ ጎኖች መቀነስ ያስፈልጋል:: Elington እና Earl (1997፣7) እንደሚያመለክቱት የቋንቋ መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ተገቢው ዕውቀትና ክሂል ሊኖራቸው ይገባል:: ከዚህም በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቋቋም መምህራን የተደራጀ የተከታታይ ምዘና ዕቅድ ያስፈልጋቸዋል::

### 2.9. በተከታታይ ምዘና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

በተከታታይ ምዘና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች አሉ:: እነዚህ ተላውጦዎች የተከታታይ ምዘናውን አተገባበር አዎንታዊ ወይም አሉታዊ በሆነ መልኩ ተፅዕኖ ያሳድሩበታል::

#### 2.9.1. ተማሪዎች በምዘና ላይ ያላቸው ግንዛቤና ልምድ

የተከታታይ ምዘና ዓላማዎች ግባቸውን በአግባቡ እንዲመቱ ወይም እንዳይመቱ ከሚያደርጓቸው ተላውጦዎች መካከል አንዱ ተማሪዎች ስለምዘና ያላቸው አመለካከት ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች በምዘና ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ማወቁ በምዘና ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ተረድቶ አስፈላጊውን እልባት ለመስጠት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ Crossman (2004፣42) ይገልፃሉ::

ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች መካከል በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚሰጡ ዕብረቃዎች፣ ምዘናው ለተደጋጋሚ ጊዜ መካሄዱ፣ የሚሰጡት ገንቢ ምጋቤ ምላሾች፣ በተማሪዎች መካከል ያለው የእርስ በርስ የመማማር ሁኔታ፣ ወዘተ. ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ እንደሆኑ Puhl (1997፣4) ይገልፃሉ::

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ተማሪዎች ለተከታታይ ምዘና አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ የሚያደርጓቸው ቢሆንም፤ በሌሎች ምክንያቶች ተማሪዎች ስለምዘና የሚኖራቸው ግንዛቤ አሉታዊ ገፅታ ሊኖረው ይችላል:: ለምሳሌ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ባሳለፏቸው የተለያዩ ምዘናዎች ላይ መጥፎ አጋጣሚዎችን አይተው ከሆነ አሉታዊ የሆነ አመለካከት እንደሚያድርባቸው Elington and Earl (1997፣4) ይገልፃሉ::

ተማሪዎች ስለተከታታይ ምዘናዎች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ከተፈለገ መምህራን ተከታታይ ምዘናን የሚጠቀሙበት ዓላማ የሚያስተምሩትን ትምህርት ለማሻሻልና ተማሪዎችን ለማበረታታት መሆን እንዳለበት Elington and Earl (1997፣7)፣ NIED (1999፣7) ይገልፃሉ::

2.9.2. መምህራን በተከታታይ ምዘና ላይ ያላቸው ግንዛቤና ልምድ

አብዛኛውን ጊዜ መምህራን የሚጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች ከዚህ በፊት እነሱ ተማሪዎች በነበሩበት ጊዜ አስተማሪዎቻቸው ይጠቀሙባቸው የነበሩትን የምዘና ስልቶች መሰረት እንደሚያደርግ Alemayehu (2004፣4)እና NOE (2005፣3) ይገልፃሉ:: በተጠቀሱት ዕሁፎች ውስጥ እንደተገለፀው መምህራን በምዘና ጊዜ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ከጊዜ እጥረት፣ ከቁሳቁስ እጥረት፣ ከግንዛቤ ማነስ፣ ከተማሪ ቁጥር መብዛትና ከአመለካከት ችግር ጋር የተያያዙ ናቸው::

Black and William (1998፣37) ፣ Nitko (2005፣27)፣ እንደሚገልጹት ብዙ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና በቂ የሆነ ግንዛቤ የላቸውም:: ይህ ደግሞ መምህራን በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ደካማ የሆነ አተገባበር እንዲኖራቸው ያደርጋል:: በመሆኑም የተጠቀሰውን ችግር ለማስወገድ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር ማስተካከል እንደሚገባቸው NIED (1999፣7) ይገልፃል::

መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ላይ ደካማ የሆነ እንቅስቃሴ እንዲያሳዩ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

- አብዛኛውን ጊዜ የምዘና አተገባበራቸው የሚያበረታታው ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ምን ያህል እንዳስታወሱት ብቻ ስለሚሆን፣
- መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎችን ለመመዘን በማሰብ የሚያወጧቸውን ጥያቄዎች በጥንቃቄ ስለማያስቡባቸውና ደግመው ደጋግመው በጥያቄዎቹ ዙሪያ ከጓደኞቻቸው ጋር ስለማይወያዩ፣
- መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ያላቸው ስልጠና አነስተኛ ስለሚሆን፣
- ለስልጠናው የሚጠቀሟቸው መፃህፍት የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶችን እንዲጠቀሙ ስለማይጋብዟቸው፣
- የምዘናው ትኩረት አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎችን በሂደት ለማስተማር ሳይሆን ውጤት ለመስጠት ብቻ ስለሚሆን፣

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቋቋምና የተከታታይ ምዘና አተገባበርን ውጤታማ ለማድረግ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና በቂ የሆነ ግንዛቤ ሊኖራቸው እንደሚገባና ስለሂደታዊና ውጤታዊ የምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች አሰልጣኝ መምህራን ተገቢውን ስልጠና ማግኘት እንደሚገባቸው Nitko (2005፣21) ይገልፃሉ::

## 2.10. ምጋቤ ምላሽና ተከታታይ ምዘና

AED/BESO II (2005፣10) እንደሚያመለክተው፣ መምህራን ተማሪዎች ያገኙትን ውጤት ብቻ ዝም ብለው የሚያስቀምጡላቸው ከሆነ ተማሪዎች አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ አግኝተዋል ለማለት ያስቸግራል:: በተለይም ዝቅተኛ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች የመማር ችሎታ እንደሌላቸው አድርገው ነው የሚቆጥሩት:: ይህንን ለማስወገድ ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ መሰረት በማድረግ ገንቢ እና አቅጣጫ ጠቋሚ ምጋቤ ምላሽ በተከታታይ ሊሰጣቸው ይገባል::

Brook (2002፣79) እንደሚገልጹት፣ የምዘና ዋነኛ ዓላማ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ነው:: ምጋቤ ምላሽ መስጠትና መቀበል የተከታታይ ምዘና ማዕከላዊ ትኩረት ነው:: ይህም በመሆኑ ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች ሊቀበሉት የሚችሉት፣ ጠቋሚ፣ ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያለው፣ ትክክለኛ፣ ወቅታዊ፣ ግልፅ እና ተማሪዎችን የሚያሳትፍ መሆን አለበት::

መምህራን አብዛኛውን ጊዜአቸውን ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ላይ ማዋል አለባቸው:: የትምህርቱን ይዘት ለመሸፈን ብቻ መሯሯጥ የለባቸውም:: Race et al. (2005፣105-106)

ደግሞ "አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች የሚፈልጉት ፈጣን የሆነ ምጋቤ ምላሽ ነው" ይላሉ:: ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው ተግባራት መምህራን ፈጣን የሆነ ምጋቤ ምላሽ ካልሰጧቸውና ተማሪዎች የሚያከናውኑት ተግባርና ምጋቤ ምላሹ የሚሰጥበት ጊዜ ክፍተታቸው በጣም የሰፋ ከሆነ የምጋቤ ምላሹ ውጤታማነት በጣም ዝቅተኛ ይሆናል::

## 2.11. ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር የሚያስችሉ መሠረታዊ ነገሮች

እንደ ICDR (2004፣15) እና Elington and Earl (1997፣4) ገለፃ፣ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች የተከታታይ ምዘናን ለመተግበር የሚያስችሉ ናቸው::

- ምዘና የታቀደ ተግባር መሆን አለበት:: ምዘናው ሲታቀድ መቼ እና እንዴት እንደሚካሄድ በጥንቃቄ መታቀድ አለበት::
- መምህሩ ስለተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶች አተገባበር እውቀቱና ችሎታው ሊኖረው ይገባል::
- በምዘና ሂደት የተለያዩ የምዘና ስልቶችን መምረጥና ማዘጋጀት ያስፈልጋል::
- የምዘና ስልቶቹ ለተማሪዎች በሚቀርቡበት ጊዜ በግልፅ እና በማያሻማ ቋንቋ መቅረብ አለባቸው::
- በምዘና ሒደት የተማሪዎችን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ውጤቶች በአግባቡ መዝግቦ መያዝ ያስፈልጋል:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ Ministry of Education, Youth and Culture of Jamica (2004፣29-38) እንደሚያሳስበው በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ የምዘና ተግባራት ውጤት ከተሰጣቸው በኋላ በአግባቡና በግልፅ ሁኔታ ተደራጅተው ሊቀመጡ ይገባል:: በመሆኑም ለተማሪዎችም ሆነ ለሚመለከተው ክፍል ተገቢውን መረጃ በወቅቱ ለመስጠት ያመቻል:: የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ውጤቶች አንድ በአንድ መዝግቦ መያዝ በያንዳንዱ የምዘና ስልት የት ደረጃ ላይ እንዳሉ ለመለየት ያስችላል::

ከላይ ከተጠቀሰው ሐሳብ በተጨማሪ Jaroliemk and Parker (1997፣27) የሚከተሉት ነገሮች ጥሩ ምዘናን ለማካሄድ እንደ መመሪያ ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ::

- ምዘና ማተኮር ያለበት በትምህርቱ ላይ ብቻ መሆን አለበት:: የምዘና ዓላማ ተማሪውን ለማበረታታትና የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል እንጅ ደካማ ተማሪዎችን

ለመቅጣትና ለማስፈራራት መሆን የለበትም:: በመሆኑም ምዘና ተማሪዎችን የሚያግዝና የሚያበረታታ መሆን አለበት::

- ምዘና በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የእርስ በርስ ትብብር የሚያበረታታ መሆን አለበት:: አብዛኛውን ጊዜ በፈተና መልክ የሚሰጥ ምዘና የተማሪዎችን የእርስ በርስ ትብብር የሚያበረታታ አይደለም::
- የተማሪዎችን አጠቃላይ ችሎታና ብቃት እውነተኛ የሆኑ ተግባራትን ለመስጠት መመዘን ያስፈልጋል::
- ምዘና ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል የሚያሳትፍና አድልዎ የሌለበት መሆን አለበት::

ጥሩ የተከታታይ ምዘናን ለማካሄድ አንድ መምህር ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የሚከተሉትን ነገሮች ማከናወን እንዳለበት NIED (1999፣ 17) ይገልፃል፤

- ተማሪዎች አንድን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ማሳየት የሚጠበቅባቸውን የባህሪ ለውጥ ማቀድ፣
- በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያስፈልጉ ተግባራትን ማቀድ፣
- በእቅዱ ውስጥ የሰፈሩትን አላማዎች መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የሚመዘኑበትን የምዘና ስልት ማቀድ::

አንድ የትምህርት ዕቅድ ተማሪዎች የሚመዘኑበትን የተከታታይ ምዘና መንገድ ማካተት አለበት:: አንድ መምህር የትምህርት ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ስለ ተማሪዎቹ ሁኔታ በተለያዩ ጊዜያት በተከታታይ ምዘና አማካይነት የተገኙትን መረጃዎች ሊጠቀምባቸው ይችላል:: መምህሩ ስለተማሪዎቹ ሁኔታ በቂ የሆነ መረጃ መያዙ ለሚከተሉት ተግባራት ይጠቅመዋል፤

- የሚያስተምረውን ትምህርት በተሻለ ሁኔታ ለማቀድ፣
- ተማሪው እንዲያሳይ የተጠበቀበትን የባህሪ ለውጥ በትክክል ማሳየት መቻሉንና አለመቻሉን ለመገምገም፣
- ተማሪዎች በሚገባ ያልተማሩትን ነገር ለመለየትና እንደገና ለማስተማር፣
- የትኛውን የምዘና ስልት መጠቀም እንዳለበት ለመወሰን:: የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ለማሰባሰብ የተለያዩ ዘዴዎችን እንደምንጠቀም ሁሉ በመማር ማስተማሩ ሂደትም የተለያዩ የምዘና ስልቶችን እንጠቀማለን:: ነገር ግን በመማር ማስተማሩ ሂደት የምዘና ስልቶችን በምንጠቀምበት ጊዜ ትክክለኛውን የምዘና ስልት መጠቀም መቻል አለብን::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ለተማሪዎችዎ ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ይሰጣሉ? | አዎ | | አይደለም | |
| | | 12 | 100 | - | - |
| 7 | በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎ" ከሆነ ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) በሚሰጡበት ጊዜ የሚያተኩሩት በምን ላይ ነው? | ትክክለኛውን መልስ በመንገር | | ትክክለኛውን መልስ በመንገርና ተማሪው ማዳበር የሚገባውን በተመለከተ ገንቢ አስተያየት በመስጠት | |
| | | - | - | 12 | 100 |
| 8 | ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት መቼ መቼ ነው፡? | በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር ላይ | | ፈተናዎችንና አሳይመንቶችን በምመልስበት ጊዜ | |
| | | 3 | 25 | 9 | 75 |

በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ አሠልጣኝ መምህራን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተከታታይ ምዘናን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማወቅና ተከታታይ ምዘናን በትምህርት ዕቅዳቸው ላይ ታሳቢ በማድረግ ማካተት አለማካተታቸውን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች፣ ሁሉም አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘናን በመማር-ማስተማሩ ሂደት እንደሚጠቀሙበትና ተከታታይ ምዘናን በትምህርት እቅዳቸው ውስጥ ታሳቢ በማድረግ እንደሚያካትቱ፡ ገልፀዋል፡፡

በተራ ቁጥር 3 ላይ በቀረበው ጥያቄ፣ አሠልጣኝ መምህራን በትምህርት ዕቅዳቸው ውስጥ የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ፣ ጊዜ እና ዘዴ በግልፅ ማስቀመጣቸውንና አለማስቀመጣቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ 58.3% የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ በግልፅ እንደማያስቀምጡ ሲገልጹ፣ 50% የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን ደግሞ የተከታታይ ምዘናውን ጊዜ በግልፅ እንደማያስቀምጡ ገልፀዋል፡፡ የተከታታይ ምዘናውን ዘዴ በተመለከተ ደግሞ 41.6% የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን በግልፅ እደማያስቀምጡ አመልክተዋል፡፡

በተራ ቁጥር 4 እና 5 ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚያተኩሩት በመመዝገቢያ ቅፆች አጠቃቀምና አዘገጃጀት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም አሠልጣኝ መምህራን የተማሪዎችን

የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመከታተያ (የመመዝገቢያ) ቅፆችን እንደሚጠቀሙ በአወንታ ሲልጹ፣ የመመዝገቢያ ቅፆችንም ኮሌጆቹ አዘጋጅተው እንደሚሰጧቸው አመልክተዋል፡፡

በተራ ቁጥር 6፣7 እና 8 ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች የሚያተኩሩት በምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ አሠልጣኝ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ በማለት በአዎንታ ሲገልጹ፣ ምጋቤ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜም ትኩረታቸው ትክክለኛውን መልስ በመንገርና ተማሪው ማዳበር ስለሚገባው ነገር ገንቢ አስተያየት በመስጠት ላይ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ ምጋቤ ምላሽ መቼ መቼ እንደሚሰጡ ለቀረበላቸው ጥያቄ ደግሞ፣ 25% የሚሆኑት መምህራን በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር ላይ እንደሚሰጡ ሲገልጹ፣ 75% የሚሆኑት መምህራን ደግሞ ፈተናዎችን፣ የግል ሥራዎችንና የቡድን ሥራዎችን ለተማሪዎች በሚመልሱበት ጊዜ እንደሚሰጡ አመልክተዋል፡፡

በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን ተከታታይ ምዘናን በመማር-ማስተማሩ ሂደት እንደሚጠቀሙና በትምህርት እቅዳቸው ውስጥም ታሳቢ በማድረግ እንደሚያካትቱ አመልክተዋል፡፡ ይህ ምላሽ ደግሞ "ተከታታይ ምዘና የመማር-ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካል ነው፡፡" ከሚለው ከNIED(1999) እና ELington and Earl(1997) እምነት ጋር ይስማማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ምላሽ መምህራን በሠንጠረዥ 5 በተራ ቁጥር 5 ላይ ከሰጡት ምላሽ ጋር ከፍተኛ ተደጋጋፊነት አለው፡፡ ይሁን እንጅ በተራ ቁጥር 3 ላይ በቀረበው ጥያቄ፣ በአማካይ ግማሽ የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን በእቅዳቸው ውስጥ የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ፣ ጊዜ እና ዘዴ በግልፅ እንደማያስቀምጡ አመልክተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራን ባዘጋጁአቸው የኮርስ ቢጋሮች (Course outlines) ላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ የምዘና ስልቶችን ብቻ ከመጥቀስ ባለፈ ስለምዘናው ዓላማ፣ እያንዳንዱ የምዘና ስልት መቼ እንደሚካሔድ ወዘተ. የተብራራ ነገር አልሰፈረም (አባሪ 5፣ 6 እና 7ን ይመለከቷል)፡፡ ይህ ደግሞ ከተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ምክንያቱም ተከታታይ ምዘናን በክፍል ውስጥ ውጤታማ በሆኑ መልኩ ለመተግበር መምህራን ግልፅ የሆነ ዕቅድ ማዘጋጀት ስለሚያስፈልጋቸው ነው፡፡



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

በተራ ቁጥር 4 እና 5 በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ አሠልጣኝ መምህራን በሰጡት ምላሽ፣ ሁሉም አሠልጣኝ መምህራን የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመመዝገቢያ ቅፆች ይጠቀማሉ፡፡ ነገር ግን የመመዝገቢያ ቅፆቹ ተዘጋጅተው የሚሰጧቸው ከየኮሌጆቹ ሬጅስትራሮች ነው፡፡ ይሁን እንጅ ከአሠልጣኝ መምህራን ጋር በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት በየኮሌጆቹ ተዘጋጅተው የሚቀርቡት የውጤት ማስፈሪያ ቅፆች ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ የምዘና ተግባራት በአግባቡ አስፍሮ ለመያዝ አመቺነት እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውጤት ማስፈሪያ ቅፆቹ ሁሉንም የትምህርት ዓይነት ለሚያስተምሩ መምህራን እንዲሆኑ ተብለው ለጋራ አገልግሎት የተዘጋጁ ናቸው፤ በመሆኑም ቅፆቹ ከቋንቋ ክሂሎች አንፃር በክፍለ ትምህርት ደረጃ ተሸንሽነው ሊዘጋጁ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱም በሬጅስትራር ደረጃ የሚዘጋጀው የውጤት መስፈሪያ ቅፅ በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ዝርዝር የቋንቋ የምዘና ተግባራት በወጉ ሸንሽኖ ባለማሳየቱ እና ሁሉንም የምዘና ተግባራት በወጉ መዝግቦ ለመያዝ አመቺ ባለመሆኑ ነው፡፡ ከየኮሌጆቹ ከተሰበሰቡት የውጤት ማስፈሪያ ቅፆች ላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻም ጎልተው የሚታዩት ተግባራት የቡድን ስራ፣ የግልስራና ፈተናዎች ናቸው፡፡(ለተጨማሪ ማብራሪያ አባሪ 8፣ 9 እና 10ን መመልከት ይቻላል፡፡)

በተራ ቁጥር 6 እና 7 ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉም አሠልጣኝ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ገንቢ ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ አመልክተዋል፡፡ ነገር ግን በተራ ቁጥር 8 ላይ በቀረበው ጥያቄ አብዛኞቹ(75%) መምህራን ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት ፈተናዎችን፣ የግልና የቡድን ሥራዎችን ለተማሪዎች አርመው በሚመልሱበት ጊዜ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ይህ ደግሞ "ተማሪዎች በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር ላይ ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ማግኘት አለባቸው" ከሚለው የምሁራን ሐሳብ ጋር አይጣጣምም፡፡ ለምሳሌ Race et al. (2005 ፣105-106) እንደሚገልጹት፤

> *ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው የምዘና ተግባራት መምህራን ፈጣን የሆነ ምጋቤ ምላሽ ካልሰጧቸውና፣ ተማሪዎች የሚያከናውኑት ተግባርና ምጋቤ ምላሽ የሚሰጥበት ጊዜ ክፍተታቸው በጣም የሰፋ ከሆነ የምጋቤ ምላሽ ውጤታማነት በጣም ዝቅተኛ ይሆናል፡፡*

## 4.4. ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ አሠልጣኝ መምህራን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘ መረጃ ትንተና

በዚህ ንኡስ ርዕስ ሥር አሠልጣኝ መምህራን ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ለማሳየት በጽሑፍ መጠይቁ ላይ የሰጧቸው ምላሾች ተተንትነዋል፤

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ-14

ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ

መምህራን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ምን ያህል አዘውትረው ይጠቀሙበታል? | የጊዜ ድግግሞሽን የሚያሳዩ አማራጮች | | | | | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ (5) | አብዛኛውን ጊዜ (4) | አንዳንድ ጊዜ (3) | አልፎ አልፎ (2) | በፍጹም (1) | | |
| | | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | ብዛት | | |
| 1 | ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘት ለመወሰን | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3.10 | 1.31 |
| 2 | ደከም ላሉ ተማሪዎች የማስተካከያ እገዛ ለመስጠት | - | 2 | 3 | 7 | - | 2.58 | 0.79 |
| 3 | ትምህርታቸውን በደንብ እየተከታተሉ ላሉ ተማሪዎች የማጠናከሪያ እገዛ ለመስጠት | 1 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2.58 | 1.37 |
| 4 | የሚቀጥለውን የትምህርት ዕቅድ ለማውጣት | 2 | 4 | 1 | 5 | - | 3.25 | 1.21 |
| 5 | የትምህርት አቀራረቡን ለማስተካከል | 4 | 6 | 2 | - | - | 4.17 | 0.71 |
| 6 | ተማሪዎች ግልፅ ያልሆነላቸውን ይዘት እንደገና ለማስተማር | 3 | 6 | 3 | - | - | 4.00 | 0.73 |
| 7 | ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ለመስጠት | 4 | 6 | 2 | - | - | 4.17 | 0.71 |
| 8 | የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ | - | 2 | 3 | 7 | - | 2.58 | 0.79 |
| 9 | የምዘና ስልቶች ለመወሰን | 2 | - | 4 | 6 | - | 2.83 | 1.11 |

የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ በሠንጠረዥ 14 ላይ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ይተነተናል፤

ከቀረበው ሠንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው፣ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ በቀዳሚነት የሚጠቀሙበት የትምህርት አቀራረቡን ለማስተካከል (አማካይ=4.17)እና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት (አማካይ=4.17) ሲሆን፣ የሁለቱም መደበኛ ልይይት(0.17)እንደሚያሳየው በመላሾች መካከል የጎላ የአጠቃቀም ልዩነት አለመኖሩንና መስማማታቸውን ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አሠልጣኝ መምህራኑ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ ተማሪዎች ግልፅ ያልሆነላቸውን ይዘት እንደገና ለማስተማር (አማካይ=4.00) አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ተግባራት በተጨማሪ አሠልጣኝ መምህራን ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የሚቀጥለውን የትምህርት ዕቅድ ለማውጣት (አማካይ=3.25) እና ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘት ለመወሰን (አማካይ=3.10) እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሁለቱ ተግባራት መካከል ያሉት መደበኛ ልይይቶችም በተከታታይ (1.21) እና (1.31) ናቸው፡፡ ከመደበኛ ልይይቶቹ መገንዘብ የሚቻለው በሁለቱ ተግባራት መካከል ያለው ልዩነት አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ ይህ አነስተኛ ልዩነትም የአሠልጣኝ መምህራን ምላሽ ከአማካይ ብዙ እንደማይርቅና በአሠልጣኝ መምህራን መካከል የጎላ የአጠቃቀም ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጅ ከአሠልጣኝ መምህራኑ ምላሽ መገንዘብ እንደሚቻለው ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የምዘና ስልቶችን ለመወሰን (አማካይ=2.83)፣ ደከም ላሉ ተማሪዎች የማስተካከያ እገዛ ለመስጠት (አማካይ=2.58)፣ ትምህርታቸውን በደንብ እየተከታተሉ ላሉ ተማሪዎች የማጠናከሪያ እገዛ ለመስጠት (አማካይ=2.58) እና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ (አማካይ= 2.58) አዘውትረው የማይጠቀሙባቸው መሆኑን ነው፡፡

ከመጠይቁ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው አሰልጣኝ መምህራን ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ አዘውትረው የሚጠቀሙበት የትምህርት አቀራረቡን ለማስተካከል፣ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት፣ ተማሪዎች ግልፅ ያልሆነላቸውን ይዘት እንደገና ለማስተማር፣

የትምህርት ዕቅድ ለማውጣትና ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘት ለመወሰን ነው፡፡ ምንም እንኳን አሰልጣኝ መምህራን ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው ቢገልጹም፣ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የምዘና ስልቶችን ለመወሰን፣ ደከም ላሉ ተማሪዎች የማስተካከያ እገዛ ለመስጠት፣ ትምህርታቸውን በደንብ እየተከታተሉ ላሉ ተማሪዎች የማጠናከሪያ እገዛ ለመስጠትና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ የመሳሰሉ ተግባራትን አዘውትረው እንደማይጠቀሙባቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በትምህርት ልማት አካዳሚ የመሰረታዊ ትምህርት ስልታዊ ግብ (1997፣30-41) እንደሚገልጸው ደግሞ ከተከታታይ ምዘና የሚገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የተለያዩ የማጠናከሪያና የማስተካከያ እገዛዎችን መስጠት አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከተማሪዎች ጋር በተደረገው የቡድን ተኮር ውይይት መገንዘብ እንደተቻለው መምህራን ለተማሪዎቻቸው የተለያዩ የማጠናከሪያና የማስተካከያ እገዛዎችን እንደማያደርጉላቸው ነው፡፡

## 4.5. ተማሪዎች ስለ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ የተገኘ መረጃ ትንተና

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር በተማሪዎች ዕይታ ምን እንደሚመስል ለማየት ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቁ ላይ የሰጧቸው ምላሾች በመልክ በመልካቸው ተፈርጀው ተተንትነዋል፡፡

ሠንጠረዥ-15

የመመሪያና የመስፈርት ግልፅነትን፣ የሚደረግላቸውን እገዛና የሚሰጣቸውን ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | መምህራን የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ከመስጠታቸው በፊት ግልፅ መመሪያ እና ማብራርያ ይሰጡኛል፡፡ | 42 | 31.1 | 14 | 10.3 | 79 | 58.5 |
| 2 | መምህራን ስራዎቹን ሲመዘኑ ግልፅ መስፈርት ይጠቀማሉ፡፡ | 24 | 17.7 | 11 | 8.1 | 100 | 74.0 |
| 3 | በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ በማሳያቸው ድክመቶች መምህራን የማስተካከያ እገዛ ያደርጉልኛል፡፡ | 18 | 13.3 | 13 | 9.6 | 104 | 77.0 |
| 4 | በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ መምህራን የተለያዩ የማጠናከሪያ ተግባራትን እየሰጡ ችሎታየን የበለጠ እንዳዳብር ያደርጉኛል፡፡ | 13 | 9.6 | 4 | 2.9 | 118 | 87.4 |
| 5 | ለማከናውናቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራት መምህራን ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት)ይሰጡኛል፡፡ | 11 | 8.1 | 5 | 3.7 | 119 | 88.1 |

ከሠንጠረዥ 15 መመልከት እንደሚቻለው በተራ ቁጥር 1 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 58.5% የሚሆኑት ተማሪዎች መምህሮቻቸው የቡድንና የግል የምዘና ተግባራትን ከመስጠታቸው በፊት ግልፅ የሆነ መመሪያ እና ማብራሪያ እንደማይሰጧቸው ሲያመለክቱ፣ በተራ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ ሁለት ሦስተኛ (74%) የሚሆኑት ተማሪዎች መምህሮቻቸው ሥራዎቻቸውን ሲመዝኑ ግልፅ መስፈርት እንደማይጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ 77% የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ ለሚያሳዩአቸው ድክመቶች በመምህራን የማስተካከያ እገዛ እንደማይደረግላቸው ሲገልጹ፣ በተመሳሳይ መልኩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው(87.4%) ተማሪዎች መምህሮቻቸው በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የማጠናከሪያ ተግባራትን እንደማይሰጧቸው በተራ ቁጥር 4 ላይ አመልክተዋል፡፡ በተራ ቁጥር 5 ላይም 88.1% የሚሆኑት ተማሪዎች መምህሮቻቸው ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጧቸው ገልፀዋል፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ከላይ ከቀረቡት ውጤቶች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው የግል እና የቡድን ተግባራት ከአሠልጣኝ መምህራን ግልፅ የሆነ መመሪያ እና ማብራሪያ እንደማያገኙና አሠልጣኝ መምህራንም የተማሪዎቻቸውን ሥራዎች ለመመዘን ግልፅ መስፈርት እንደማይጠቀሙ ነው፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ በተካሄደው ምልከታ እንደተስተዋለውም ከየቡድኑ አንዳንድ ተማሪዎች ስለ ልቦለድ እና ኢ-ልቦለድ ልዩነት እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ አሠልጣኝ መምህሩ ማስታወሻ እየያዙ የተማሪዎችን ስም እየጠየቁ የተሳትፎ ውጤት ይሰጡ ነበር፡፡ መምህሩ ይህንን ነገር ለተማሪዎች ግልጽ ያደረጉላቸው በትምህርቱ መጨረሻ ላይ እንጂ መጀመሪያ ላይ አልነበረም፡፡ ተማሪዎች ባከናወኗቸው የግል ሥራዎች ላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻም አሠልጣኝ መምህራኑ ውጤት ለመስጠት መስፈርቶችን አልተጠቀሙም (አባሪ 11 እና 12ን ይመለከቷል)፡፡ ይሁን እንጅ Brown and Kinght (1994፣ 102) በአፅንኦት እንደሚያሳስቡት፣ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ስራዎች በሚመዝኑበት ጊዜ መመሪያዎችንና መስፈርቶችን ለተማሪዎች በግልፅ መናገርና ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መመሪያዎችንና መስፈርቶችን ግልፅ ማድረጉ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ያግዛቸዋል፡፡

ምንም እንኳን ተከታታይ ምዘናን በመማር-ማስተማሩ ሂደት የማካተቱ ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የሚያሳዩአቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይቶ ምጋቤ ምላሽ፣ የማስተካከያና የማጠናከሪያ እገዛ ለመስጠት ቢሆንም፣ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራኑ ግን ለተማሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽና የማስተካከያ እገዛ እንደማይሰጡ በተማሪዎች የግል ሥራዎች ላይ ከተደረገው የሰነድ ፍተሻና ከተገኘው የቡድን ተኮር ውይይት ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ እንደተስተዋለው፣ አንድ መምህር ብቻ ተማሪዎች ስማዊ ሐረግንና ግሳዊ ሐረግን ወጥተው ጥቁር ሰሌዳ ላይ እየለዩ በሚያሳዩበት ጊዜ ስህተቶችን በማረም ላይ ብቻ ያተኮረ ምጋቤ ምላሽ ይሰጧቸው ነበር፡፡ ሌሎች መምህራን ግን ይሰጡ የነበሩት ምጋቤ ምላሽ ሳይሆን ማጠቃለያ ነበር፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሃሳቦች በተጨማሪ ምንም እንኳን አሠልጣኝ መምህራን ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ለመስጠት አዘውትረው እንደሚጠቀሙበት በሠንጠረዥ 14 ተራ ቁጥር 7 ላይ ቢገልጹም፣ ተማሪዎች በሠንጠረዥ 15 ተራ ቁጥር 5 ላይ ከሰጡት ምላሽ ጋር ግን ይቃረናል፡፡

ሠንጠረዥ-16

## በተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እና የአሠልጣኝ መምህራንን የተከታታይ ምዘና ትኩረት በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 6 | በቋንቋ ትምህርቱ ሒደት ሁሌጊዜ የራሴን ስራ በራሴ እገመግማለሁ፡፡ | 30 | 22.2 | 11 | 8.1 | 94 | 69.6 |
| 7 | በቡድንም ሆነ በግል ለማከናውናቸው ተግባራት ጓደኞቹ አስተያየት (ምጋቤ ምላሽ) ይሰጡኛል፡፡ | 42 | 31.1 | 9 | 6.6 | 84 | 62.2 |
| 8 | በማከናውናቸው የቡድንና የግል የምዘና ተግባራት የመምህራን ትኩረት አንድን ነገር እንዴት አድርጌ እንደሰራሁት ማየት ሳይሆን ምን እንደሰራሁ ማየት ነው፡፡ ማለትም ከስራው ሒደት ይልቅ በውጤቱ ላይ ያተኩራሉ፡፡ | 101 | 74.8 | 15 | 11.1 | 19 | 14.0 |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ እንደሙከራ፣ የቡድንና የግል ስራ የመሳሰሉ የምዘና ስልቶችን የሚጠቀሙት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሒደት ያሳየሁትን መሻሻል ለመመዘን ሳይሆን ውጤት ለመስጠት ነው፡፡ | 92 | 68.1 | 13 | 9.6 | 30 | 22.2 |
| 10 | ከተለያዩ የምዘናስልቶች የማገኘው መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለብኝን ነገር እንድገነዘብ አስችሎኛል፡፡ | 43 | 31.8 | 19 | 14.0 | 73 | 54.0 |

በተራ ቁጥር 6 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 69.6% የሚሆኑት ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ሒደት የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንደማይመዝኑ ሲገልጹ፣ ከግማሽ በላይ (62.2%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ በተከታታይ ምዘና ሒደት ለሚያከናውኗቸው የቡድንና የግል ተግባራት ጓደኞቻቸው አስተያየት (ምጋቤ ምላሽ) እንደማይሰጧቸው አመልክተዋል፡፡ በተራ ቁጥር 8 ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ተማሪዎች እንደገለጹት በሚያከናውኗቸው የተከታታይ ምዘና ተግባራት የመምህሮቻቸው ትኩረት በውጤቱ ላይ እንጅ በሒደቱ ላይ



ILS LIBRARY ... UNIVERSITY

አይደለም፡፡ 68.1% የሚሆኑት ተማሪዎች በተራ ቁጥር 9 ላይ እንደገለጹት፣ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህሮቻቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶችን የሚጠቀሙት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ሒደት ያሳዩትን መሻሻል ለመመዘን ሳይሆን ውጤት ለመስጠት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ 54% የሚሆኑት ተማሪዎች እንዳመለከቱ ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚያገኙት መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን ነገር እንዲገነዘቡ አላስቻላቸውም፡፡

ከላይ ከቀረበው የትንተና ውጤት መገንዘብ የሚቻለው፣ ተማሪዎች የጓደኞቻቸውንና የራሳቸውን ሥራ በራሳቸው እንዲመዝኑ እድል አላገኙም፡፡ ይህ ሁኔታ በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ ላይም አልተስተዋለም፡፡ ይሁን እንጅ Shaaban (2001፣ 20)፣ Harris (1997፣10) እና Puhl (1997፣7) እንደሚያሳስቡት በተከታታይ ምዘና ወቅት ተማሪዎች የጓደኛ ለጓደኛ እና የራሳቸውን ሥራ በራሳቸውን እንዲመዝኑ (እንዲገመግሙ) ማድረግ የቋንቋ ችሎታቸውን የበለጠ እንዲያዳብሩና ብስለት የተሞላበት የማሰብ ችሎታ እንዲያጎለብቱ ያደርጋቸዋል፡፡

ምንም እንኳን ተከታታይ ምዘናን በመማር-ማስተማሩ ሂደት የማካተቱ ዋነኛ ዓላማ የትምህርት አሠጣጡን ሂደት ለማሻሻል ቢሆንም፣ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ግን ተከታታይ ምዘናን የሚጠቀሙት ውጤት ለመስጠት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚያገኙት መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን ነገር እንዲገነዘበቡ አለማስቻሉ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ትኩረት በሒደቱ ላይ ሳይሆን በውጤቱ ላይ ያተኮረ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሠንጠረዥ-17

አሠልጣኝ መምህራን ለተማሪዎች ያላቸውን ሚዛናዊነት በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 11 | በተከታታይ ምዘና ሒደት የሰራናቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ስራዎች እንዴት እንደሚታረሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ከመምህራን ጋር ተወያይተን እንወስናለን፡፡ | 27 | 20.0 | 18 | 13.3 | 90 | 66.6 |
| 12 | ለምሰራቸው የግልና የቡድን ስራዎች የማገኘው ውጤት ከስራዩ ጋር የሚመጣጠን እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ | 45 | 33.3 | 20 | 14.8 | 70 | 51.8 |
| 13 | በቋንቋ ትምህርቱ ሒደት የስራሁት ስራ አጥጋቢ ካልሆነ ድክመቴን የማሻሽልበት ሌላ እድል ይኖረኛል፡፡ | 18 | 13.3 | 13 | 9.6 | 104 | 77.0 |

በተራ ቁጥር 11 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 66.6% የሚሆኑ ተማሪዎች የስሯቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ስራዎች እንዴት እንደሚታረሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ከመምህሮቻቸው ጋር ተወያይተው እንደማይወስኑ አመልክተዋል፡፡ ይህ ምላሽ ደግሞ በሰንጠረዥ 3 በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው የግንዛቤ ጥያቄ 66% የሚሆኑት አሠልጣኝ መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር ይስማማል፡፡ ይህም ምላሽ በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት ያለባቸው መምህራን ናቸው የሚል ነው፡፡ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (51.8%) ተማሪዎች፣ ለሚሰሯቸው የቡድንና የግል ሥራዎች የሚያገኙት ውጤት ከስራቸው ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ ሲያመለክቱ፣ በተመሳሳይ መልኩ በተራ ቁጥር 13 ለቀረበው ጥያቄ ከሦስት እጅ በላይ (77.0%) በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ሒደት የሰሩት ሥራ አጥጋቢ ካልሆነ ድክመታቸውን የሚያሻሽሉበት ሌላ ዕድል እንደማይኖራቸው ገልፀዋል፡፡

በተራ ቁጥር 11 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ከተገኘው ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው 66.6% የሚሆኑት ተማሪዎች የሰሯቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ሥራዎች እንዴት

እንደሚታረሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ከመምህሮቻቸው ጋር ተወያይተው አይወስኑም፡፡ ይሁን እንጅ Pierce (2002፣19) የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት ሂደት ተማሪዎችን ማሳተፍና እንዲወስኑ ማድረግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም መስፈርቶችን በማውጣት ሂደት የምዘናው ትኩረት (ዓላማ) የትላይ እንደሚሆን እንዲገነዘቡ ስለሚያደርጋቸው ነው፡፡

በተራ ቁጥር 12 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ከተገኘው ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው ከግማሽ በላይ (51.8%) የሚሆኑት ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው የተለያዩ የቡድንና የግል የምዘና ተግባራት የሚያገኙት ውጤት ከስራቸው (ከድካማቸው) ጋር የማይመጣጠን መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ Ministry of Education Youth and Culture of Jamica(2004 ፣ 13) ሲያሳስብ፣ "ከእያንዳንዱ መደበኛ ምዘና ቀደም ብሎ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የተለያዩ ሥራዎች በምን ዓይነት መስፈርት እንደሚመዘኑ ለተማሪዎች ማሳወቅ ይገባቸዋል" ይላል፡፡ መምህራን ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን የተለያዩ ስራዎች እንዴት አድርገው እንደሚመዝኑና ውጤት እንደሚሰጡ በሚናገሩበት ጊዜ ተማሪዎች በመስፈርቶቹ መሰረት ስራዎቹን ለማከናወንና ጥሩ ውጤት ለማግኘት ተግተው ይሰራሉ፡፡ ይሁን እንጅ መምህራን የመመዘኛ (ውጤት መስጫ) መስፈርቶችን የማይጠቀሙና ለተማሪዎች የማያሳውቁ ከሆነ የተማሪዎችን ሥራዎች በሚያርሙበትና ውጤት በሚሰጡበት ጊዜ ግለሰባዊ አድልዎ ሊያድርባቸው ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ያገኙነው ውጤት ከሥራችን (ከልፋታችን) ጋር የማይመጣጠን (ኢፍትሐዊ) ነው ሊሉ ይችላሉ፡፡

በተራ ቁጥር 13 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ከተገኘው ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው፣ ከሦስት እጅ በላይ (77%) የሚሆኑት ተማሪዎች እንደገለጹት በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሰሩት ሥራ አጥጋቢ ካልሆነ ድክመታቸውን የሚያሻሽሉበት ሌላ እድል አይኖራቸውም፡፡ ይሁን እንጅ የተለያዩ ምሁራን በአፅንኦት እንደሚገልጹት፣ ከተከታታይ ምዘና ዓላማዎች መካከል አንዱ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የሚያሳዩትን ጠንካራና ደካማ ጎን መለየትና የተሻለ ውጤታማ እንዲሆኑ መርዳት ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ NIED(1999) እንደሚገልጸው፤

> *የተከታታይ ምዘና ዋነኛ ዓላማ ተማሪዎች በሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መለየትና ማገዝ ነው፡፡ ችግሮችን ከተለያየ አቅጣጫ ለመረዳትና ለመለየት የተለያዩ ናሙና የመመዘኛ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ እድሉን ማመቻቸት አንዱ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡*

ሠንጠረዥ-18

## ከአሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ያገኙትን ጥቅም በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 14 | ከሙከራ፣ ከቤት ስራ፣ ከቡድንና ከግል ስራ የማገኘው መረጃ የራሴን የጥናት ፕሮግራም እንዳስተካክል ረድቶኛል፡፡ | 26 | 19.2 | 11 | 8.1 | 98 | 72.5 |
| 15 | በቡድንና በግል የማከናውናቸው የተለያዩ የምዘና ተግባራት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የማሳያቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንድለይ አስችለውኛል፡፡ | 36 | 26.6 | 20 | 14.8 | 79 | 58.5 |
| 16 | በጽሑፍ ፈተና ላይ ከተመሰረተ ምዘና ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት የማከናውናቸው የቤት ስራዎች፣ የቡድን ስራዎችና የግል ስራዎች በአማርኛ ቋንቋ የምወስደውን ስልጠና የተሻለ አድርገውልኛል፡፡ | 63 | 46.6 | 17 | 12.5 | 55 | 40.7 |

በተራ ቁጥር 14 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ከተገኘው ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው፣ 72.5% የሚሆኑት ተማሪዎች እንደገለጹት፣ ከተከታታይ ምዘና የሚያገኙአቸው መረጃዎች የጥናት ፕሮግራማቸውን እንዲያስተካክሉ በማድረግ በኩል እድሉን አልፈጠረላቸውም፡፡ 58% የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የሚካሄዱ ምዘናዎች ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ለይተው እንዲያወቁ አላስቻላቸውም፡፡ በተራ ቁጥር 16 ላይ ደግሞ ግማሽ (46.6%) ያህሉ ተማሪዎች በፅሁፍ ፈተና ላይ ከተመሰረተ ምዘና ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት የሚያከናውኗቸው የቤት ሥራዎች፣ የቡድን ሥራዎች እና የግል ሥራዎች በአማርኛ ቋንቋ የሚወስዱትን ሥልጠና የተሻለ እንዳደረገላቸው ሲገልጹ፣ ተመሳሳይ ቁጥር (40.7%) ያላቸው ተማሪዎች ደግሞ በቀረበው ጥያቄ አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡

ተከታታይ ምዘና እያንዳንዱ ተማሪ ራሱን ከመማር-ማስተማሩ ሁኔታዎች ጋር እንዲያስተካክልና መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ የራሱ የወደፊት አቅጣጫ እንዲኖረው በማበረታታት በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ከዚህ በፊት ለመግለፅ እንደተሞከረው፣



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዲለዩ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታም ማስተካከልና የበለጠ ማጎልበት ስለሚገባቸው ነገሮች እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ ከተማሪዎች ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው የመምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ከላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሞች እንዲያገኙ እድሉን አልፈጠረላቸውም፡፡ ምክንያቱም በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሒደት አሰልጣኝ መምህራን ተማሪዎች ማዳበር ስለሚገባቸው ነገር ግልፅ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ስለማይሰጧቸው ነው፡፡

## ሠንጠረዥ-19

### በተከታታይ ምዘና ሂደት ስለሚሰማቸው ሃላፊነትና ከጓደኞቻቸው ጋር ስላለው ትብብር የተማሪዎች ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መስማማት | | መወሰን አልችልም | | አለመስማማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድምር | | ድምር | | ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 17 | በተለያዩ ጊዜያት በቡድንና በግል የማከናውናቸው የምዘና ተግባራት ከፅሁፍ ፈተና ይልቅ በትምህርቱ የራስ ተነሳሽነትና ሓላፊነት እንዲሰማኝ አስችለውኛል፡፡ | 32 | 23.7 | 16 | 11.8 | 87 | 64.4 |
| 18 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በቡድን፣ በግልና በቤት ስራ መልክ የሚሰጡኝ ምዘናዎች የተለያዩ ተግባራትን (ስራዎችን) ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመተባበር እንድሰራ አስችሎኛል፡፡ | 96 | 71.1 | 15 | 11.1 | 24 | 17.7 |
| 19 | በሰነደትምህርት፣ በክፍል ስራ፣ በቡድንና በግል ስራ መልክ የሚካሔዱት የምዘና ተግባራት የፅሁፍ ፈተናን ያህል አያስጨንቁኝም፡፡ | 44 | 32.5 | 18 | 13.3 | 73 | 54.0 |
| 20 | በቡድንና በጥንድ የሚከናወኑ ተግባራት አንደኛው ተማሪ በሌላኛው ተማሪ ላይ ጥገኛ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ | 90 | 66.6 | 7 | 5.1 | 38 | 28.1 |

በተራ ቁጥር 17 ለቀረበው ጥያቄ ከተገኘው ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው፣ ሁለት ሦስተኛ (64.4%) የሚሆኑት ተማሪዎች ፣ ተከታታይ ምዘና በትምህርቱ ሐላፊነት ተሰምቶኝ የቡድንና የግል ተግባራትን እንዳከናውን አላስቻለኝም ብለዋል፤ ይሁን እንጅ

71.1% የሚሆኑት ተማሪዎች፣ በተራ ቁጥር 18 ላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የሚሰጡኝ የተከታታይ ምዘናዎች የተለያዩ ተግባራትን ከክፍል ጓደኞች ጋር በመተባበር እንድሰራ አስችሎኛል ብለዋል፡፡ በተራ ቁጥር 19 ላይ በቀረበው ጥያቄ 54% የሚሆኑት ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና መልክ የሚሰጧቸው ተግባራት እንደሚያስጨንቃቸው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም 66.6% የሚሆኑት ተማሪዎች በተራ ቁጥር 20 ላይ እንዳመለከቱት በቡድንና በጥንድ የሚከናወኑ የምዘና ተግባራት አንደኛው ተማሪ በሌላኛው ተማሪ ላይ ጥገኛ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

Puhl (1997) እና Shaaban (2001) እንደሚገልጹት፣ በተከታታይ ምዘና ሒደት ተማሪዎች የየራሳቸውን ስራዎች በራሳቸው እንዲመዝኑ ማበረታታት ተማሪዎች በሚሰሩት ሥራ የሐላፊነት ስሜት እንዲሰማቸውና የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ በጣም ይጠቅማል፡፡ ይሁን እንጅ ተማሪዎች እንደገለጹት፣ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህሮቻቸው የተከታታይ ምዘና አተገባበር አንድን ሥራ ሃላፊነት ተሰምቷቸው በራሳቸው እንዲያከናውኑ አላስቻላቸውም፡፡

Elington and Earl(1997) በአፅንኦት እንደሚገልጹት ደግሞ፣ አንድ ምዘና ሲታቀድ ምዘናው መቼ እና እንዴት እንደሚካሄድ በግልፅ መስፈር አለበት፡፡ አግባብነት የሌለው የምዘና አጠቃቀም በተማሪዎች ዘንድ ጭንቀትን ይፈጥራል፡፡ በተራ ቁጥር 19 ላይ ደግሞ ተማሪዎች እንዳመለከቱት አሰልጣኝ መምህራን የሚሰጧቸው የምዘና ተግባራት ያስጨንቃቸዋል፡፡ በፅሁፍ መጠይቁ በቀረበው ክፍት ጥያቄ ላይ እንዳመለከቱትም ለቡድንና ለግል ስራዎች ማከናወኛ የሚሰጧቸው ጊዜ እንደሚያጥራቸውና ስራዎቹን በተመደበው ጊዜ ለመጨረስ ሲሉ እንደሚሯሯጡና ይህም ጭንቀት እንደፈጠረባቸው ገልፀዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በቡድን ሥራ ጊዜ አብዛኛውን ሥራ የሚሰሩት ጠንካራ የሆኑት የቡድን አባላት ብቻ መሆናቸው፣ ሌሎች አባላት ግን በሥራው ላይ ሙሉ ተሳትፎ እንደማያደርጉ በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ እና በጽሑፍ መጠይቁ ላይ ተገልጿል፡፡

## 4.6. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በጽሑፍ መጠይቁ እና በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ለቀረቡላቸው ልቅ ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ትንተና

በጽሑፍ መጠይቁ ላይ የቀረቡት ልቅ ጥያቄዎች የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘናን እንዴት እንደሚተገብሩት እና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሒደት ምን ምን ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው ለማወቅ (ለመፈተሽ) የተዘጋጁ ናቸው::

በተራ ቁጥር 1 ላይ የቀረበው ልቅ ጥያቄ ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ መልኩ አሠልጣኝ መምህራን ሥልጠና መሳተፋቸውን ወይም አለመሳተፋቸውን የሚጠይቅ ነው:: በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረትም፣ በሦስቱም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ያሉ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ፣ ተከታታይ ምዘናን በተመለከተ ሥልጠና ላይ መሳተፋቸውን ገልፀዋል:: የተከታታይ ምዘናው ስልጠና ይዘቶችም እንደ አብዛኞቹ መምህራን ገለፃ ስለተከታታይ ምዘና ምንነት፣ ስለተከታታይ ምዘና ዓላማ፣ ስለተከታታይ ምዘና ዘዴዎች፣ ስለምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ወዘተ. በማለት ዘርዝረዋል:: የተከታታይ ምዘናው ሥልጠና በተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው ላይ ምን ለውጥ እንዳመጣ ሲገልጹም፣ የትምህርት አቀራረባቸውን ለማስተካከል፣ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት፣ በትምህርታቸው ደከም ላሉ ተማሪዎች እገዛ ለመስጠት፣ የምዘና ዓይነቶችን በአግባቡ ለመተግባር እንዳስቻላቸው ገልፀዋል:: ለምሳሌ ያህል አንድ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህር የወሰዱት የተከታታይ ምዘና ሥልጠና በተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው ላይ የሚከተለውን ለውጥ እንዳመጣ ገልፀዋል፤

> *የወሰድኩት የተከታታይ ምዘና ሥልጠና የትምህርት አቀራረቡን ለማስተካከል፣ ተማሪዎች ግልፅ ያልሆነላቸውን ይዘት እንደገና ለማስተማር እና ደካም ላሉ ተማሪዎች እገዛ ለመስጠት በጣም ረድቶኛል::*

ከላይ በአሠልጣኝ መምህራን የተሰጡት ምላሾች፣ ተማሪዎች በሠንጠረዥ 15 ላይ ከሰጡት ምላሽ ጋር ይቃረናል:: እዚህ ላይ መምህራን እንዳመለከቱት፣ የወሰዱት የተከታታይ ምዘና ሥልጠና በትምህርታቸው ደከም ላሉ ተማሪዎች እገዛ ለመስጠት ረድቷቸዋል፤ ይሁን እንጅ በተራ ቁጥር 3 ላይ 77% የሚሆኑት ተማሪዎች እንደገለጹት በቋንቋ

ትምህርቱ ዙሪያ በሚያሳዩአቸው ድክመቶች አሠልጣኝ መምህራን የማስተካከያ እገዛ አያደርጉላቸውም፡፡

በተራ ቁጥር 2 ላይ የቀረበው ልቅ ጥያቄ በተከታታይ ምዘና አተገባበር አሰልጣኝ መምህራን እስከአሁን ያጋጠሟቸው ችግሮች ምንምን እንደሆኑ እንዲገልጹ የሚያደርግ ነው፡፡ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረትም በሦስቱም መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ አብዛኞቹ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያጋጥሙናል ብለው ከጠቀሷቸው ችግሮች መካከል ከአቅም በላይ ክፍለ ጊዜያት መያዝ፣ የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ ከተማሪዎች ጋር የሚደረግ አላስፈላጊ የውጤት ይገባኛል ጭቅጭቅ፣ የጊዜ እጥረት፣ የማስተማሪያ ሞጁሎች ስፋት በመምህራን በኩል ስለተከታታይ ምዘና በቂ ዕውቀትና ክሂል አለመኖር የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በቡድን ተኮር ውይይት መልክ ለአሠልጣኝ መምህራን የቀረቡት ጥያቄዎች በይዘታቸው በጽሑፍ መጠይቁ ላይ ከቀረቡት ልቅ ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን ምን ዓይነት የምዘና ሥልቶችን እንደሚጠቀሙ፣ በተከታታይ ምዘና ሂደት የተማሪዎችን የተለያዩ የምዘና ተግባራት መዝግቦ ለመያዝ ስለሚጠቀሙበት ቅፅ አመቺነት፣ በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮች እና ስለመፍትሔዎቹ ሐሳብ እንዲሰጡ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

ከቡድን ተኮር ውይይቱ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተውም፣ አሠልጣኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች የክፍል ሥራ፣ የቤት ሥራ፣ የቡድን ሥራ፣ የግል ሥራ ናቸው፡፡ የተማሪዎችን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመቆጣጠርና መዝግቦ ለመያዝ የሚጠቀሙበት የተከታታይ ምዘና ቅፅ የሚዘጋጀው በኮሌጆቹ ሬጅስትራሮች እንጅ በትምህርት ክፍሉ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከሚጠቀሙት ምዘና አንፃር በወጉ ተሸንሽኖ ያልቀረበና አመቺነት የሌለው መሆኑ በውይይቱ ላይ ተገልጾአል፡፡ ይህን ሲተመለከቱ ከአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ጋር በተካሔደው የቡድን ተኮር ውይይት አንድ መምህር የሚከተለውን ብለዋል፤

*የውጤት ማስፈሪያው ማርክ ሊስት (ቅፅ) በትምህርት ክፍል ደረጃ (ከቋንቋ ትምህርት አንፃር) ታይቶና ከቋንቋ ከሂሎች አንፃር ተሸንሽኖ ቢዘጋጅ፣ መምህራን የተለያዩ የቋንቋ የምዘና ተግባራትን በአግባቡ መዝግበው እንዲይዙና እንዲቆጣጠሩ ያስችላቸዋል። ማርክ ሊስቱ በዲፖርትመንት ደረጃ ቢዘጋጅና ለእያንዳንዱ የቋንቋ የምዘና ተግባርም ራሱን የቻለ ማርክ ተሸንሽኖ ቢቀርብለት የተሻለ ነው።*

Alausa (1999) እና Ministry of Education, Youth and Culutre of Jamica (2004) በአፅንኦት እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ ተከታታይ ምዘናን በአግባቡ ለመተግበርና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመለየት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚያከናውኗቸውን የምዘና ተግባራት ውጤት በአግባቡ መዝግቦ መያዝ ያስፈልጋል።

አሠልጣኝ መምህራን በጽሑፍ መጠይቁ ላይ በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሒደት ያጋጥሙናል ብለው የጠቀሷቸው ችግሮች በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይም ተጠቅሰዋል። በመሆኑም ችግሮቹን ለመፍታትና ተከታታይ ምዘና በአግባቡ እንዲተገበር ለማስቻል ስለተከታታይ ምዘና ምንነት፣ ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር፣ ስለተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው ብለዋል። ከዚህም በተጨማሪ የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ዕውቀት ማጎልበት እንደሚገባም ገልፀዋል።

## 4.7. ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቁና በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ለቀረቡላቸው ልቅ ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ትንተና

በፅሁፍ መጠይቁ ላይ የቀረቡት ልቅ ጥያቄዎች፣ ተማሪዎች በአሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያስተዋሏቸውን (ያዩአቸውን) ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዲገልጹ እና በችግሮቹ ዙሪያ የመፍትሔ ሓሳቦችን እንዲሰነዝሩ የሚያስችሉ ናቸው።

የአሠልጣኝ መምህራንን ጠንካራ ጎን በተመለከተ በሦስቱም ኮሌጆች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት አብዛኞቹ ተማሪዎች እንደገልጹት በተለያዩ ጊዜያት መምህራን የሚሰጧቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ሥራዎች ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩና የአማርኛ ቋንቋ

ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ አስችሎአቸዋል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች እንደገልጹት ደግሞ፣ የተለያዩ የቡድንና የግል ሥራዎችን በሚሰሩበት ጊዜ ከቤተ መጻሕፍት የተለያዩ ማጣቀሻ መጻሕፍትን እንዲያነቡና ዕውቀታቸውን እንዲያሰፉ አስችሎአቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ተማሪ በፅሁፍ መጠይቁ ላይ የሚከተለውን አስተያየት አስፍሮአል፤

> *አዎ መምህራችን የሚሰጡን የተከታታይ ምዘና ተግባራት ከጓደኞቻ ጋር ሁኜ ከላይብረሪ ብዙ ዕውቀት እንድዳስስ ያደርገኛል፡፡ ይህ ማለት የሚሰጡኝን በቂ መረጃ ተጠቅሜ ብዙ ዕውቀት አግኝቻአለሁ፡፡ ለቀጣይም በዚህ እንዲቀጥሉበት አስተያየት እሰጣለሁ፡፡*

በሌላ በኩል ደግሞ አሠልጣኝ መምህሮቻቸው የተከታታይ ምዘናን ሲተገብሩ ያስተዋሏቸውን ደካማ ጎኖች አንስተዋል፡፡ በጽሑፍ መጠይቁና በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ከተጠቀሱት ደካማ ጎኖች መካከል ለሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ የቡድን ሥራ መስጠት፣ የቡድንና የግል ሥራዎችን በወቅቱ አርሞ አለመመለስ፣ ማዳላት፣ ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ አለመስጠት፣ ለቡድንና ለግል ሥራዎች ተገቢውን ውጤት አለመስጠት፣ ግልፅ ትዕዛዝና መመሪያ አለመስጠት፣ የሚሰራውንና የማይሰራውን ተማሪ አለመለየት፣ ወዘተ. በአብዛኞቹ ተማሪዎች የተጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህልም አንድ ተማሪ የሚከተለውን አስተያየት ሰንዝሯል፤

> *የሥራነው የግልም ሆነ የቡድን ሥራ በትክክል አይታይም (አይታረምም)፡፡ ዝም ብለው ላይ ላዩን ማለትም ሽፋኑን አይተው እንደመሰላቸው ነው የሚያርሙት፡፡ ሌላም ነገር ማዳላት አለ፤ የቡድንና የግል ስራ ታይቶ አይመለስልንም፡፡*

Jarolemik and parker (1997) በአፅንኦት እንደሚያሳስቡት ደግሞ፣ ምዘና ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል የሚያሳትፍና አድልዎ የሌለበት መሆን አለበት፡፡



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

በመጨረሻም የመምህሮቻችሁን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ለማሻሻል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ? በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ የተለያዩ የመፍትሔ ሃሳቦችን የጠቆሙ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል መምህራን የሚሰራውንና የማይሰራውን ተማሪ መለየት አለባቸው፤ መምህራን የግልና የቡድን ስራዎችን በወቅቱ አርመውና ምጋቤ ምላሽ ሰጥተው መመለስ አለባቸው፤ የሚሉት በአብዛኞቹ ተማሪዎች ተደጋግመው የተነሱ አስተያየቶች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሓሳቦች

### 5.1. ማጠቃለያ

የመማር-ማስተማሩ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ተከታታይ ምዘናን በትክክል ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማም በትግራይ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች (ማለትም በዓድዋ፣ በዓብይ ዓዲ እና በመቀሌ ኮሌጆች) የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተጠቀሰውን ዋነኛ ዓላማ መሰረት በማድረግ፣ በየኮሌጆቹ የሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል፣ በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት የትኞቹን የምዘና ስልቶች እንደሚጠቀሙ፣ በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ለተማሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ መስጠት አለመስጠታቸውንና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ምን እንደሆኑ ለመዳሰስ ያለመ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት መምህራን፣ ተማሪዎችና ሰነዶች ናቸው፡፡ በጥናቱ ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ደግሞ የጽሑፍ መጠይቅ፣ የቡድን ተኮር ውይይት፣ ምልከታ እና የሰነድ ፍተሻ ናቸው፡፡

አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ 20 የግንዛቤ ጥያቄዎች የተዘጋጁ ሲሆን፣ እነዚህም የግንዛቤ ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው ከ"በጣም እስማማለሁ" እስከ "በጣም አልስማማም" ያሉ የመስማማት ደረጃዎችን የያዙ አማራጮች ያሏቸው ናቸው፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች መሠረት የተሰበሰቡት መረጃዎች በመቶኛ የአኃዛዊ ስሌት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በተከታታይ ምዘና ሂደት አሠልጣኝ መምህራን የትኞቹን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ለመፈተሽ የተለያዩ የምዘና ስልቶችን የያዙ አስራ አንድ ጥያቄዎች ለሁለቱም ወገን ማለትም ለመምህራንና ለተማሪዎች የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህም

ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው ከ'ሁልጊዜ' እስከ 'በፍጹም' ያሉትን የጊዜ ድግግሞሽን የሚያሳዩ የውሳኔ ሐሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡ በመጨረሻም በነዚህ ጥያቄዎች መሠረት የተሰበሰቡት መረጃዎች ከአሃዛዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች መካከል አማካይንና መደበኛ ልይይትን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሠልጣኝ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሟቸውን የምዘና ሥልቶች ለመከታተል 7 የመከታተያ ነጥቦችን የያዘ የምልከታ ቅፅ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በምልከታው መሠረት የተገኙት መረጃዎች በዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ አሠልጣኝ መምህራን ከተከታታይ ምዘና የሚገኙትን መረጃዎች ምን ያህል አዘውትረው እንደሚጠቀሙባቸው ለማወቅ የተለያዩ ተግባራትን የያዙ 9 ዝግ ጥያቄዎች ለመምህራን የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህም ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው ከ'ሁልጊዜ' እስከ 'በፍጹም' ያሉ የጊዜ ድግግሞሽን የሚያሳዩ የውሳኔ ሓሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጥያቄዎች የተገኙት መረጃዎችም አማካይንና መደበኛ ልይይትን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

የተከታታይ ምዘና አተገባበርን በተመለከተ ለአሠልጣኝ መምህራን 8 ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህም ጥያቄዎች ስለተከታታይ ምዘና እቅድ፣ ስለ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥና ስለ ውጤት መመዝገቢያ (ማስፈሪያ) ቅጹ የሚያትቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጥያቄዎች የተገኙት መረጃዎችም በመቶኛ የሒሳብ ስሌት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

የመምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር በተማሪዎች እይታ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ለተማሪዎች 20 ዝግ የግንዛቤ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህም ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው ከ"በጣም እስማማለሁ" እስከ "በጣም አልስማማም" ያሉ የመስማማት ደረጃዎችን የሚያሳዩ አማራጮች ያሏቸው ናቸው፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች መሠረት የተገኙት መረጃዎች በመቶኛ የሒሳብ ስሌት ተተንትነዋል፡፡

በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት አሠልጣኝ መምህራንና ተማሪዎች ያጋጠሟቸውንና ያስተዋሉአቸውን ችግሮች በተመለከተ በፅሁፍ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልትን በመከተል ተተንትነዋል፡፡

ከአራቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ማለትም ከጽሑፍ መጠይቅ፣ ከቡድን ተኮር ውይይት፣ ከምልከታ እና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች ከተተነተኑ በኋላ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

1. የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል በተደረገው የግንዛቤ አሰሳ አማካይነት ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ በጽሑፍ መጠይቁ ላይ የቀረቡት ዝግ ጥያቄዎች ምላሽ እንደሚያሳየው አሰልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህ (ተከታታይ ምዘና የመማር-ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካል ስለመሆኑ)፣ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በማነሳሳትና በማነቃቃት በኩል ስለሚሰጠው ጥቅም፣ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት በኩል ስለሚሰጠው ጥቅም፣ ስለተከታታይ ምዘና ዓላማ (በውጤት ላይ ሳይሆን በሒደት ላይ ስለማተኮሩ) ጥሩ ግንዛቤ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጅ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ስለሚሰጠው ጥቅም፣ ስለተከታታይ ምዘና ዕቅድ፣ ተከታታይ ምዘና ከቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ ጋር ስላለው ግንኙነት፣ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት ሒደት መምህራንና ተማሪዎች ስለሚኖራቸው የእርስበርስ ሚና እና ስለምጋቢ ምላሽ አሰጣጥ ያላቸው ግንዛቤ የተሟላ አለመሆኑን ከምላሾቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡
2. ለመምህራንና ለተማሪዎች ባቀረቡት ጥያቄዎችና በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ መሰረት አሰልጣኝ መምህራን የሚጠቀሟቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች የቡድን ሥራ፣ የግል ሥራ፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ እና በተወሰነ መልኩ የቤት ሥራ እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡
3. የተከታታይ ምዘና አተገባበርን በተመለከተ አሠልጣኝ መምህራን በጽሑፍ መጠይቁ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ የተከታታይ ምዘናን በመማር-ማስተማሩ ሂደት እንደሚጠቀሙና በትምህርት ዕቅዳቸውም ታሳቢ በማድረግ እንደሚያካትቱ አመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጅ መምህራን ባዘጋጇቸው የኮርስ

ቢጋሮች ወይም እቅዶች ላይ በተደረገ የሰነድ ፍተሻ የምዘና ሥልቶችን ከመጥቀስ ባለፈ ስለእያንዳንዱ ምዘና ዓላማ፣ ዘዴ እና መቼ እንደሚካሔድ በግልፅ የሰፈረ ነገር የለም፡፡

4. የምጋቢ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ መምህራን የሰጧቸው ምላሾች እንደሚያመለክቱት አሠልጣኝ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ምጋቢ ምላሽ እንደሚሰጡ አመልክተዋል፡፡ ነገር ግን እንደ አብዛኞቹ መምህራን ምላሽ፣ ምጋቢ ምላሽ የሚሰጡት የግል ሥራዎችንና የቡድን ሥራዎችን ለተማሪዎች አርመው በሚመልሱበት ጊዜ እንጅ በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር ላይ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከተማሪዎች በተሰበሰቡ የግል ሥራዎች ላይ በተካሔደው የሰነድ ፍተሻ መገንዘብ የተቻለው አሰልጣኝ መምህራን ምጋቢ ምላሽ እንደማይሰጡ ነው፡፡

5. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር በተማሪዎች ዕይታ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው፣ ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው የቡድንና የግል የምዘና ተግባራት አሠልጣኝ መምህራን ግልፅ የሆነ መመሪያ እና ማብራሪያ እንደማይሰጧቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምላሾቹ እንደሚያሳዩት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ሥራዎች ለመመዘን ግልፅ መስፈርት አለመጠቀማቸውን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በግል ሥራዎች ላይ በተደረገ የሰነድ ፍተሻ ተስተውሏል፡፡ ውጤቶቹ መስፈርትን መሠረት በማድረግ ሳይሆን በጥቅሉ ነው የተቀመጡት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራኑ ተማሪዎች የራሳቸውን ሥራ በራሳቸው እንዲመዝኑ እድሉን አላማመቻቸታቸው፣ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት ሂደት ተማሪዎችን አለማሳተፋቸው፣ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ለተማሪዎች የማስተካከያና የማጠናከሪያ እገዛ አለመስጠታቸውና፣ ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው የቡድንና የግል የምዘና ተግባራት ምጋቢ ምላሽ አለመስጠታቸው ከተማሪዎች ምላሾች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

6. በሦስቱም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያጋጥሙናል ብለው ከጠቀሷቸው ችግሮች መካከል ከአቅም በላይ ክፍለ ጊዜያት መያዝ፣ የተማሪ ቁጥር

መብዛት፣ የማስተማሪያ ሞጁሎች ስፋት እና በመምህራን በኩል ስለተከታታይ ምዘና በቂ ዕውቀትና ክሂል አለመኖር ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች አሠልጣኝ መምህሮቻቸው ተከታታይ ምዘናን ሲተገብሩ ካስተዋሏቸው ችግሮች መካከል ለሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ የቡድን ሥራ መስጠት፣ የቡድንና የግል ሥራዎችን በወቅቱ አርሞ አለመመለስ፣ ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ አለመስጠት፣ ለቡድንና ለግል ስራዎች ተገቢውን ውጤት አለመስጠት፣ ማዳላት፣ ግልፅ ትዕዛዝና መመሪያ አለመስጠት፣ የሚሰራውንና የማይሰራውን ተማሪ አለመለየት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

7. የውጤት ማስፈሪያ ቅጾችን በተመለከተ የጽሑፍ መጠይቁ፣ የቡድን ተኮር ውይይቱ እና የሰነድ ፍተሻው ውጤት እንደሚያሳየው ቅጾቹ ከቋንቋ ክሂል (ከቋንቋ ተግባራት) አንጻር በወጉ ተሸንሽነው የቀረቡ አይደሉም፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

በጥናቱ አማካይነት የተሰበሰቡትን ውጤቶች መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ሊደረስ ተችሏል፤

1. ምንም እንኳን ተከታታይ ምዘናን በመማር-ማስተማሩ ሂደት የማካተቱ ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የሚያሳዩአቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለመለየትና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ቢሆንም፣ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ግን ፈጣንና ገንቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎቻቸው እንደማይሰጧቸው ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅና የቡድን-ተኮር ውይይት ለማወቅ ተችሏል፡፡
2. ምንም እንኳን የጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት መምህራን መካከል እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በኮሌጆቹ የሚሰጠውን የከፍተኛ ዲፕሎማ ሥልጠና እና ስለተከታታይ ምዘና ሌሎች ተጨማሪ አጫጭር ሥልጠናዎችን በማግኘታቸው ምክንያት ስለተከታታይ ምዘና የተሻለ ተጋልጦ (exposure) ቢኖራቸውም ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ ግን የተሟላ አይደለም፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

3. የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙባቸው የምዘና ሥልቶች፣ የቡድን ሥራ፣ የግል ሥራ፣ እየወጡ ማቅረብና የቤት ሥራ ናቸው፡፡ እነዚህ የምዘና ስልቶች ደግሞ በአብዛኛው የተማሪዎችን የመፃፍና የመናገር ችሎታ የሚያዳብሩ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሠልጣኝ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የምዘና ስልቶች በመማር-ማስተማሩ ሂደት እና ከማስተማር በኋላ የሚካሄዱ የምዘና ተግባራትን ነው፡፡ በመሆኑም ከማስተማር በፊት የሚካሄዱ የምዘና ተግባራትን አይጠቀሙም፡፡

4. አሠልጣኝ መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት የሚያጋጥሟቸው ችግሮች የክፍለጊዜያት መብዛት፣ የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ ከተማሪዎች ጋር የሚደረግ አላስፈላጊ የውጤት ይገባኛል ጭቅጭቅ፣ የማስተማሪያ ሞጁሎች ስፋት እና በመምህራን በኩል ስለተከታታይ ምዘና በቂ ዕውቀትና ክህሎት አለመኖር ናቸው፡፡

5. ከአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ተማሪዎች ያስተዋሏቸው ችግሮች ለሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ የቡድን ሥራ መስጠት፣ የቡድንና የግል ሥራዎችን በወቅቱ አርሞ አለመመለስ፣ ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ አለማግኘት፣ ለቡድንና ለግል ሥራዎች ተገቢውን ውጤት አለመስጠት፣ ግልፅ ትዕዛዝና መመሪያ አለመስጠት፣ የሚሰራውንና የማይሰራውን ተማሪ አለመለየት ናቸው፡፡

6. ምንም እንኳን ከተከታታይ ምዘና መርሆዎች ውስጥ አንዱ የተማሪዎች ስራ የሚመዘንበትን መስፈርት ለተማሪዎች ማሳወቅና መስፈርት በማውጣቱ ሒደትም ተማሪዎችን ማሳተፍና እንዲወስኑ ማድረግ ቢሆንም፤ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ግን የተማሪዎችን የቡድንና የግል ሥራዎች መስፈርት አውጥተው እንደማያርሙና መሥፈርት በማውጣት ሒደትም ተማሪዎችን እንደማያሳትፉ ከሰነድ ፍተሻውና ከፅሁፍ መጠይቁ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

7. ተከታታይ ምዘና በእቅድ የሚመራ ተግባር ሆኖ ሳለ፣ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ግን ተከታታይ ምዘናዎችን መቼ እና እንዴት እንደሚተገብሩ በትምህርት እቅዳቸው ውስጥ በግልጽ አለማካተታቸው በተደረገው የሰነድ ፍተሻ አማካይነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

8. ተከታታይ ምዘናን በአግባቡ ለመተግበር ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚያከናውኗቸውን የቋንቋ የምዘና ተግባራት በአግባቡ መዝግቦ መያዝ መሠረታዊ

ነገር ቢሆንም፤ የውጤት ማስፈሪያ ቅጾቹ ግን ከቋንቋ ክሂሎች አንፃር በወጉ ያልተሸነሸኑ እና ጥቅል ተግባራትን የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## 5.3. የመፍትሔ ሐሳቦች

በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች መሠረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

1. ተማሪዎች በየጊዜው ለሚያከናውኗቸው የምዘና ተግባራት አሠልጣኝ መምህራን ፈጣንና ገንቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ቢሰጧቸው፤ AED/BESOII (2005) እንደሚያመለክተው የተከታታይ ምዘና ዋነኛ ዓላማ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ነው፡፡ መምህራን ተማሪዎች ያገኙትን ውጤት ብቻ ዝም ብለው የሚያስቀምጡላቸው ከሆነ፣ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ ስለሚያሳዩት ጠንካራና ደካማ ጎን የሚሰጠው መረጃ የለም፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው ተግባራት በየጊዜው ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ስለተከታታይ ምዘና ዓላማና መርህ እንዲሁም የተለያዩ የምዘና ሥልቶችን እንዴት እንደሚተገበሩ አሠልጣኝ መምህራን ቀጣይነት ያለው ሥልጠና ሊያገኙ የሚችሉበት ዕድል ቢመቻች፤ አሠልጣኝ መምህራን ቀጣይነት ያለው ሥልጠና በሚያገኙበት ጊዜ ስለተከታታይ ምዘና ዓላማና አጠቃላይ መርህ ጥሩ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡ ጥሩ ግንዛቤ ካላቸው ደግሞ ተከታታይ ምዘናን በአግባቡ እንዲተገብሩ ያስችላቸዋል፡፡
3. ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን የተለያዩ የቡድንና የግል የምዘና ተግባራት መምህራን በሚያርሙበትና ውጤት በሚሰጡበት ጊዜ ግልፅ የሆኑ መስፈርቶችን ቢጠቀሙና መስፈርቶቹንም ለተማሪዎች ቢያሳውቁ፤ Sheepard (2000) እንደሚያሳስቡት መስፈርቶቹን ለተማሪዎች ግልፅ ማድረግና መስፈርት በማውጣት ሂደት ተማሪዎችን ማሳተፍ፣ ተማሪዎች በመስፈርቶቹ መሠረት ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡና ተግተው እንዲሰሩ ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተማሪዎችን ሥራ በመስፈርት መሠረት ሲያርሙ ግለሰባዊ አድልዎንና ከተማሪዎች ጋር የሚደረገውን አላስፈላጊ የውጤት ይገባኛል ጭቅጭቅ ይቀንሳሉ፡፡
4. አሠልጣኝ መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ተማሪዎች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ቢያመቻቹ፤ Harris(1999) እና Shaaban(2001) እንደሚያሳስቡት፣

በተከታታይ ምዘና አተባበር ሂደት ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማድረግ ተማሪዎች ስለሚማሩት ነገር ሐላፊነት እንዲሰማቸው፣ በራስ የመተማመን ችሎታ እንዲያዳብሩ፣ ስለምዘና የተለያዩ ነገሮችን እንዲያውቁ እና ምዘና የመምህሩ ሥራ ብቻ አለመሆኑን እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የራሳቸውን ሥራ በራሳቸው በሚመዝኑበት ጊዜ እና የጓደኞቻቸውን ስራ በሚመዝኑበት ጊዜ፣ የቢጤ ምዘና እና የራስ ምዘና ባህልን ያዳብራሉ፡፡ በመሆኑም የእርስ በርስ ትብብራቸውን ከፍ ያደርጋል፡፡

5. አሠልጣኝ መምህራን የሚያከናውኗቸውን የምዘና ተግባራት በአግባቡ ለማካሄድ ግልፅ የሆነ የተከታታይ ምዘና ዕቅድ ቢያዘጋጁ፤ NIED (1999) እንደሚያሳስበው፣ መምህራን የምዘናውን ዓላማ፣ ዘዴ እና ጊዜ በግልፅ የሚያሳይ ዕቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የተከታታይ ምዘናው በዕቅድ የሚመራ ከሆነ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ከወዲሁ መቀነስ ይቻላል፡፡
6. የሦስቱም መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር እየተመካከሩ የሚሰሩበት ሁኔታ በኮሌጆቹ አስተዳደር አካላት ቢመቻች የቋንቋ ትምህርት አሠጣጡን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ ተከታታይ ምዘናን በቋንቋ ክፍል ውስጥ መጠቀም የተማሪዎችን ሁለተኛ ቋንቋ ለማሳደግ ከፍተኛ እገዛ እንዳለው Puhl (1997) ያሳስባሉ፡፡ በመሆኑም የሦስቱም ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን በጋራ እየተመካከሩ የሚሰሩበት ሁኔታ ቢመቻች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ የበለጠ ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡
7. የሦስቱም ኮሌጆች አሠልጣኝ መምህራን የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የምዘና ተግባራት በአግባቡ መዝግቦ ለመያዝ የሚጠቀሙበትን የውጤት ማስፈሪያ ቅጽ በትምህርት ክፍል ደረጃ ከቋንቋ ክሂሎች አንጻር በወጉ ከፋፍለውና ሸንሽነው ቢያዘጋጁ፤

ADDIS ABABA UNIVERSITY ... 'S LIBRARY

## ዋቢ ጽሑፎች


ሰሎሞን ተሰማ (1987) "የቢጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት"፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት:: (ያልታተመ)::

በትምህርት ልማት አካዳሚ የመሰረታዊ ትምህርት ስልታዊ ግብ (1997) ተከታታይ ምዘናና የአጠቃቀም መንገዱ:: በዩናይትድ ስቴትስ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ:: አዲስ አበባ፣ አማኑኤል ማተሚያ ድርጅት::

አልማዝ ሃይሉ (1999) "አራተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት:: (ያልታተመ)::

አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ (1997) "ተከታታይ ምዘና እና ተግበራዊ ምርምር ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ስልጠና የተዘጋጀ" ባህርዳር፣ ያልታተመ ጥራዝ (ሞጁል)::

ዳንኤል ዘውዴ (1999) "የተከታታይ ምዘና አተገባበር"፣ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ ለአጭር ስልጠና የተዘጋጀ:: (ያልታተመ)::

AED/BESO II (2005) "A Concise Manual for Developing and Implementing Continuous Assessment in Teacher Education Institutions and Primary Schools of Ethiopia". Addis Ababa. USAID.

AED/BESO II (2006) "A Concise Manual for Developing and Implementing Continuous Assessment in Teacher Education Institutions and Primary Schools of Ethiopia." Addis Ababa. USAID.

Alausa, A. (1999) "Continuous Assessment in Our Schools: Advantages and Problems." Journal of Educational Reform in Namibia. Vol.13, No.6. Nambia.




ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

Alemayehu Bishaw (2004) "Continuous Assessment." A Compilation of Notes to be Presented at a Workshop Organized by Debremarkos College of Teacher Education. Sponsored by AED/BESO Project. Bahirdar.

Baye Ashebir (2006) "Assessment and Practises of EFL Teachers in Teacher Education Institutions: Alternative Assessment Methods in Focus" Unpublished M.A. Thesis, Addis Ababa University.

Black, P. and William, D (1998) Assessment and Classroom Learning. Assessment in Education, Vol. 5, No.1. http://www.oup.co.uk/jnis/list/elt

Bligh, D and Jagues, D. (1980) Methods and Techniques in Post Secondary Education. Paris: Unesco.

Broks, V. (2002) Assessment in Secondary Schools: Recording, Reporting and Accountablity. Buckingham: Open University Press.

Brown, G. Hull, J. and Pendlebury, M. (1997) Assessing Student Learning in Higher Education. London: Routledge.

Brown, S. and Knight P. (1994) Assessing Learners in Higher Education. London: Routledge.

Crossman, J. (2004) "Factors Influencing the Assessment Perception of Training Teachers," International Education Journal. Vol. 5, No. 4.

Cullingford, C. (1995) The Effective Teacher. New York: Cassell.

Curzon, L. (1990) Teaching in Further Education: An Outline of Principles and Practises. (4th ed). London: Cassel Education Ltd.

Elington, H. and Earl, S. (1997) "Making Effective Use of Continuous Assessment and Portfolios." Available on File://apu.qca.ac.uk/ ciced/ ch.25,htm.56k.

Farrant, j.S. (1980) Principles and Practices of Education (2nd ed). London: Cambridge University Press.

Harris, M. (1997) "Self Assessment of Language Learning in Formal Settings." ELT journal, Vol 51, No.1. Oxford: Oxford University Press.

Heaton, J.B. (1988) Writing English Language Tests. London: Longman Group Limited.

Hedge, T. (2000) Teaching and Learning in Language Classroom. London: Oxford University Press.

Huges, A. (1989) Testing for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

ICDR (2004). "Continuous Assessment and its Application." Addis Ababa. Ministry of Education (unpublished).

Jarolemek, J. and Parker, W. (1997) Social Studies in Elementary Education. New Jersey: Prentice- Hall-Inc.

Livingston, G. (2001) "Taking Teacher Educators Forward." Ten steps Twards Quality: A Report: Ministry of Education. Addis Ababa.

Mc Afee and Leong (1997) Assessing and Guiding young Children Development and Learning (2nd ed.) Oxford: Oxford University Press.

Ministry of Education (2003) "Teacher Education System Overhaul". Addis Ababa. (Unpublished).

Ministry of Educaiton (2004) "Higher Diploma Program for Teacher Educators." A Handbook for Trainers. Addis Ababa.

Ministry of Education, Youth and Culture (2004). "Effective Classroom Assessment: Principles of Continuous Assessment." Jamica. Kingston.

Mulu Nega (2005) "The Current Status of Continuous Assessment Practices at the Addis Ababa University". A Discussion Paper Presented to the National Workshop on Continuous Assessment, Organized by AED/BESO. (3-7 June, 2005). Addis Ababa.

Murphy, P. (1996) Integrating Learning and Assessment: Contemporary Issues in Teaching and Learning. London: Open University Press.

National Institute for Educational Development (NIED) (1999) "Towards Improving Continuous Assessment in Schools: A Policy and Information Guide." Okahandja, Namibia.

Nibret Asrade (2005) "An Evaluation of EFL Teachers' Implementation of Continuous Assessment" Unpublished M.A. Thesis, Addis Ababa University.

Nitko, A.J. (2005). Continuous Assessment in Teacher Education. Washington, DC: Academy for Educational Development.

NOE (2005) "Perspectives of the National Organization for Examinations on Implementation of Continuous Assessment at School Level in Ethiopia." Organized by AED/BESO Project in Collaburation with MOE from June 3-7/2005. Addis Ababa.

Norris, J.M. (2000). "Purposeful Language Assessment: Selecting the Right Alternative Test." English Teaching Forum, Vol, 38, No. 1.

Pasigna, A.L. (2000) "Continuous Assessment: Remediation and Enrichment." Washington, DC: American Institute for Research.

Pierce, L.V. (2002) "Performance Based on Assessment: Promoting Achievement for English Language Learners." ERIC/CLL News Bulletin Fall 2002. Vol. 26, No.1. http://www.cal.org/ericcll/2002fal/ performance htm.

Puhl, C,A. (1997) "Develop, Not Judge: Continuous Assessment in the ESL Classroom." English Teaching Forum, Vol. 35, No. 2.

Race, P., Brown, S. and Smith, B. (2005). 500 Tips on Assessment (2nd ed.). London: Roultedge Falmer.

Richard, H. (2004) "Active Learning in Large Classes. A Continuous Assessment Model." A Paper Presented at the Annual Meeting of the 2004 APSA Teaching and Learning Conference; (http://www.all academic.com/meta/P 117483-index.html)

Shaaban, K. (2001) "Assessment of Young Learners" English Teaching Forum. Vol. 39, No. 4, pp. 16-23.

Shepard, L.A. (2000). "The Role of Assessment in a Learning Culture" Educational Research, Vol., 29, No.7-pp.4-14.

Teshome Demssie (2001) "Assessment of Pupils Achievements in the Teaching of English Training and Practice in focus." The Ethiopian Journal of Education. Vol. 21, No. 1, pp.25-47.

Ur, P. (1996) A Course in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Wall, D. and Alderson, C. (1991) Examining Washback: Philadelphia: Multilingual Matters, Ltd.

Wilkin, L. (1991) The Assessment of Performance and Competence. A Practical Guide for Trainees. London: Stanley Thornes Publishers, Ltd.

Wilson, S. (2002) "Comparing Peer, Self and Tutor Assessment in a Course for University Teaching Staff." http://www.cshe.unimib.edu.au/assessing learning/05/.

# አባሪዎች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አባሪ 1

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

# የድህረ ምረቃ ፕሮግራም

## በኮሌጅ አሠልጣኝ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በትግራይ ውስጥ በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው::

በጥናቱ የሚደረስበት ውጤት የቋንቋ መምህራን በተከታታይ ምዘና ላይ ያላቸውን ግንዛቤና ክህሎት ምን መምሰል እንዳለበት በመጠቆም በኩል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታመናል:: በመሆኑም ከመጠይቁ የሚገኘው ምላሽ ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው ይታሰባል:: ጥናቱ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕግስትና በጥሞና በማንበብ ትክክል ናቸው የሚሏቸውን መልሶች በተሰጡት ቦታዎች ላይ በመፃፍ እንዲመልሱልኝ ስጠይቅ ለሚደረግልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

**ማሳሰቢያ:-**

ሀ. በጽሑፍ መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም::

ለ. መጠይቁን ከሌላ የስራ ባልደረባ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው::

## ክፍል አንድ:- አጠቃላይ መረጃ

1. የሚያስተምሩበት ኮሌጅ ስም ________________
2. ፆታ ________________
3. የትምህርት ደረጃ ____________
4. በኮሌጁ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ አስተምረዋል? __________
5. በኮሌጁ ውስጥ የሚሰጠውን የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም ተከታትለዋል?

   ተከታታየአለሁ ☐ በመከታተል ላይ እገኛለሁ ☐ አልተከታተልኩም ☐

**ክፍል ሁለት:-** ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አምስት አማራጮች ተሰጥተዋል:: እነዚህም አማራጮች በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃዎች የያዙ ናቸው::

5 = በጣም እስማማለሁ

4 = እስማማለሁ

3 = መወሰን አልችልም

2 = አልስማማም

1 = በጣም አልስማማም

እርስዎም ጥያቄዎቹን ካነበቡ በኋላ በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ የ "✓" ምልክት በማድረግ ያስቀምጡ::

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካል ነው:: | | | | | |
| 2 | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘቶች ለመወሰን ይረዳል:: | | | | | |
| 3 | ከተከታታይ ምዘና የተገኘው መረጃ የበለጠ የሚጠቅመው ለአስተማሪው ነው:: | | | | | |
| 4 | እንደ እኔ እምነት ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ለመርዳት ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ በጣም አስፈላጊ ነው:: | | | | | |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5 | በተከታታይ ምዘና ሂደት እቅድ ማወጣት ከፍተኛ ቦታ አለው:: | | | | | |
| 6 | የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በተከታታይ ምዘና ዕቅድ ውስጥ ማካተት በራሱ በቂ ነው:: | | | | | |
| 7 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን እንደየ ቋንቋ ችሎታቸው ለመለየት ያስችላል:: | | | | | |
| 8 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አዘውትረው መገኘታቸውን በተመለከተ በመምህራን የሚደረገው ቁጥጥር የተከታታይ ምዘና አንድ ክፍል ሆኖ ይሰማኛል:: | | | | | |
| 9 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ሥራዎች ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል:: | | | | | |
| 10 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው መገምገም ይችላሉ:: | | | | | |
| 11 | ተከታታይ ምዘና መምህራን ብቸኛ የውሳኔ ሰጭ አካል እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል:: | | | | | |
| 12 | በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት ያለባቸው መምህራን ብቻ ናቸው:: | | | | | |
| 13 | ከተለምዷዊው (በፅሁፍ ፈተና መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርአት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነሳሳል:: | | | | | |
| 14 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተነቃቅተው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል ብዬ አስባለሁ:: | | | | | |
| 15 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት ተማሪዎችን ጎበዝ ወይም ደካማ ናቸው ብሎ ለመፈረጅ እንደሆነ ይሰማኛል:: | | | | | |
| 16 | ከተለምዷዊው (በጽሁፍ ፈተና መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በተሻለ ሁኔታ ለመለየት ያስችላል:: | | | | | |
| 17 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት በአብዛኛው በውጤት ላይ እንጂ በሂደት ላይ አይደለም:: | | | | | |
| 18 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ሲሰጥ ትክክለኛ እና ስህተት መልሶችን በመንገር ላይ ብቻ ማተኮር አለበት:: | | | | | |
| 19 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) መስጠት ያለበት በመምህራን እንጂ በተማሪዎች መሆን የለበትም:: | | | | | |
| 20 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ማተኮር ያለበት ተማሪዎች የሚያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል ነው:: | | | | | |



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

## ክፍል ሦስት:-

ሀ. የሚከተሉትን የተከታታይ ምዘና ስልቶች ተማሪዎችዎን ለመመዘን ምን ያህል እንደሚጠቀሙባቸው ለማወቅ ከምዘና ስልቶቹ ትይዩ አማራጮች ቀርበዋል:: አማራጮቹም በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የጊዜ ድግግሞሽ የሚያሳዩ የውሳኔ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው::

5 - ሁልጊዜ

4- አብዛኛውን ጊዜ

3- አንዳንድ ጊዜ

2- አልፎ አልፎ

1- በፍፁም

እርስዎም በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ የ "√" ምልክት በማደረግ ያመልክቱ::

| ተ.ቁ | የተከታታይ ምዘና ስልቶች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ቅድመ ፈተና | | | | | |
| 2 | የቤት ስራ | | | | | |
| 3 | ምልከታ | | | | | |
| 4 | ሙከራ (ፈተና) | | | | | |
| 5 | የግል ስራ (ፕሮጀክት) | | | | | |
| 6 | የቡድን ስራ (ፕሮጀክት) | | | | | |
| 7 | የመምህር ተማሪ ውይይት | | | | | |
| 8 | ሰነደ ትምህርት (ፖርትፎሊዮ) | | | | | |
| 9 | ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | | | | | |
| 10 | የራስ ምዘና | | | | | |
| 11 | የጓደኛ ለጓደኛ (የቢ.ጤ) ምዘና | | | | | |

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበቡ በኋላ በቀረበው ሳጥን መሰል ክፍት ቦታ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያስቀምጡ::

1. በመማር ማስተማሩ ሂደት የተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

2. በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 'አዎ' ከሆነ ተከታታይ ምዘናን በትምህርት ዕቅድዎ ውስጥ ታሳቢ በማድረግ ያካትታሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

3. በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 'አዎ' ከሆነ የሚከተሉትን ተግባራት በእቅድዎ ውስጥ በግልፅ ያስቀምጣሉ?

   ሀ. የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

   ለ. የተከታታይ ምዘናውን ጊዜ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

   ሐ. የተከታታይ ምዘናውን ዘዴ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

4. የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመከታተያ (የመመዝገቢያ) ቅጾች ይጠቀማሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

5. በተራ ቁጥር 4 ለቀረበው ጥያቄ መልሰዎ 'አዎ' ከሆነ የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት ለመከታተል (ለመመዝገብ) የሚጠቀሙበትን ቅፅ የሚያገኙት ከየት ነው?

   ኮሌጁ አዘጋጅቶ ይሰጠናል

   በትምህርት ክፍል ደረጃ እናዘጋጃለን ☐

6. ለተማሪዎችዎ ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ይሰጣሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

7. በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 'አዎ' ከሆነ፣ ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) በሚሰጡበት ጊዜ የሚያተኩሩት በምን ላይ ነው?

   ትክክለኛውን መልስ በመንገር ☐

   ትክክለኛውን መልስ በመንገርና ተማሪው ማዳበር ስለሚገባው ነገር ገንቢ አስተያየት በመስጠት

8. ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት መቼ መቼ ነው?

በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር ላይ ☐

ፈተናዎችን፣ የግል ሥራዎችንና የቡድን ሥራዎችን ለተማሪዎች በምመልስበት ጊዜ

ሐ. ከዚህ ቀጥሎ ከተከታታይ ምዘና የሚገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የተለያዩ ተግባራት ተዘርዝረዋል:: ከተዘረዘሩት ተግባራት ትይዩ ደግሞ አማራጮች ቀርበዋል:: አማራጮቹም በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የጊዜ ደግግሞሽ የሚያሳዩ የውሳኔ ሐሳቦችን የያዙ ናቸው::

5 - ሁልጊዜ 4- አብዛኛውን ጊዜ 3- አንዳንድ ጊዜ 2- አልፎ አልፎ

1- በፍፁም

እርስዎም ጥያቄዎችን ካነበቡ በኋላ በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ የ "√" ምልክት በማደረግ ያመልክቱ::

| ተ.ቁ | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ምን ያህል ይጠቀሙበታል? | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘት ለመወሰን | | | | | |
| 2 | ደከም ላሉ ተማሪዎች የማስተካከያ እገዛ ለመስጠት | | | | | |
| 3 | ትምህርታቸውን በደንብ እየተከታተሉ ላሉ ተማሪዎች የማጠናከሪያ እገዛ ለመስጠት | | | | | |
| 4 | የሚቀጥለውን የትምህርት ዕቅድ ለማውጣት | | | | | |
| 5 | የትምህርት አቀራረቡን ለማስተካከል | | | | | |
| 6 | ተማሪዎች ግልፅ ያልሆነላቸውን ይዘት እንደገና ለማስተማር | | | | | |
| 7 | ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ለመስጠት | | | | | |
| 8 | የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ | | | | | |
| 9 | የምዘና ስልቶችን ለመወሰን | | | | | |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## ክፍል አራት:- ልቅ ጥያቄዎች

**መመሪያ:- ከዚህ በታች ሦስት ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ስለዚህ የእያንዳንዱን ጥያቄ የአጠያየቅ መንፈስ በመከተል መልሳችሁን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ግለፁ::**

1. ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ መልኩ ሥልጠና ተሳትፈው ያውቃሉ?

   አዎ ☐ አልተሳተፍኩም ☐

   በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 'አዎ' ከሆነ

   ሀ. የተከታታይ ምዘናው ሥልጠና ይዘቶች ምን ምን ነበሩ?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ለ. የተከታታይ ምዘናው ስልጠና በተከታታይ ምዘና አተገባበርዎ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

2. በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት እስካሁን ያጋጠሙዎት ችግሮች ካሉ ምን ምን ናቸው?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

3. በኮሌጁ የሚያስተምሩ አሠልጣኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘናዎችን በአግባቡና በተሳካ ሁኔታ እንዲተገብሩ ለማስቻል ምን መደረግ አለበት ብለው ያስባሉ?

## አባሪ 2

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የድህረ ምረቃ ፕሮግራም

### በኮሌጅ ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በትግራይ ውስጥ በሚገኙ ሶስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል ጥናት ለማካሄድ የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው::

ከመጠይቁ የሚገኘው ምላሽ ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው ይታሰባል:: ጥናቱ የታለመውን ግብ ይመታ ዘንድ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕግሥትና በጥሞና በማንበብ ትክክል ናቸው የምትሏቸውን መልሶች እንድትገልጹልኝ ስጠይቅ ለሚደረግልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

ማሳሰቢያ:-

ሀ. በጽሑፍ መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም::

ለ. መጠይቁን ከሌላ ጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው::

### ክፍል አንድ:- አጠቃላይ መረጃ

1. የምትማርበት/የምትማሪበት ኮሌጅ ስም ____________________
2. ፆታ ____________________
3. አመት ________________

**ክፍል ሁለት:-** ከዚህ ቀጥሎ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህሮቻችሁ የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው በእናንተ ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ከቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች ትይዩ መልስ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አምስት አማራጮች ቀርበዋል:: እነዚህም አማራጮች በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃዎች የያዙ ናቸው፤

5 በጣም እስማማለሁ

4 እስማማለሁ

3 መወሰን አልችልም

2 አልስማማም

1 በጣም አልስማማም

እናንተም ከጥያቄዎቹ ትይዩ የምትሰጡትን መልስ የ "✓" ምልክት በማድረግ አስቀምጡ::

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | መምህራን የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ከመስጠታቸው በፊት ግልፅ የሆነ መመሪያ እና ማብራሪያ ይሰጡኛል:: | | | | | |
| 2 | መምህራን ሥራዎቼን ሲመዝኑ ግልፅ መስፈርት ይጠቀማሉ:: | | | | | |
| 3 | በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ በማሳያቸው ድክመቶች መምህራን የማስተካከያ እገዛ ያደርጉልኛል:: | | | | | |
| 4 | በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ መምህራን የተለያዩ የማጠናከሪያ ተግባራትን እየሰጡ ችሎታዬን የበለጠ እንዳዳብር ያደርጉኛል:: | | | | | |
| 5 | ለማከናወናቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራት መምህራን ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ይሰጡኛል:: | | | | | |
